# በጅማ ከተማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራ

# ሂደት ትንተና


በ

ዘይነባ ሽረፋ


በአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ በተግባራዊ ስነልሳን የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች አንዱን ለማሟላት የቀረበ ጥናት


ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል



ነሐሴ 2011

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በጅማ ከተማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራ ሂደት ትንተና

በ

ዘይነባ ሸረፋ

አማካሪ ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

በአማርኛ ቋንቋ በተግባራዊ ስነልሳን የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች አንዱን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2011

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ምስጋና

ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ከዳር ለማድረስ በየጊዜው ክትትል በማድረግ፣ ግድፈቶቼን በማቃናትና አቅጣጫ በማሳየት የረዱኝን የጥናት አማካሪዬን ዶ/ር ማንያለው አባተን እጅግ በጣም ከልብ አመሰግናለሁ።

ይህን ጥናት በመስክ ተገኝቼ በማካሂድበት ወቅት የጥናቱን መረጃ በፈቃደኛነት ያቀበሉኝን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ። በተለይ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለተባበሩኝ አቶ ዊዳድ አባፊጣ፣ እንዲሁም መረጃ ከእነማን ማግኘት እንደምችል አቅጣጫ ከማሳየት ጋር በመልካም መስተንገዶ የተቀበሉኝን ሼህ መሀመድአሚን አበዱልዋሂድና ቤተሰቦቻቸውን በሙሉ በጣም አመሰግናለሁ።

ይህንን ትምህርት እንድማር እና ለዚህ ጥናት መሳካት የተለያዩ ቁሳቁሳዊ ድጋፎችን በማድረግ እና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ለዚህ እንድበቃ ላደረጉልኝ ቤተሰቦቼ፣ በተለይ ደግሞ ለእህቴ ዘሀራ ሽረፋ ምስጋናዬ ከፍ ብሎ ይድረሳቸው።

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የቁባ ኣባ አረቡ የመውሊድ ክብረ በአል ስርዓተ ክዋኔ ሂደት ትንተና ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፤ የጥናቱ ዋና ዓላማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ክበራ (ከዚያራ እስከ ፍጻሜው) ያለውን ሂደት መተንተን ነው። አላማውን ለማሳካት ጥናቱ በገላጭ የምርምር ስልት በመመርኮዝ የተከናወነ ሲሆን፤ ያነሳቸው የምርምር ጥያቄዎችም (1) የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ምን ይመስላል? (2) በመውሊድ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚቀርቡት ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ እና ክብረ በዓሉን አጅበው የገቡ ቁሳዊ ባህሎች ከሐይማኖታዊ ገጽታቸው ባሻገር ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ ለመመለስ ተሞክሮዋል። አላማ ተኮርና የጓድ ጠቆም የንሞና ዘዴን በመጠቀም የጥናቱ አካባቢና ናሙናዎች ምርጫ የተከናወነ ሲሆን፤ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን  በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመሰብሰብ በአውዳዊ ወይም ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ የተደገፈ ትንተናና ማብራሪያ ቀርቧል።  በጥናቱ ግኝቶች መሰረት፤ የመውሊድ በአሉ ክዋኔ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ሁነቶች ድምር ውጤት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ከጥናቱም የተገኘው ውጤት የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ክብረ በዓል ከዋናው ዋዜማ በፊት በወንዶችና ሴቶች መውሊድ ስርአተ ክዋኔዎች የሚጀምር ሲሆን ዋናው የዋዜማ ቀን ደግሞ ረቢያል አወል 11 ሌሊት ለ12 መንጊያ ነው። በመውሊድ በአሉ የአከባበር ስርዓት ላይ የተስተዋሉት የክዋኔ ሁነቶች ዚያራ፣ ዱአ (ምርቃት)ና መንዙማ ናቸው። የነዚህ ሁነቶች አጠቃላይ መጠሪያ ‹‹ዱአይ›› እንደሚባልና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁነቶች በስፋት የተንጸባረቁበት እንደሆነ ጥናቱ ቃኝቷል። ከዚሁ ጎን የታዩት የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሒደት አንጻር በሁለት መንገድ (በድቤ እና በእንጉርጉሮ)  እንደሚባሉ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤ የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔን አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎች ከአሰራራቸውና ጠቀሜተቸው አንጻር በሶስት መልኮች (ቃላዊ ግጥሞቹን አጅበው የሚገቡ፣ የመመገቢያና ጌጣጌጥ) እንደሚፈረጁ ጥናቱ ተመልክቷል። እነዚህን ቁሶች ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸውና የተፈጥሯዊና ተለጣፊ እሴት፣ ታሪክ ነቃሽነት፣ ተወካይነትና ውስንነት ሆነው ገጽታ እንዳላቸው ጥናቱ ቃኝቷል። የቁባ ኣባ አረቡ የመውሊድ ክብረበአል ተግባርም የማጠናከር፣ የማምለጥና ማህበረሰቡን የመቆጣጠር ተግባር ያለው ከመሆኑ አንጻር ይህ መንፈሳዊ፣ ታሪካዊና ቁሳዊ ባህል ማህበረሰቡን ከማስተዋቅ አንጻር ያለው ፋይዳ ቀላል ባለመሆኑ ጥበቃ ቢደረግለት የሚል አስተያየት ተሰጥቷል።*

## የማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ

**የጥናቱ ርዕሱ፡-** *በጅማ ከተማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ክበራ ሂደት ትንተና*

**ሚጋገጫ –**

*እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩ ይህ በአማርኛ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ በተግባራዊ ስነልሳን እና ባህል የድህረ-ምረቃ ትምህርት መርሃ-ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት የራሴ የጥናት ውጤት የሆነ፣ ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሁፍነት ያልቀረበ፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ምንጮች ሁሉ በተገቢው መንገድ እውቅና ተሰጥቷቸው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ።*

ዘይነባ ሸረፋ ____________________ ____________________

**የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ**

**የጥናቱ ዋና አማካሪ**

ዶ/ር ማንያለው አባተ ____________________ ____________________

አቶ ሃብታሙ እንግዳው ____________________ ____________________

ስም *ፊርማ* *ቀን*

**የጥናቱ ገምጋሚዎች**

____________________ ____________________ ____________________

ስም *ፊርማ* *ቀን*

____________________ ____________________ ____________________

ስም *ፊርማ* *ቀን*

____________________ ____________________ ____________________

ስም *ፊርማ* *ቀን*

## ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀባቢ | የነብዩ የሙገሳ ስም |
| ላህዲ | ቀብር ውስጥ አስክሬን የሚርፍበት |
| መርሀባ | ይሁን (እሺ) |
| መርሀባ ነቢ | እሺ በሉ ነቢ |
| ሱብ | የሌሊት ስግደት |
| ሰላማለይኩም ጀማላ | ነብዩ ሰላም ለርስዎ ይሁን |
| ሰኪና | ሰላም |
| ሰይዲ | ጌታዩ |
| ሰለላ አለይ ወሰለም | የፈጣሪ ሰላም ለርስዎ ይሁን |
| ሹባኪ | መስኮት |
| ቁባ | ለኡለሞች የሚሰጥ  የቀብር ስያሜ |
| ባህሪኮ | ሁሉ የሞላሎት |
| በረካ | ጸጋ |
| በርዘንጅ | የመውሊድ ማክተሚያ መንዙማ |
| በዛሂር | በህይወት ጊዜ |
| ቢስሚላሂ | በፈጣሪ ስም |
| ኑ ፈረማ | ቃል ኪዳን ፈጽሙ |
| ከን ኒያሳ | ያሰበውን (የወሰነውን) |
| ወሲያ | ኑዛዜ |
| ወትዋዳ | እጣራለሁ |
| አላሁ ሞሰሌ | የፈጣሪ ሰላም ባንቱ ላይ ይውረድ |
| ወጁድ | መገኘት |

| | |
|---|---|
| አህለል ከይር | በጎ አድራጊ |
| አለሁመርሀም ሼከና ሁሴን | የፈጣሪ ሰላም ለሼከና ሁሴን ይሁን |
| አባ ጃርሳ | የሀገር ሽማግሌ |
| አልሀምዱሊላህ | ፈጣሪ ምስጋና ይገባዋል |
| አሊም | አዋቂ |
| ኡለማ | አዋቂዎች |
| ኢሻ | የምሽት ሰላት |
| አዛን | የሰላት ጥሪ |
| አኪራ | የመጨረሻው አለም |
| አጅር | ምንዳ (ክፍያ) |
| ከሎ አባቦኒ ዱዱ | የጀነት ጨፌ |
| ዘምዘማ | ቅዱስ ውሃ |
| ዞርባ | የጫት ጥቅል |
| ያደዋ | መድሀኒቴ (ሁሉ ነገሬ) |
| ዱአቶች | ተጣሪዎች |
| ደርጋ | ከግቢ ወጭ የሚኖሩ የአባአረቡ ካዳሚዎች |
| ጀመዓ | ስብስብ (ህብረት) |
| ጀዋበኒሩ | ተቀብለዋል |

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና …………………………………………………………………………………..iii

አጠቃሎ……………………………………………………………………………….iv

የማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ …………………………………………v

ሙዳየ ቃላት……………………………………………………………………………vi

ማውጫ…………………………………………………………………………………viii

የምስሎች ማውጫ……………………………………………………………………xii

**ምዕራፍ አንድ**

መግቢያ.....................................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..........................................................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........................................................................................3

1.3 የጥናቱ አላማዎች.....................................................................................................4

1.3.1 የጥናቱ አቢይ አላማ ……………………………..………………4

1.3.2 የጥናቱ ንኡሳን አላማዎች …………………………………..………4

1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ...................................................................................5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ .......................................................................................................5

1.6 የጥናቱ ወሰን............................................................................................................6

1.7 የመስክ ጥናት ተሞክሮ እና ገጠመኝ…………………………………………6

1.7.1 የመስክ ተሞክሮ……………………………………………..………..6

1.7.2 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች…………………………………..9

**ምዕራፍ ሁለት**

የክለሳ ድርሳናት ፍተሻ…….……………………………………………..………..11

2.1 የእስልምና እምነት አምዶች …………………………………………………..11

2.2 የመውሊድ ክብረበአል ምንነት…………………………………………………13

2.3 የመውሊድ ክብረበአል አመጣጥና እድገት…………………………………………14

2.4 መውሊድ ለምን ይከበራል?…………………………………………….……14

2.5 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት……………………………………………………………..………15
2.5.1 ክብረ በዓል………………………………………………………………….16
2.5.2. ክዋኔ……………………………………………………………………18
2.5.3 አውድ……………………………………………..…………………….….19
2.6 የጥናቱ ስልተ-ትወራ…………………………………………………...……….20
2.7 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት………………………………………………………22

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ስልትና አካሄድ……………………………………………………………26
3.1 ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ………………………………………26
3.2 የአጠናን ስልት……………………………………………………………29
3.3 የናሙና አመራረጥ…………………………………………………………..29
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች……………………………………………….30
3.4.1 ምልከታ……………………………………………………………31
3.4.2 ቃለ መጠይቅ……………………………………………………….**32**
3.4.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት………………………………………………….32
3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ………………………………………………………...33

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ መረጃ ትንተና……………………………………………………………34
4.1 የአባ አረቡ የህይወት ታሪክ፣ የቁባ አባ አረቡ መስጅድ አመሰራረትና ታሪካዊ ዳራ…………………………………………………………………………....34
4.1.1 የአባ አረቡ የህይወት ታሪክ…………………………………………….34
4.1.2 የቁባ አባ አባረቡ አመሰራረት…………………………………………….37
4.1.3 የቁባ አባ አረቡ መስጂድ አመሰራረት…………………………………….40

4.1.4 የመውለድ ክብረ በዓል ምንነትና ዓይነት……………………………………..43
4.1.5 የቁባ አባ አረቡ መውሊድ ታሪካዊ አጀማመር………………………………..45
4.2 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክዋኔ፣ ቃላዊ ግጥሞችና በዕለቱ የሚታዩ
ቁሳዊ ባህሎች……………………………………………………………………………46
4.2.1 የቁባ አባአረቡ የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔ…………………………………46
4.2.1.1 የሥርዐተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት……………………………………..……46
4.2.1.2 የሥርዐተ ክዋኔው ዋዜማ………………………………………………….49
4.2.1.3 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል፣ የበዓለ ዕለቱ ሁናቴ………………….55
4.2.2 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርዐተ ክዋኔ አካሄድ……………………………58
4.2.2.1 ዝያራ…………………………………………………………………………...59
4.2.2.2 ዱኣ (ምርቃት)……………………………………………………...….64
4.2.2.3 መንዙማ…………………………………………………………………….76
4.2.2.4 የክዋኔዉ ማግስት ሁነቶች…………………………………………………..78
4.3 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በኣል ላይ የሚከወኑ ቃለዊ ግጥሞች ክዋኔ……………..80
4.3.1 በዱፊ የሚባሉ መንዙማዎች…………………………………………...……...83
4.3.2 በእንጉረጉሮ የሚቀርቡ መንዙማዎች…………………………………………..88
4.4 የቁባ አባአረቡ የመውሊድ ክብረበዓልን ለማጀብ የገቡ ቁሳዊ ባህሎች………………92
4.4.1 የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች (ዱፊ፣
ኡሌ ዱፊ እና አሸቀ)…………………………………………………………………..94
4.4.2 በክብረ በዓሉ ለመመገቢያ የዋሉ ቁሳዊ ባህሎች……………….…………….96
4.4.2.1 የመመገቢያ ቁስ……………………………………….…………….97
4.4.2.2 ለመጠጫ የዋሉ ቁሳዊ ባህሎች ……………………..………………….98
4.4.2.3 በክብረ በአሉ እለት የታዩ ጌጣጌጦች………………………………………99
4.4.2.3.1 ከእጨት የተሰሩ……………………………………..…………100
4.4.2.3.2 ከጨሌ የተሰሩ…………………………………………………..103
4.5 የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር (Function)…………………………………………106

**ምዕራፍ አምስት**

**የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት**……………………………………………………108
5.1 **የጥናቱ ማጠቃለያ**…………………………………………………………..108
5.2 **አስተያየት**……………………………………………………………………110

**ዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች**…………………………………………………………112
**አባሪዎች**……………………………………………………………………………..114
**አባሪ አንድ፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች**

**አባሪ ሁለት፡ የመረጃ አቀባዬች ስም ዝርዝር**

**አባሪ ሶስት ፡-በቁባ አባ አረቡ መውሊዱ ላይ የሚቀርቡት መንዙማዎች (ቃል ግጥም)**

**በመገኛ ቋንቋ (ኦሮምኛ)**

**አባሪ አራት ፡-በቁባ አባ አረቡ መውሊዱ ላይ የሚባሉት መንዙማዎች (ቃል ግጥም)**

**ትርጉም በአማርኛ ቋንቋ**

**አባሪ አምስት፡ የመንዙማ ክብረበአሉን ክዋኔ ገጽታ የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶዎች**

## የምስሎች ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

*ምስል አንድ፦ መውሊዱ የሚከበርበትን ቦታ የሚያሳይ ፎቶ……………………………42*

*ምስል ሁለት፡ እርድ ሲካሄድ የሚያሳይ ፎቶ……………………..……………………51*

*ምስል ሦስት፡ ገንፎ ሲመገቡ የሚያሳይ ፎቶ ……………………………………………….53*

*ምስል አራት፡ የቁባ (የአባ አረቡ) መቃብር ፎቶ ………………………………………..54*

*ምስል አምስት፡ ምእመናን ዚያራ ሲከውኑ የሚያሳይ ምስል………………………..……62*

*ምስል ስድስት፡ ጫት ሲቃም የሚያሳይ ፎቶ………………………………………………65*

*ምስል ሰባት፡ ከቁባው ውጭ የነበሩ የበዓሉ አክባሪዎች ፎቶ……………..………………73*

*ምስል ስምንት ፡ ቁሳዊ ባህሎቹን የሚያሳዩ ፎቶዎች ……………………………………93*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ከአምስቱ የእስልምና እምነት ምሰሶዎች - ሻሐዳ (Shahada) በአላህና በነቢዩ መሃመድ የማመን መንፈሳዊ ድንጋጌ፣ ሳላት (Salat) በቀን አምስት ጊዜ የሚከናወን የጸሎት ስርአት፣ ዛካት (Zakat) ለተቸገሩና ለድሆች ምጽዋት የመስጠት ግዴታ፣ የአስልምና ጾም ስርአት እና የሃጂ መንፈሳዊ ጉዞ (Hajj) - እያንዳንዱ የእስልምና እምነት ተከታይ ከሚያከብራቸው የእምነቱ መገለጫዎች በተጨማሪ በእስልምና ህግ የመንጻት ስርአት (Ritual purity) እና ሌሎች የእምነቱ ተከታዮች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ክብረበአላት አሉ። ከእነዚህ መካከል መውሊድ አንዱና ትልቁ የእስልምና መንፈሳዊ ክብረበአል ነው (ሀሰን /ኡስታዝ/፣ 2009፣ 12)።

ከሀይማኖት ጋር የተያያዙ የተወሰኑ መንፈሳዊ ክንዋኔዎችና የሚከበሩ በአላት ለእስልምና እምነት ተከታዮች በጣም አስፈላጊ መሆናቸው ይታመናል። እነዚህ ከእስልምና እምነት ጋር ተያይዘው የሚታሰቡ መንፈሳዊ ክንውኖች በእስልምና ታሪክ ውስጥ ረጅም እድሜ ያስቀጠሩ፣ የጽኑ እምነት ብሎም ለአላህ (ፈጣሪ) ታማኝነት፣ ፍቅር፣ የእምነቱ ፍላጎትና ራስን መስጠት ብርቱ መገለጫዎች ናቸው። ከእነዚህ የእስልምና እምነት ተከታዮች የግልና የጋራ መንፈሳዊ ክንዋኔዎች መካከል አንዳንዶቹ በየቀኑ የሚዘወተሩ (ለምሳሌ፡- የጸሎት ስርአት) ሲሆኑ፤ ሌሎች በየአመቱ የሚከበሩ የአስልምና ሃይማኖት ክብረበአላት አሉ። የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያከናውኗቸው መንፈሳዊ ተግባራትና ክብረበአላት በቁጥር የተወሰኑ ሲሆኑ፤ ማናቸውም መንፈሳዊ ክንዋኔ አምስቱን የእስልምና እምነት አምዶች ህገ-መሰረት ያደረጉ ናቸው። ከሌሎች እምነቶች ሲነጻጸርም እስልምና ያሉት ክብረበአላት ጥቂት የሚባሉ ሲሆኑ፤ የእምነቱ ተከታዮች በመንፈሳዊ ስርአት መሰረት እንደ ትእዛዝ ወይም ቃል የሚከተሏቸውና ቅዱስ አድርገው የሚየስቧቸው ቀናት ናቸው (Kaplan, 2015)።

የእስልምና እምነት ክብረበአላት በአጠቃላይ ሲጤኑ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በወል ተግባርነት የተለመዱ ለፈጣሪ ክብር፣ መውደድ ሲባሉ የሚከናወኑ፣ በእምነቱ ውስጥ በጉልህ የሚታወቁትን ነቢይ ለማሰብና ለእምነቱ ተከታዮች ያወረሱዋቸውን ታላላቅ መንፈሳዊ መሰረቶች ለማዘከር ሲባሉ የሚካሄዱ የአክብሮት መገለጫዎች ናቸው። በዚህ መሰረት ዋንኞቹ የእስልምና እምነት ክብረበአላትና በአላቱን ተከትለው የሚፈጸሙ ሁነቶች ታላቁን የእምነቱን አስተምህሮቶች ፈጣሪ ነቢዩ መሃመድን ለማስታወስ እና ነቢዩ የመሰረቷቸውን ልዩ የተባሉ ቀናት ለማሰብ ሲባል የሚከናወኑ ናቸው (Brill, 2008)።

በልማዳዊ መንገድ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሁሉ የሚያስቧቸው ሁለት ዋንኛ መንፈሳዊ ክብረበአላት ኢድ አል-ፈጥርና ኢድ አል-አድሃ አረፋ ሲሆኑ፤ ሙስሊም የሆኑ ሁሉ በፈቃደኝነት የሚገቡባቸው ለአንድ ወር ጊዜ ቀኑን ሙሉ የሚጾምባቸው ቀናት (a day voluntary fasting) ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ መካከል የመውሊድ ክብረበአል በአመት አንድ ጊዜ የነቢዩ መሃመድን ልደት ለማሰታወስ ሲባል በእምነቱ ተከታዮች በጋራ የሚከበር

በአል ነው። የእስልምና ተከታዮች ሁሉ የነቢዩ መሃመድ የልደት ቀንን በእስልምና የቀን አቆጣጠር (Rabi' al-Awwal) መሰረት በሦስተኛው ወር በ12ኛው ቀን ያከብራሉ። የጨረቃ የቀን አቆጣጠር (lunar calendar) በየአመቱ 11 ቀናት ወደፊት ስለሚቀድም የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀን በየአመቱ ይለዋወጣል (Reynolds, 2017)።

ይሁንና ሁሉም የእስልምና እምነት ተከታይ ሀገሮች መውሊድ ተብሎ የሚጠራውን የነቢዩ መሃመድ የልደት ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ አያከብሩትም። ለምሳሌ የሱፊ እስልምና አማኞች (Sufistrains of Islam)እንዲሁም እንደ ሳውዲ አረቢያ ያሉ ሀገሮች የእምነቱ ተከታዮች የልደት ቀኑን ሕዝባዊ ክብረበአል አድርገው ከመውሰድ ይልቅ እንደ አላስፈላጊ ሃይማኖታዊ ፈጠራ (religious innovation) ይቆጥሩታል። በአብዛኛዎቹ የእስልምና እምነት ተከታይ ሀገሮች የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀን የነቢዩን ክብር በሚያወድሱ የምስጋና መዝሙሮች (ዝየራዎች) እና ግጥሞች ታጅቦ ይከበራል። እነዚህ የምስጋና መዝሙሮችና ግጥሞች ነቢዩ መሀመድ ከፈጣሪ ዘንድ ለእምነቱ ተከታዮች ሁሉ የተቀበሉትን ይቅርታና ምህረት የሚያስታውሱና ጥልቅ መንፈሳዊ አክብሮትን የሚዋጁ ሲሆኑ የበአሉ አከባበር ልማድ በየሀገሮቹ ይለያያል (Reynolds, 2017)።

የመውሊድ በዓል በሀገራችን የእስልምና እምነት ተከታዮችዘንድ ከነቢዩ መሀመድ ውልደት (ልደት) ቀን ጋር በተያያዘ ሁኔታ ይከበራል።ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ሰዎች መውሊድን ደግሶ ለሰዎች(ለድሆች)ከማብላት ጋር አያይዘው ትርጉም ይሰጡታል (ኡስታዝ ሀሰን፣ 2009፣12)።

ኡስታዝ ሀሰን (2009፣12) መውሊድን በተመለከተ እንደገለጹት፤ "መውሊድ" ሥርወ-ቃሉ ወለደ የሚለው የአረበኛ ግስ ሲሆን፤ ቋንቋዊ ትርጉሙም ‹የውልደት ስፍራ ወይም እለት› ማለት መሆኑንና በኡለሞች ዘንድ የታላቁን ነብይ የልደት ቀን በተለየ ከበሬታ የመዘከርን ሁኔታ ለመግለጽ ማገልገሉን፤እንዲሁም በሀገራችን ህዝባዊ አጠቃቀም ደግሞ በየትኛውም ጊዜና ቦታ አላህን (ፈጣሪን)ለመለመን የሚደረግን መሰባሰብ በተለይም ድሆችን ሰደቃ የማብላትን ድርጊት እስከ ማጠቃለል የሚደርስ ሰፋ ያለ ትርጉም ይይዛል።

መውሊድን በሚያከብሩ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሁለትአይነት የመውሊድ ክብረ በአላት አሉ።አንደኛው የረቢያል አወል መውለድ (የነቢዩ መሐመድ የልደት በአል) ሲሆን ይህም የሂጅራ ዘመን አቆጣጠርን የሚከተል ነው።ሁለተኛው የመውለድ አይነት የኡለማ (አሊም) መውሊድ መሰረት በማድረግ የሚከበር ሆኖየነብዩ መሐመድ ኢስላማዊ አስተምህሮዎች የሚቀርቡበት ሲሆን፤ ይህም ኡለማ(አሊም) መውሊድታላላቅ ሰዎችን ለማስታወስ ፣ የሰሩትን ስራ ለማወደስ ሲባል የሚከበር ነው። ክብረ በአሉ በእምነታዊ ገጽታው ተመሳሳይ ቢሆንም በአከዋወን ስርአቱ እንደ አካባቢው ባህል ፣ ቋንቋ ፣ አኗኗር እና የግንዛቤ ደረጃ ልዩነት ሊፈጠር ይችላል ። ልዩነቱ ደግሞ የማህበረሰቡ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል (አብዱራህማን፤2007)።

በዚህ ጥናትም በጅማ ከተማ የቁባአባ አረቡ የመውሊድ በአልን (ኡለማ መውሊድን) መሰረት በማድረግ የስረአተ-ከበራውን ሂደት ከነክዋኔው እንዲሁም ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳውን አውድን መሰረት በማድረግ ተዳሶ ቀርቧል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው።የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ ማህበረሰቡ ይህን በጅማ ከተማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስፍራን ለምን ለመውሊድ በአል ማክበሪያነት ለምን መረጠው፤ ከሌላ ቦታ ምን የተለየ ሚስጥር አለው? የሚለው ጥያቄ ሁሌም የመውሊድ በኣል በደረሰ ጊዜ ሁሉ በአዕምሮዬ ውስጥ መመላለሱና በዚህ ታሪካዊ ስፈራ ያሉትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለማወቅ ካደረብኝ ፍላጎት የተነሳ ነው።

ሁለተኛው ምክንያቴ ደግሞ ይህእኔ የማጠናው የኡለማ መውሊድ በአካዳሚው አለም ብዙም ያልተጠና ጥናት በመሆኑ፤ያለመጠናቱ ለጥናቱ ትኩረት እንድሰጥ ሌላኛው ምክንያት ሆኖኛል። የቁባ አባ አረቡን የህይወት ታሪክ ምን እንደሚመስል፣ የመውሊድ በዓሉ አመሰራረት እና አጀማመር፣በከበራው ላይ ያሉት ስርዓቶችና ሁነቶች ትስስር፣ ከልዩ ልዩ ቦታ የሚመጡ ምእመናን ላይ ያለውን ተጽእኖ ማጥናቱ ክብረ በዓሉን በጉልህ እንዲታወቅ ያደርጋል።ይህንን በማሰብም ለጥናቱ እንድነሳሳ አድርጎኛል።

ሶስተኛውና የመጨረሻው የአካባቢው ተወላጅ እንደ መሆኔ መጠን የተጠኚውን ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ በማወቄ መረጃውን ለማግኘት አይቸግረኝም ብዬ በማሰቤ እና እንደ ፎክሎር ተማሪነቴ የታሪካዊ ስፍራውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በማጥናት ለትውለድ ለማስተላለፍ ካለኝ ፍላጎት የተነሳ ነው። ይህም ለፎክሎር አካዳሚያዊ መስኩ መጠነኛም ቢሆን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል።

ከዚህ ቀደም የቁባ አባ አረቡን ታሪካዊ ስፍራን መሰረት በማድረግ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ ጥናቶችን ለዚህ ጥናት ዝግጅት በማደርግበት ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ትምህርት ክፍልየተሰሩ ጥናቶችን ለማስተዋል ችያለሁ። እነዚህ ሁለት ጥናቶች የቦታውን ታሪካዊነትና ታሪካዊ ያደረጉትን ጉዳዮች ላይ በማትኮር የተሰሩ ጥናቶች ሲሆኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮች አልተካተቱበትም። ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት የቁባ አባ አረቡን የመውሊድ በዓል መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (ኡለማ መውሊድን) አከባበር፣ ስርአተ ክዋኔውን እንዲሁም ማህበራዊ እና ባህላዊ ፋይዳውን አውዱን መሰረት በማድረግ ተጠንቶ ቀርቧል። በዚህም በቀደሙት ጥናቶች ላይ ያልተስተዋለውን የከበራ ስርዓትና የሁነቶች ትስስር፣ የክዋኔው ማህበራዊ ፋይዳ፣ የክዋኔው ባህላዊ ፋይዳና የሚፈጸሙ ድርጊቶችንና ሁነቶችን እንዲሁም ክብረ በአሉን አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል።

## 1.3 የጥናቱዓላማዎች

### 1.3.1 የጥናቱ አቢይ አላማ

የዚህ ጥናት ዋንኛ ዓላማ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራ (ከዚያራ እስከ ፍጻሜው)ያለውን ሂደት መመርመር ነው።

### 1.3.2 የጥናቱ ንኡሳን አላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ንኡሳን አላማዎች አሉት፡-

1. በጅማ ከተማ የሚከበረው የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራን መግለጽ፡-
2. በስርአተ-ከበራ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ቁሳዊ ባህሎችና ቃል-ግጥም (መንዙማ) ለበአሉ የሚሰጡትን ፋይዳ መተንተን።
3. የበዓሉ ተሳታፊዎች ስለ ቁባ አባ አረቡ ማንነትና ስለ መውሊድ በአሉ ያላቸውን አመለካከት ማብራራት።
4. የመውሊድ በአሉ ለተሳታፊዎችየሚያስገኝላቸውን ባህላዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ መዘርዘር ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ከላይ የተጠቀሱትን የጥናቱን አላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎችበጥናቱ ይመለሳሉ።

1. በጅማ ከተማ የሚከበረው የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራ ምን አይነት ገጽታ አለው?
2. በስርአተ-ከበራ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ቁሳዊ ባህሎችና ቃል-ግጥም (መንዙማ) ለበአሉ የሚሰጡት ፋይዳ ምንድነው?
3. የበዓሉ ተሳታፊዎች ስለ ቁባ አባ አረቡ ማንነትና ስለ መውሊድ በአሉ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. የመውሊድ በአሉ ለተሳታፊዎች የሚያስገኝላቸውን ባህላዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ምንድነው?

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

የአንድ ማህበረሰብ ክብረበአልና ስርዓተ-እምነት ማጥናት የማህበረሰቡን ልማድ፣ ባህል፣ወግ፤ የህይወት ፍልስፍናና ማህበረሰባዊ ታሪኩን በጽሁፍ ወይም በሌሎች የመረጃ ማቆያ ዘዴ በመጠቀም ለተተኪው ትውልድ ለማቆየት ይረዳል። በዚሁ መሰረት ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያበረክታል።

- ስለ ቁባ አባ አረቡ ታሪካዊ ስፍራ እና የመውሊድ በአል በዚህ ስፈራ መከበሩ ለምን እንዳስፈለገ ማወቅ ለሚሹ ሰዎች መረጃ ይሰጣል።
- በስርአተ-ከበራ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ቁሳዊ ባህሎችና ቃል-ግጥም (መንዙማ) ለበአሉ የሚሰጡት ፋይዳ በመተንተንና በመሰነድ ትውፊታዊ ቅርስ አድርጎ የማቆየት ጠቀሜታ አለው።
- የመውሊድ በአሉ ለተሳታፊዎች የሚያስገኝላቸውን መንፈሳዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ለትውልድ ለመሰነድ ይጠቅማል።
- ወደፊት በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ስለሚከበረው መውሊድ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ለሚፈለግ ተመራማሪ እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

- ከዚህም በተጨማሪ ለፎክሎር ትምህርትክፍሉ በዚህ  ርእስ ዙሪያ ጥናት መሰራቱ ያለውን አካዳሚያዊ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል አበርክቶ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.6 **የጥናቱ ወሰን**

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በኦሮሚያ ክልል በጅማ ከተማ በጅሬን ቀበሌ በሙጃ ቀበሌና በዙሪያው ባሉ አካባቢዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው።ርእሰ ጉዳዩን አስመልክቶ የተካሄደው ጥናት በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚታወቁትን ክብረበአላት ሁሉ ላይ ያተኮረ አይደለም። ጥናቱ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየአመቱ በሚከበረው የነቢዩ መሃመድ የልደት በአል (መውሊድ) አከባበር ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። በይዘት ደረጃ የመውሊድ እስላማዊ ክብረበአል በቁባ አባረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ-ከበራ(ከዚያራ እስከ ፍጻሜው)ያሉትን ሂደቶችና የሚፈጸሙ ሁነቶች  ትንተና ላይ የተወሰነ ነው። ከዚያራ እስከ ፍጻሜ ሲባልም በመውሊድ በአሉ ሂደት ውስጥ የሚካሄዱትን ልዩ ልዩ ክብረበአላዊ ድርጊቶች /ሁነቶች/፣ ክብረበአሉን ለማጀብ የሚቀርቡ መንዙማዎች /መዝሙሮች/፣ ቃላዊ ግጥሞችና ቁሳዊ ባህሎችን ያካትታል።

## 1.7 **የመስክ ጥናት ተሞክሮ እና ገጠመኝ**

### 1.7.1 **የመስክ ተሞክሮ**

ለዚህ ጥናት መረጃ ለማግኘትለጥናት ወደ ተመረጡት ቦታዎች የተደረጉት ጉዞዎች ሁለት ጊዜ የተከናወኑ ሲሆን ሂደታቸውም የሚከተለውን ይመስለላል።በመጀመሪያ ጉዞ ከማድረጌ በፊት በቀን 05/03/2011 ዓ.ም የቀድሞው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት  ሀላፊ የነበሩትን አቶዊዳድ አባፊጣን ስለጉዳዩ ሳማክራቸው፤‹‹ከመጓዝሽ በፊት ዝግጅቱ መች እንደሚጀምር ማረጋገጥ  አለብሽ።›› በማለት ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ብለው ላሰቡት ለሼህ መሀመድአሚን አብዱልዋሂድ በመደወል ዝግጅቱ ከመች ጀምሮ እንደሚካሄድ አረጋገጡልኝ። በዚሁ መሰረት በቀን 08/05/2011 የአካባቢው ወንዶች ለሚያከብሩት የዋዜማ የመውሊድ በዓል  በ07/03/2011 ዓ.ም ከአንድ እህቴና ወንድሜ ጋር አስፈላጊውን የመረጃ መቀበያ መሳሪያዎች አሟልተን ከቤታችን እስከዚያው የሚያደርሰን ባጃጅ ኮንተራት ይዘን ከጥዋቱ 3፡20 ላይ በቦታው ተገኘን።

እንደደረስን በቦታው ወዲያ ወዲህ የሚንቀሳቀሱበርካታ ሰዎች ይታዩ ነበር። አመጣጣችን በአካባቢው ለነበሩ ሰዎችአዲስክስተት ስለነበረ እንግዳ ስሜት አየሁባቸው። እኔ ምንም ስሜት ያልተፈጠረብኝ በማስመሰል ሰብሰብ ብለው የቆሙትን ሰዎች ጠጋ በማለት ‹‹አሰላሙ አለይኩም ጀሪ ኬኛ›› በማለት የነሱ አካል መሆኔን ለመግለጽ ሞከርኩ።ከዚያም  በኋላ ስለተገኘሁበት አለማና ምክንያት አስረድቼ ፍቃደኛነታቸውን አገኘሁ።ቀጠል አድርጌ  ሼህ መሀመድአሚንአብዱልዋሂድን የት ላገኛቸው እንደምችል ጠየኳቸው። ከመሀከላቸው ልጅ የሚመስለው ‹‹ያኚውልሽ በሬው አጠገብ የቆሙት ጉፈታ ያደረጉት›› በማለት አመላከተኝ።እኔም አብረውኝ ከነበሩት እህትና ወንድሜ ጋር በመሆን ወደተጠቀምኩት ሰው በመጠጋት በመጀመሪያ ኢስላማዊ ሰላምታዬን አቀረብኩላቸው።ከዚያም በኦሮምኛ ከየት እንደ መጣሁ፣ ለምን እንደመጣሁና ማን ከሳቸው ጋር እንድገናኝ

እንደጠቀመኝ ስነግራቸው፤ በጣም ደስ ብሏቸው፣ ምንም ችግር እንደሌለና አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንደሚያደርጉልኝ ፍቃደኝነታቸውን ገለጹልኝ።

ከዚያም ቤታቸው እዚያው ጎረቤት በመሆኑ፤ ‹‹የተሸከምሸውን እቃ ማስቀመጥ፤ እንዲሁም ለማረፍ ከፈለጋችሁ በኋላ ላይመች ስለሚችል በጊዜ ከቤተሰቦቼም ጋር ላስተዋውቃችሁ። ቤቴንም ላሳያችሁ።›› በማለት ወደ ቤት ወስደውን ከልጆቻቸውና ከባለቤታቸው ጋር ካስተዋወቁን በኋላ ለጊዜው የማንፈልጋቸውን እቃዎች አስቀምጠን የምንፈልገውን ብቻ ይዘን ቤት ያሉትን ሰላም ብለናቸው ወጣን። ወደ ቁባው ስንመለስ ሸህ መሀመድ አሚን መረጃ በደንብ አላቸው ብለው ካሰቧቸው ትላልቅ አባቶች ዘንድ ሊያሥተዋውቁኝ በቁባው ግቢ ውስጥ በሚገኘው አንድ የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ይዘውኝ ገቡ።እንደደረስንም ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፤ ለምን እንደመጣሁ ሸህ መሀመድአሚን አግባብተው ነገሯቸው።ከመሀከላቸው አንዱ ‹‹እሱስ ይሁን የኛ ናት። እስካሁን እዚህ ከነበረች እስካሁን የት ነበረች? እራሷ ትመልስ›› በማለት ኮስተር አሉ።እኔም እንዲህ በማለት ለማግባባት ሞከርኩ። ‹‹በመጀመሪያ እስካሁን ላለመምጣቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ።ይህ የሆነውም ባለማወቅ ነው። አሁን የመጣሁትም በመማሬና እንዲህ አይነት ታሪካዊና የተቀደሰ ስፍራ መኖሩን በመገንዘቤ ይህን ታሪካዊ ስፍራ እንደኔ ሳያውቁ ለቀዩት አጥንቼ ሳበቃ የቁባ አባ አረቡን ታሪክ ለመሰነድና ዘመን ተሻጋሪ ለማድረግ ከማሰቤ የተነሳ ነው።›› በተወሰነ መልኩ ለማግባባት ሞከርኩ።እቤት ውስጥ ካሉት ትንሽ በጎልማሳነት እድሜ ያሉት በኦሮምኛ ድምጻቸውን ቀነስ አድርገው ‹‹ሀሊ ኢሳኒ ጀረ ዋቢያ ፈካቱ።›› ሲሉ ስለሰማኋቸው፤ እኔ ሌላምንም አላማ ከበስተኋለዬ እንደሌለና ሸህ መሀመድ አሚን ዋስ ሊሆኑልኝ እንደሚችሉ አስተዛዝኜ ተናገርኩ። ከዚያም የተወሰኑት ምንም አይነት የፎቶ ካሜራም ሆነ ቪዲዮ ካሜራ መጠቀም እንደማልችል፤ በጽሁፍና በድምጽ መጠቀም እንደምችል ገለጹልኝ።

እኔም በተባልኩት መሰረት ፍቃደኛ ለሆኑት ካሜራ እየተጠቀምኩ መረጃመሰብሰቤን ቀጠልኩ።የመሰጂዱ ኢማምና የመውሊዱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሆኑት ሼህ መድአሚን ‹‹የዛሬው ዝግጅት ለነገው በአካባቢው ወንዶች ለሚከበረው መውሊድ ነው። ከዚያቀጥሎ ደግሞ የአካባቢው ሴቶች መውሊድ ይቀጥላል።ዋናው መውሊድ የሚከበረው በ12 ነው። ከፈለግሽ ወደቤትሽ ሄደሽ ለመመለስ ጊዜ ስላለሽ ትችያለሽ።›› ሲሉኝ ‹‹አይ በወንዶቹም በሴቶቹም የአካባቢ መውሊድ ላይ መገኘት ስለምፈልግ እቀያለሁ›› አልኳቸው።

ከዚያም በቀን 8 እና በቀን 9/5/2011 የተከበረውን መውሊድ ተከታትዬ እና መረጃዎቹን ሰብስቤ በቀን10/5/2011 ከ10፡00 ሰዓት በኋላ ሁሉም የመጡት ሴቶች ወደ የቤታቸው በመግባታቸው፤ የበዓሉ ፍጻሜ መሆኑን አረጋገጥኩ።እኔም ከመጣሁ ከሁለት ቀን ቆይታ በኋላ  ዋናው (በ12/5/2011 የሚከበረው) መውሊድ ለአምስት ተከታታይ ቀናት እንደሚቀይ እና እስከ ቀን 11/5/2011 ምሽት ምንም የተለየ ነገር እንደ ሌለ ስለተነገረኝ፤ ማስተካከል ያለብኝን ነገር ለማስተካከል ከቀኑ 10፡45 ከቦታው ወደቤት ለመመለስ ጉዞ ጀመርን። በእግራችን 1.3ኪ.ሜ ያህል ተጉዘን አባጅፋር ቤተ መንግስት ስንደረስ ከምሽቱ 12፡30 ነበር።ከዚያም ወደ ጅማ ከተማ የሚያደርሰንን ታክሲ አግኝተን ወደ ቤታችን ተመለስን።

ከዚያም በ10/05/11 ዓ.ም ለቀጣይ ጉዞ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች አስተካክዬ አመሸሁ። በነጋታው ሰኞ በ11/05/11 ዓ.ም በተለመደው ባጃጃችን ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን አሟልቼ፤ ከቀድሞ ረዳቶቼ ጋር ከአስር ሰላት በኋላ የበአሉ ማክበሪያ ቦታ ደረስን። በዚህ እለት ቦታው እጅግ በሰው ብዛት የተጨናነቀ በመሆኑቦታ አግኝቶ ለመቀመጥ ሁኔታውአስቸጋሪ ነበር። አስቀድሜ የተዋወኳቸው የአካባቢውን ሰዎች ስላገኘሁ ለምጠይቃቸው ጥያቄ ‹‹እከሌ ከእከሌ ይሻላል››እያሉ በሰጡኝ የመረጃ አቀባዮች ጥቆማ በመታገዝ አስፈላገውን መረጃ ሁኔታው በፈቀደው መንገድ ለመሰበሰብ ችያለሁ።ለቡድን ውይይት የተሻሉ ናቸው ያሉትን ሼህ መሀመድአሚን አብዱልዋሂድ መርጠው ስለሰጡኝ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መረጃዬን በተሳካ መለኩ እንድሰበስብ ረድተውኝ ከቀን 11-15 ያለውን ክንውን አጠናቅቄ በቀን 15/03/11 ዓ.ም ከምሽቱ 12፡10 ወደ መኖሪያ ቤታችን ተመለስን።

### 1.7.2 ያጋጠሙ ችግሮች ና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ምን ምን እንደነበሩና ለማቃለል የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበዋል።ጥናቱ የመስክ ስራን (የኢ-ከዋኝ ታዛቢ የመረጃ አሰባሳቢነት ብልሃት) የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። መስክ ላይ ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

የመጀመሪያው ችግር ለጥናቱ በመረጃ አቀባይነት ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች ውስጥ ስምንቱ ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ የበአሉ ተሳታፊዎች ናቸው። እነዚህን እንግዳ ሰዎች ለማነጋገር ደግሞ የጥናቱን ዓላማ በስርአት ማስረዳት ግድ ይላል። ነገር ግን አብዛኞቹ የተለየ ፊት በማየታቸው ማንም ሰው ቢያስረዳቸው ከጥርጣሬያቸው ነጻ መሆን በቀላሉ አልቻሉም ነበር። የጥርጣሬያቸው ዋነኛው ምክንያት እንደተነገረኝ ‹‹መውሊድን ለማጥፋት የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው›› የሚል ነበር። ካሜራ ሲመለከቱማ በግልጽ አውጥተው ‹‹ካሜራ የያዘ ሰው ጤና የለውም፤ እኛ በአባ አረቡ ካሜራ እንኳ በማንም ተራ ካሜራ አንቀረጽም›› በማለት ፊታቸውን ሲያዞሩብኝ፤ ከነዚህ መረጃ አቀባዮች የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት የተሻለ ሌላ አማራጭ መፈለግ ነበረብኝ።

ሁለተኛው ችግር ጥናቴን ተጨባጭ ለማድረግ የተጠቀምኩት ቪዲዮ ካሜራናፎቶ ካሜራ ሁለቱን በአንድ የያዘ በመሆኑ የተወሰኑ መረጃዎችን ከሰበሰብኩ በኋላ ያለመቀያየር ወይም የመድረቅ ስሜት አሳየኝ።ይህም ሌላው አሳዛኝና እልህ አስጨራሽ ፈተና ሆኖብኝ ነበር።

በጥናቱ ያጋጠመኝ ሶስተኛው ችግር አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ ድምጻቸውን እንኳ በቪዲዮ ካሜራም ሆነ በፎቶ ካሜራ እንዳይቀረጽ መከልከላቸውና ፎቶግራፍ አንነሳም ማለታቸው ነው።

በመስክ ላይ ያጋጠሙኝን ችግሮች የፈታሁት በሚከተለው መልኩ ነው።እነዚህ ስምንቱም ሰዎች ከተለያየ ቦታ እንደመምጣታቸው አቀማመጣቸውም በቅረብ ርቀት ሆኖ በቤት ውስጥ በሶስት ቡድን ተከፍለው ነበር የተቀመጡት። ነገርግን እርስ በርስ ያለመስማማታቸውን ስሜት ሲያሳዩ የነበረው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ መቀጠሉ እንደማያዋጣ በመገመት ከወንድሜ ጋር ተመካክረን ና በ12/03/11 ዓ.ም ምሽት ላይ በሶስት ቡድን ተከፍለው

ለተቀመጡት መረጃ አቀባዮቼ ሶስት ዞርባ (ጥቅል) ጫት፣ ለእያንዳነዱ ቡድን ስኳርና ነድ ገዝቼ፤ በየቡድኑ የያዝኩትን ከፊት ለፊታቸው እያስቀመጥኩ ‹‹ሀጃዬእንዲወጣ ዱአ አድርጉልኝ›› በማለት ሁሉንም በሚያማክል መሀል ላይ በመቆም እጄን ወደፊት ዘርግቼ አንገቴን ደፍቼ ቆምኩ። ከዚያም ዱኣ ተደርጎልኝ የዱአ ጫት ተሰጥቶኝ ወደ ቡድኑ መቀላቀል በመቻሌ መረጃዬን ለመሰብሰብ ችያለሁ። (ጫት በእስልምና ሃይማኖታዊ ስነስርአት ለጸሎት ማካሄጃ በሰፊው ጠቀሜታ ላይ ይውላል።)

ሁለተኛው ችግር የተቃለለው የተበላሸውን ካሜራ በወንድሜ ወደ ከተማ በመላክ እንዲሰራ በማድረግና ተሰርቶ እስኪመጣ ያለውን በማስታወሻ ደብተሬና በመቅረጸ ድምጽ በመጠቀም በሰአቱ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ችያለሁ።

ሶስተኛው እና የመጨረሻውን ችግር ያቃለልኩት ደግሞ ምስላቸውን በቪዲዮካሜራ እናበፎቶ ካሜራ መስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን መረጃ አቀባዮች መቅረጸ ድምጽ በመጠቀምና መረጃው ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ በጽሁፍ በማስታወሻዬ ለማስፈር በመሞከር ነው።

# ምዕራፍሁለት
# የክለሳ ድርሳናት ፍተሻ

በዚህ ምዕራፍ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ተዳሰው ይቀርባሉ።በመጀመሪያው ክፍል የእምነት ከበራ፣ ክዋኔ እና አውድ በሚሉ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ንድፈ ሐሳባዊ ማብራሪያ ቀርቧል።በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከእኔ የጥናት ርዕስ ጉዳይ ጋር ቅርበት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተከልሰው ቀርበዋል።

## 2.1 የእስልምና እምነት አምዶች

ከአምስቱ የእስልምና እምነት ምሰሶዎች - ሻሐዳ (Shahada) በአላህና በነቢዩ መሃመድ የማመን መንፈሳዊ ድንጋጌ፣ ሳላት (Salat) በቀን አምስት ጊዜ የሚከናወን የጸሎት ስርአት፣ ዛካት (Zakat) ለተቸገሩና ለድሆች ምጽዋት የመስጠት ግዴታ፣ የአስልምና ጾም ስርአት እና የሃጂ መንፈሳዊ ጉዞ (Hajj) - እያንዳንዱ የእስልምና እምነት ተከታይ ከሚያከብራቸው የእምነቱ መገለጫዎች በተጨማሪ በእስልምና ህግ የመንጻት ስርአት (Ritual purity) እና ሌሎች የእምነቱ ተከታዮች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ክብረበአላት አሉ። ከእነዚህ መካከል መውሊድ አንዱና ትልቁ የእስልምና መንፈሳዊ ክብረበአል ነው (ሀሰን /ኡስታዝ/፣ 2009፣ 12)።

ከሀይማኖት ጋር የተያያዙ የተወሰኑ መንፈሳዊ ክንዋኔዎችና በጣም የሚከበሩ በአላት ለእስልምና እምነት ተከታዮች በጣም አስፈላጊ መሆናቸው ይታመናል። እነዚህ ከእስልምና እምነት ጋር ተያይዘው የሚታሰቡ መንፈሳዊ ክንውኖች በእስልምና ታሪክ ውስጥ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ፣ የጽኑ እምነት ብሎም ለአላህ (ፈጣሪ) ታማኝነት፣ ፍቅር፣ የእምነቱ ፍላጎትና ራስን መስጠት ብርቱ መገለጫዎች ናቸው። ከእነዚህ የእስልምና እምነት ተከታዮች የግልና የጋራ መንፈሳዊ ክንዋኔዎች መካከል አንዳንዶቹ በየቀኑ የሚዘወተሩ (ለምሳሌ፡- የጸሎት ስርአት) ሲሆኑ፤ ሌሎች በየአመቱ የሚከበሩ የአስልምና ሃይማኖት ክብረበአላት አሉ። የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያከናውኗቸው መንፈሳዊ ተግባራትና ክብረበአላት በቁጥር የተወሰኑ ሲሆኑ፤ ማናቸውም መንፈሳዊ ክንዋኔ አምስቱን የእስልምና እምነት አምዶች ህገ-መሰረት ያደረጉ ናቸው። ከሌሎች እምነቶች ሲነጻጸርም እስልምና ያሉት ክብረበአላት ጥቂት የሚባሉ ሲሆኑ፤ የእምነቱ ተከታዮች በመንፈሳዊ ስርአት መሰረት እንደ ትእዛዝ ወይም ቃል የሚከተሏቸውና ቅዱስ አድርገው የሚያስቧቸው ቀናት ናቸው (Kaplan, 2015)።

የእስልምና እምነት ክብረበአላት በአጠቃላይ ሲጤኑ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በወል ተግባርነት የተለመዱ ለፈጣሪ ክብር፣ መውደድ ሲባሉ የሚከናወኑ፣ በእምነቱ ውስጥ በጉልህ የሚታወቁትን ነቢይ ለማሰብና ለእምነቱ ተከታዮች ያወረሱዋቸውን ታላላቅ መንፈሳዊ መሰረቶች ለማዘከር ሲባሉ የሚካሄዱ የአክብሮት መገለጫዎች ናቸው። በዚህ መሰረት ዋንኞቹ የእስልምና እምነት ክብረበአላትና በአላቱን ተከትለው የሚፈጸሙ ሁነቶች ታላቁን የእምነቱን አስተምህሮቶች ፈጣሪ ነቢዩ መሃመድን ለማስታወስ እና ነቢዩ የመሰረቷቸውን ልዩ የተባሉ ቀናት ለማሰብ ሲባል የሚከናወኑ ናቸው (Brill, 2008)።

በልማዳዊ መንገድ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሁሉ የሚያስቧቸው ሁለት ዋንኛ መንፈሳዊ ክብረበአላት ኢድ አል-ፊጥርና ኢድ አል-አድሃ አረፋ ሲሆኑ፤ ሙስሊም የሆኑ ሁሉ በፈቃደኝነት የሚገቡባቸው ለአንድ ወር ጊዜ ቀኑን ሙሉ የሚጾምባቸው ቀናት (a day voluntary fasting) ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ መካከል የመውሊድ ክብረበአል በአመት አንድ ጊዜ የነቢዩ መሃመድን ልደት ለማስታወስ ሲባል በእምነቱ ተከታዮች በጋራ የሚከበር በአል ነው። የእስልምና ተከታዮች ሁሉ የነቢዩ መሃመድ የልደት ቀንን በእስልምና የቀን አቆጣጠር (Rabi' al-Awwal) መሰረት በሦስተኛው ወር በ12ኛው ቀን ያከብራሉ። የጨረቃ የቀን አቆጣጠር (lunar calendar) በየአመቱ 11 ቀናት ወደፊት ስለሚቀድም የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀን በየአመቱ ይለዋወጣል (Reynolds, 2017)።

ይሁንና ሁሉም የእስልምና እምነት ተከታይ ሀገሮች መውሊድ ተብሎ የሚጠራውን የነቢዩ መሃመድ የልደት ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ አያከብሩትም። ለምሳሌ የሱፊ እስልምና አማኞች (Sufistrains of Islam) እንዲሁም እንደ ሳውዲ አረቢያ ያሉ ሀገሮች የእምነቱ ተከታዮች የልደት ቀኑን ሕዝባዊ ክብረበአል አድርገው ከመውሰድ ይልቅ እንደ አላስፈላጊ ሃይማኖታዊ ፈጠራ (religious innovation) ይቆጥሩታል። በአብዛኛዎቹ የእስልምና እምነት ተከታይ ሀገሮች የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀን የነቢዩን ክብር በሚያወድሱ የምስጋና መዝሙሮች (ዝየራዎች) እና ግጥሞች ታጅቦ ይከበራል። እነዚህ የምስጋና መዝሙሮችና ግጥሞች ነቢዩ መሀመድ ከፈጣሪ ዘንድ ለእምነቱ ተከታዮች ሁሉ የተቀበሉትን ይቅርታና ምህረት የሚያስታውሱና ጥልቅ መንፈሳዊ አክብሮትን የሚዋጁ ሲሆኑ የበአሉ አከባበር ልማድ በየሀገሮቹ ይለያያል (Reynolds, 2017)።

## 2.2 የመውሊድ ክብረበአል ምንነት

መውሊድ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚታወቅ ክብረበአል ሲሆን በአሉ የእምነቱ መስራች የሆኑትን የነቢዩ መሃመድ ልደት ለማስታወስ የሚከበር ነው። ከዚህ ክብረበአል ጋር በተያያዘ በመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በሰፊው የሚዘወተሩ ክንዋኔዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል የነቢዩ መሀመድን ታላቅነት የሚያወድሱ የምስጋና መዝሙሮች (መንዙማ) ዋንኞቹ ሲሆኑ እነዚህ መዝሙሮች ከአላህ (ፈጣሪ) ጋር የሚያገናኙ ክብሩን፣ ዘላለማዊነቱንና ለዚህ አለም ሃጢአት ሁሉ ይቅርታና ምህረት አድራጊነቱን የሚዋጁ ናቸው (Kaplan, 2015)።

ነቢዩ መሃመድ በፈጣሪ ዘንድ በጣም የተወደዱና ለተከታዮቻቸው የፈጣሪን መንገድ በአስተምህሮቶቻቸው ያመላከቱና የእስልምና እምነት ተከታዮች በፍጹም ልባቸው፣ ሕሊናዊና አካላዊ ንጽህናቸው ራሳቸውን ለፈጣሪ ህግጋት ማስገዛት እንዳለባቸው ያመላከቱ ነቢይ ናቸው። የነቢዩ መሀመድን የልደት ቀን - መውሊድ - መሰረት በማድረግ የሚቀርቡት መንዙማዎች ከዛሬ 700 አመት ገደማ ጀምሮ በእስልምና አማኞች ዘንድ የእምነቱ ትርክቶች የሚገለጽባቸው ሆነው ለነቢዩ ልደት ሞገስና ክብር ለመስጠት ይቀኛሉ (Brill, 2008)።

በምእራቡ አለም በሚገኙ ሀገሮች የእስልምና እምነት ተከታዮች በየአመቱ ለሚከበረው የመውሊድ ክብረበአል አጋር ናቸው። ነቢዩ መሀመድ የአላህ ብቸኛ መልእክተኛ መሆናቸውን በሕብረ-ዝማሬዎችና በግጥሞች በማቅረብ የልደት ቀኑን ያስባሉ፤ ያወድሳሉ። የእስልምና እምነት ተከታይ ኢሚሮች (የተለያዩ የሙስሊም መሪዎች ማእረግ ነው) እና ምሁራን መውሊድ በጥልቅ አእምሯዊና ስሜታዊ ግፊት የሚመሰጡበት መንፈሳዊ ሁነት ነው። መውሊድ በአለም ዙሪያ በሚገኙ የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የህዝብ ክብረበአል ሆኖ የሚከበር፤ ከሁለቱ ታላላቅ የእስልምና ሐይማኖታዊ ክብረበአላት (two Eids) ጎን በአማኞቹ መንፈሳዊ ስነልቡና ጉልህ ቦታ የሚሰጠው ሐይማኖታዊ በአል ነው(Reynolds, 2017)።

## 2.3 **የመውሊድ ክብረበአል አመጣጥና እድገት**

ስለ እስልምና እምነት ሰፊ እውቀትና ግንዛቤ ያላቸው ምሁራን ስለ መውሊድ ክብረበአል ታሪካዊ አመጣጥና እድገት ሲገልጹ፤ የነቢዩ መሀመድ የልደት ቀንን ለማስታወስ ሲባል በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው የመውሊድ ክብረበአል ከተወለዱበት የመጀመሪያ አመት ጀምሮ መከበር የጀመረ አይደለም። ነቢዩ መሀመድ ከተወለዱበት አመት ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ክፍለ ዘመናት መውሊድ አል-ነቢ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የክብረ በአልነት እሳቤ ሳያገኝ ቀይቷል። ይህ ማለት ግን ቅዱሱ ነቢይ ክብርና አስተምህሮዎቻቸውን የሚገልጹ መዝሙሮች እንዳይነሱ ክልከላ (ግዝት) አድርገው አልነበረም። በመካና አካባቢዋ በወቅቱ ተነስተው ከነበሩ እምነት የለሽ አረመኔዎች (kafirun) ጋር ተነስቶ በነበረው ውዝግብና ትግል መካውያኑ በወቅቱ የነበሩ ገጣሚያን በነቢዩ መሀመድ ታላቅነትና አስተምህሮ ላይ አሉታዊ  አስተሳሰብ ያላቸው ግጥሞች እንዲነዙ በማድረጋቸው ነው። በዚህ የተነሳ በልማዳዊ አስተሳሰብ በሚመራው የአረቡ አለም ዘንድ የቃላት ጦርነት መፈጠሩ በእስልምና ታሪክ የሚታወስ ሁነት ነው። በዚህ እምነታዊ ዳራ አለመጣጣም የተነሳ የተለያየ አንድምታ ያላቸው ግጥሞች (Qasidas) በነቢዩ መሀመድ ስም ሲደመጡ ቀይተዋል (Brill, 2008)።

ይሁንና መውሊድ ከግጥም መነባንብ የጠለቀ ትርጉም ያለው መሆኑ ግንዛቤ እያገኘ ሲመጣ በሙስሊም እምነት ተከታዮች ዘንድ በመንፈሳዊና ማህበራዊ ሁነቶች በመታጀብ የሚታሰብ ክብረበአል ሆነ። የነቢዩ መሀመድ የህይወት ታሪክ (Sirah)፣ አስተምህሮዎች በድጋሚ በመመርመርም በመካና መዲና ባሉ የሱፊ ምሁራንና መዘምራን አማካኝነት የዘመኑ ወጣት የሙስሊም እምነት ተከታዮችና የሙስሊም ማህበረሰቦች የመውሊድን እውነታ እንዲያውቁት ተደረገ። በዚህም የተነሳ አብዛኛዎቹ ግጥሞችና የቅዱሳን ታሪክ መጽሐፎች በእስልምና እምነት ታሪክ ውስጥ ምእተአመታት የቅዱሱ ነቢይ ህይወትና ዘመን መንፈሳዊ እውነታዎች እድገት ያገኙት በግለሰብ የእስልምና እምነት ተከታዮች ብርቱ ጥረት ነበር ለማለት ይቻላል (Brill, 2008)።

### 2.4 መውሊድ ለምን ይከበራል?

ምንም አክራሪ ወይም ጽንፈኛ አስተሳሰብ አራማጅ በሆኑ አንዳንድ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በሃይል ጭምር በመጠቀም ከመውሊድ ክብረበአል እሳቤ በተቃራኒ ቢቆሙም፤ መውሊድ አል-ነቢ የነቢዩ መሃመድ ልደትን የሚዘክር ትልቅ የእስልምና እምነት ተከታዮች ክብረበአለ በመሆን ይታወቃል። በተለያዩ እስልምና አማኝ የአለም ማህበረሰቦች ዘንድ በተለያዩ አውዶችና ክዋኔዎች በድምቀት ይከበራል (Kaplan, 2015)።

የመውሊድ ክብረበአል የእስልምና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ለነቢዩ መሃመድ ያለው አክብሮትና ፍቅር የጥንካሬ መገለጫ ነው። በእስልምና ሀይማኖት ልማድ መሰረት እንስሳት፣ ዛፎች እንዲሁም ግኡዛን ነገሮች ሳይቀሩ ለነቢዩ ያላቸውን ፍቅር አሳይተዋል፤ ነቢዩም ለእነዚህ ሰው ያልሆኑ ነገሮች ሁሉ ፍቅር አላቸው የሚል ትርክት አለ። በመሆኑም ለእኚህ ነቢይ የእስልምና እምነት ተከታዮች ያላቸው ፍቅርና ይህንኑ የሚገልጹበት መንገድ የመንፈሳዊ ጽድቅ መሻት ማሳያ እንደሆነ በሰፊው ይታመናል (Reynolds, 2017)።

ለነቢዩ መሃመድ ፍቅር መሰጠት በጣም አስፈላጊ የእምነቱ ተከታዮች ልምድ ነው። ሙስሊሞች ሁሉ ነቢዩ የተለየ ችሎታ ያላቸውና በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ተምሳሌት የሆኑ የፍቅርና የምህረት፣ የርህራሄና የበጎ አድራጎት፣ የደግነትና የፍትህ ሞዴል ናቸው። የበላይ የበታቹን እንዲያከብር፣ የበታች ለበላዩ እንዲታዘዝ፣ ወንድም ለወንድሙ እንዲያዝን፣ አንዱ ሌላውን እንዳያጠቃ በአስተምህሮዎቻቸው እና በድርጊቶቻቸው ሁሉ አሳይተዋል። በቅዱስ ቁርአን እንዲህ ተጽፏል። ‹‹እኛ እንዲሁ አልላክንህም፤ ይልቅ ለአለማቱ ሁሉ ምህረትን ታወርድ ዘንድ እንጂ›› {We have not sent you but as a mercy to the worlds} [Quran 21:107](Brill, 2008)።

በዚህ የተነሳ የነቢዩ መህመድን ልደት ማክበር ለእስልምና እምነት ተከታዮች ሁሉ የጽኑ ፍቅራቸው መገለጫና ራሳቸውን ከህይወት (ጽድቅ) ጋር የሚያስተሳስሩበት፣ በነቢዩ የህይወት ዘመን አስተምህሮዎችና ባህርያት ለመታነጽ ያላቸውን ጠንካራ ፍላጎት የሚገልጹበት መንገድ ነው።

### 2.5 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ በመሆን የሚያገለግሉትን ክብረ በዓልን፣ ክዋኔንና አውድን በማስመልከት በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ንድፈ ሃሳባዊ ትወራዎች ላይ ቅኝት የተደረገበት ክፍል ነው። በመሆኑም በዚህ ክፍል ንድፈ ሀሳቦቹን የተመለከቱና በመስኩ ምሁራን የተጻፉ ልዩ ልዩ ጽሁፎች ቀርበዋል።

## 2.5.1 ክብረ በዓል

ምሁራን ክብረ በዓልን አስመልክቶ ተመሳሳይ እንድምታ ያለው የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተዋል።Sims እና Stephens (2005: 95) እንደገለጹት፤ "በማህበረሰቡ ዘንድ ተደጋጋሚ ሆኖ የሚከበር፣ ድርጊቶች /ሁነቶች/የሚሰተዋሉበትና ዘወትር ከምናከናውናቸው ልማዶች የተለየ አላማ ያለው ነው።" በማለት ይገልጹና፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ያለውን ቦታ ሲያስረዱ፤"ክብረ በዓል አንድ ነጠላ ባህል ዐይነት ሆኖ ፎክሎረኞች ሲያጠኑ ግን የተለያየ ምድብ ውስጥ ያስገቡታል" ይላሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Rappaport (1992) አገላለጽ፤ "ክብረ በዓል ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች አንዱ ሲሆን ለሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገልጹት) ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ ግልጽ የሆነ ቅርጽ ያለው፤ የተለያዩ ገጽታዎችንና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑ በላይ እነዚህ ባህሪያቱ አነሰም በዛም እርስ በእርስ የተያያዙ ናቸውይላሉ።

ከዚህም በተጨማሪ፤ እያንዳንዱ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ በዝግጅት እና በጉጉት የሚጠብቃቸው ክብረ በዓላት አሉት። እነዚህ ክብረ በዓላት ደግሞ ወቅታዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ በሚል የሚታውቁ ናቸው። Sims እና Stephenes (2005 ፣102 –125)፤ ክብረ በዓላት ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውና ከሀይማኖታዊ ይዘት ውጭ መኖራቸውን በመግለጽክብረበዓላት ሁለቱንም የሚይዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ። ይህ ምን ማለት ነው? ሃይማታዊ የሆኑት በዓላት እንደየሰው እምነቱ በተለያየ መንገድ ለሚያመልከው አምላኩ ምስጋና የሚያቀርብበት ክብረበዓላዊ ስርዓትን የሚመለከት ሲሆን፤ ከሀይማታዊ ስርዓት ውጭ ያለውን ማህበራዊውን የወሰድን እንደሆነ ለምሳሌ፡- ብሄራዊ ቀናት፣ ልደት፤ ክርስትና እና ሰርጉን እንመለከታለን።

በዚህ መልኩ ሃይማኖታዊ ክብረበአላት በሃይማኖቱ አምዶች ላይ ተመስርቶ በምክንያት ተደግፎ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በወል የሚታሰብ፣ የሚከበር፣ የሚዘከር፣ በአውድና በክዋኔ የታጀቡ ሁነቶች የሚተገበሩበት የመንፈሳዊ እምነት መገለጫ ሲሆኑ፤ ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ክብረበአላት ከመንፈሳዊ አውድ ይልቅ በጋራ ስሜት ወይም በሰዎች የግል ትውስቶች ላይ የቆሙ ናቸው። በመሆኑም ሃይማኖታዊ ክብረበአላት ሃይማኖታዊ ካልሆኑ ክብረበአላት ይልቅ ለፎክሎር ጥናት ቅርብ ናቸው።

እነዚህ የህይወት ምዕራፍ መክፈቻዎች ሁለቱንም (sacred እና secular) የሚይዙ ክብረ በዓላት መሆናቸው ግልጽ ነው።በተመሳሳይ መልኩ አብዛኞቹ ክብረ በዓላት ሲከበሩ በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በአንድ አጠቃለው ይዘው ይመጣሉ። ለምሳሌ የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የመውሊድ ስርዓት ከበራን ስንመለከት ስርዓተ ከበራውን ለማጥናት ሲባል በሂደቱ ወቅት ተያይዘው የሚመጡትን ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎች፣ቃላዊ ግጥም (መንዙማ) በመንዙማው ክዋኔ ወቅት የሚታዩትንና ተያይዘው የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን መዳሰስ ይመለከታል ማለት ነው።ይህንንም በተመለከተ Sims እና Stephens (2005 ፣ 95) "rituals are repeated habitual actioins, highly organized and controlled …. bring together many types

of folklore.” በማለት ክብረ በአላት በአንድ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ የሚከናወኑ ድርጊቶችና ሁነቶች የሚገለጹበት፣ የማህበረሰቡን ልማዶች የሚያሳዩ በርካታ የፎክሎር ዓይነቶች የሚከወኑባቸው መቼቶችና ግብሮች መሆናቸውንይገልጻሉ።

በመጨረሻም ክብረ በዓላት ሲባሉ ውቅታዊ፣ ማህበራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ በዓላት ሆነው የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ በጉጉትና በዝግጅት የሚጠብቃቸውና በጊዜው የሚያከብራቸው ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለማድረግ የሚሞክር ፎክሎረኛ የክብረ በዓሉን አጠቃላይ ይዘት መግለጽ ላይ ብቻ መወሰን የለበትም።ነገር ግን ዐውድን መነሻ በማድረግ ክብረ በዓላትን በሚያጠናበት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት Finnegal (1992፣ 86) ትመክራለች።አጥኚው በዙሪያው ያሉ ቁሳቁሶች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች፣ ምልክቶች እርስ በእራስ በምን ግንኙነት አላቸው? በትርጉም ላይ የሚያመጡት ነገር አለ? በሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ መመስረት እንዳለበት ትገልጻለች።

ክብረበዓላትን በርካታ ምሁራን በተለያየ ቦታ በመክፈል ተመልክተዋል። የክብረ በዓል አይነቶችን በስፋት እና በጥልቀት ከብዙ ምሳሌዎች ጋር ያቀረበችውን Bell (1997፣ 93-94)ን ተመራጭ አድርጌ በጥናቴ አካትታለሁ። በBell (1997) መጽሃፍ ክብረበዓል በስድስት ቦታ ተከፍለው ቀርበዋል። ከስድስቱ የክብረ በዓላት አይነቶች ደግሞ የኔ ጥናት የሚያተኩረው ‹‹ዓመታዊ ና የመታሰቢያ ከበራ›› በሚለው ላይ ነው። የእኔም ጥናት ተመሳሳይ መንፈስ ያለው በመሆኑ እኔም ለጥናቴ የተጠቀምኩት ይህንኑ ነው።Bell (1997፣ 239) ይህንን ከበራ በተመለከተ “calanderical rites give socially meaningful definition to the passage of time, creating an ever renening cycle of days, months and years ……” በማለት ትገልጻለች።እነዚህ ከበራዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚከበሩ ስለሆኑ ከተቀረጠላቸው ቀን ወይም ወር ላይ የማያልፉ ናቸው። ይህም ማለት ክብረበአላት በየአመቱ በተወሰነ አንድ ቀን ወይም ቀናት ውስጥ በድርጊቶችና ሁነቶች ሰንሰለቶች ታጅበው የሚታሰቡ፣ የሚከበሩና የሚዘከሩ ናቸው።
የመከበሪያ ጊዜያቸውን ከክብረበአሉ ከየት መጣነት በመነሳት የሚወስኑትም የበዓሉን መኖር የሚያምኑበትና የሚያከብሩት የማህበረሰቡ አባላት ናቸው በማለት Bell (1997)ትገልጻለች።

### 2.5.2. ክዋኔ

Green (1997፣630) የክዋኔንብያኔ በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሮ ይገኛል።ክዋኔ በፎክሎር ውስጥ ማንኛውም ከዋኝ በታዳሚው ፊት ሲቀርብ ጥበባዊነቱን እና ኪናዊነቱን በጠበቀ መልኩ የሚያቀርበው ድርጊት ነው።በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ስንመለከተው ደግሞ የክዋኔ ጽንሰ ሃሳብ የሚገነባው ነገሮች ላይ ተመስርተን ለነገሮች በምንሰጠው ፍች እና ትሩጓሜ አንጻር ነው። ይህ የሚያሳየው በሚተገበረው ነገርና ተግባሪው ችሎታ ፣ የሚገለጸውን ካለን እውቀት፣ ከበራን ከእምነት፣ የሚታዩ ተጨባጭ ባህሪ ካለው ሁኔታ ጋር ማጣጣምና በተለይ በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በዳንስ ወይም በጭፈራና ድራማ የሚቀርበውን ኪናዊ እይታ ይመለከታል። በፎክሎር ጥናት

ክዋኔ በሚቀርበውና በተሰነደው መካከል ያለውን ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይታሰባል ሲል Green (1997) ገልጾታል።

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ክዋኔ ማህበራዊ መሰረት ያለውና በድርጊት የሚገለጽነው። ማንኛውም ከዋኝ በታዳሚው ፊት ሲቀርብ ጥበባዊነቱንና ኪናዊነቱን በጠበቀ መልኩ የሚቀርብ ድርጊት ሲሆን በተጨማሪ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ጥበባዊ የሚሆነው ሲከወን መሆኑን ያስረዳናል።

ይህንኑ ጽንሰሀሳብ በተለከተ Bauman (1976፣ 4-5) “ክዋኔ ውበታዊ ተግባር ነው፤ የፎክሎር አፈጻጸም ነው፤ በፎክሎር ውስጥ ያለ ውበታዊ ክስተት መገለጫ ነው። ክዋኔ በከዋኝ፣ የአከዋወን ስርዓትን የግድ የሚል፣ ታዳሚንና መቼትን የሚያቀራኝና በአንድ ላይ የክዋኔ አቀራረብን እድገት ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ አጣምሮ የሚይዝ ነው።” በማለት አስቀምጦታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የክዋኔና የክብረ በዓል ትስስር በተመለከተ Rappaport (1992፣ 250) የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሮ ይገኛል።

‹‹…. There is no performance, there is no ritual performance is self an aspect of that which is performed. The medium is a part of the message. More precisely, it is a meta message about what ever is encoded in the ritual. ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ክብረ በዓል ያለ ክዋኔ ብቻውን ህልውና እንደሌለው (መኖር እንደማይችል) እና በከበራው ወቅት የሚደረግ ማንኛውም ድርጊት ክዋኔ መሆኑን ነዉ።ክዋኔና ክብረ በዓል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ይህም ማለት ክብረበአል ባለበት ሁነት አለ፤ ሁነት ደግሞ ሊገለጽ የሚችለው ሰዎች በግልና በጋራ በሚያከናውኗቸው በአላማና ገቢር ላይ የተመሰረቱ ክዋኔዎች ነው። በዚህ ምክንያት ክብረበአላት የክዋኔ አምዶች ሲሆኑ ክዋኔዎች በበኩላቸው ለክብረበአሉ ሁነኛ ጉላትና ድምቀት ያቀዳጁታል ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ይህንኑ ጉዳይ በተመሳሳይ መልኩ Sims እና Stephens(2005፣ 94-126) ከምሳሌ ጋር በማዋዛት አቅርበዋል። ስለዚህ የሞሊድን ክብረ በዓል አጠቃላይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ምን ምን እንደሚደረግ ሂደቱን ስንገልጽ በሌላ መልኩ ክዋኔውን ተናገርን ለማለት ይቻላል።

በመጨረሻም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ክዋኔ እንደ ባህሉ አይነትና ይዘት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል። በመሆኑም ክዋኔ የሚቀርብበትና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖረው እንደማይችል (Finnegal 1977, Rappaport 1999) ያስረዳሉ። ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ክዋኔ ምንም እንኳ እንደየባህሉ አይነትና ይዘት የተለያየ አቀራረብ ቢኖረውም፤በምንም አይነት መልኩ ያለክዋኔ ትውፊታዊነቱን መግለጽ እንደማይቻልና ክዋኔ ዋነኛው ፍሬ ነገርና አይቀሬው ክስተት መሆኑን ነው።

### 2.5.3 አውድ

በርካታ ምሁራን ስለ አውድ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። ከዚህ መሀከል ሰለሞን (2007፣47)፤ አንድ ሎር በክወና በሚቀርብበት ወቅት ያለውን ባህሪያት የሚገልጽ ነው በማለት ሲገልጽ፤ Dundes (1994፣86) አውድን፤ አንድ ድርጊት የሚከወንበታ ጊዜ እና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ ይገልጻል። በዚህ መሰረት አውድ የሁነት ወይም ክዋኔ መከሰቻ መቼት ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ Abrehames (1972፣45) “context is sem in such phress as seremonial communicative interaction of small groups`` “communicative event“ በማለት ገልጾታል። Sims እና Stephens (2005፣ 37) ደግሞ “context rsferes to anything and every thing that surrounds a text and performance” በማለት ይገልጹታል። አውድን አስመልክቶ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ ሀሳቦች የአገላለጽ ለውጥ እንጂ ተመሳሳይ ትርጓሜ ያላቸውን ሃሳቦች ሰጥተውበታል። ይህም ማለት አውድ ማንኛውም ፎክሎራዊ ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም አጠቃላይ የድርጊት ድባብ ነው ማለት ይቻላል።

አውድን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን በገለጹበት መንገድ ለመበየን ቢሞከርም ገዢ ሀሳብ ተደርጎ የሚቀጠረው ግን Bauman (1983፣ 36-37) ባቀረበው ጽሁፍ ውስጥ የተሰጠው ገለጻ ነው። በዚህ ጽሁፍ ቦውማን እንደሚያስረዳው አንድ የፎክሎር ክዋኔ ቢያንስ ሁለት አውዶች ይኖሩታል ይላል።እነዚህም ባህላዊና ማህበራዊ መሆናቸውን ይገልጻል።

የእኔም ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሰረተው በዚሁ ቦውማን ባስቀመጣቸው ማህበራዊ አውድ (social context) እና ባህላዊ አውድ (cultural context) ነው። ባህላዊ አውድን ሲያስቀምጥ ባህላዊ አውድ ማህበረሰቡ ባለው ባህል መሰረት ለአንድ ቴክስት፣ድርጊት ወይም ሁኔታ የሚሰጠው አውዳዊ ፍቺ ነው በማለት ይገልጽና፤ ማህበራዊ አውድ ደግሞ ከቤተሰብ አባላት ባልና ሚስት፣ ልጆች፣እስከ ቡድናዊ፣ ሀይማኖታዊ ቡድኖች ፣ አካባቢያዊና የመሳሰሉትን ተግባቦት የሚያጠቃልል ነው በማለት አስቀምጧል።

### 2.6 የጥናቱ ስልተ-ትወራ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የቁባ አባአረቡ የመውሊድ በዓል ስርዓት ክንዋኔ ሂደት ትንታኔ መስጠት እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጫለሁ። አላማዬን ከግብ አደርስ ዘንድ ስለ ክብረ በአላት ምንነት እና ባህሪ የሚያስረዱ የተለያዩ ተመራማሪዎችን ስራዎች በግብአትነት ተጠቅሚያለሁ።

ይህን ጥናት ለማካሔድ የምጠቀመው ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ አውዳዊ አቀራረብን (Contextual Approach) ወይም ክዋኔ-ተኮር አቀራረብ (Performance Centered Approach) ነው። ምክንያቱም የቁባ አባአረቡን የመውሊድ በዓል ክዋኔን በተፈጠረበት፣ ባደገበትና አገልግሎት በሚሰጥበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ተንትኖ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ ነው። ይህንንም በተመለከተ Ben-Amos (1974፣ 209) ቴክስትን ከአውድ ነጣጥሎ መመልከት አስቸጋሪ እንደሆነ ሲያስረዳ፤ "The meaning of a text

is its meaning in context… In terms of contextual analysis there is no dichotomy between text and context›› በማለት ይገልጻል። በዚህም መሰረት ቴክስትን ከአውድ ነጥሎ መመልከቱ እምብዛም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም። ይህም ማለት በመውሊዱ በዓል ላይ የሚደረጉ ስርዓቶችንም ሆነ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞች እንዲሁ ብናቀርባቸው የተሟላ ስሜት ላይሰጡ ይችላል። ነገር ግን በተከወኑበት አውድ ውስጥ እያስገባን ስንመለከታቸው እንዲሁ ከቀረቡት የበለጠ ነፍስ የሚዘሩ ይሆናል።

ስለዚህ የቁባ አባ አረቡንም የመውሊድ በዓል መንፈሳዊ ስርዓቶች ከሚከወኑበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንጻር መተንተን እና ትርጓሜ ላይ መድረስ ያስፈልጋል ማለት ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ክዋኔ ተኮር አቀራረብ የሚፈልጋቸውን ስነ-ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል። ይህንንም በማስመልከት Bauman (1983) በበኩሉ፤ አንድ ጉዳይ በዚህ አቀራረብ ሲጠና ጉዳዩ እንዴት እና የት ተከወነ? ቅንጅቱ እንዴት ነው? እነ ማን ነበሩ? ስርአቱ ምን ይመስላል? ተደራሲው እንዴት ምላሽ ይሰጣል? የሚሉ ጉዳዮችን አጽእኖት ሰጥቶ ማጥናት አለበት ይላል። ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖረውም እንደማይችል (Finnegan 1977,Rappaport 1999) ያስረዳሉ። የአራቱም ምሁራን ንድፈ ሐሳባዊ ጥቆማዎችና በምእራፍ ሁለት የተካተቱት ሌሎች ሀሳቦች ጥናቱምን ላይ ማተኮር እንዳለበት አመላክተዋል። ለአብነት ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ ብንመለከት ጥናቱ በመውሊድ ስርአቱ ላይ ብቻ ሳይወሰን በስርአቱ አማካይነት የታዳሚውን እሴት አመለካከት እና እምነት ምንእንደሚመስል ለማሳየት እንዲሞከር ሆኗል። እኔም ከዚህ ነጥብ በመነሳት በጥናቱ ወቅት የሚከተሉትን መሰረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች በጥያቄ መልክ በማንሳት ጥናቴን አካሂጃለሁ።

- ✓ ተተኳሪው ክብረ በዓል ለምን ይከበራል?
- ✓ ታሪካዊ አጀማመሩ ምን ይመስላል?
- ✓ መቼ፣ እንዴትና በምን አይነት አውድ ያከብሩታል?
- ✓ የከበራው አጠቃላይ መዋቅር ምን ይመስላል?
- ✓ በክብረ በዓሉ ላይ የሚስተዋል የተለየ ቁሳቁስ፣ምግብ… አለ? ለምን?
- ✓ የመከበሩ አጠቃላይ ማህበራዊ ፋይዳውስ ምንድን ነው?
- ✓ በከበራው ላይ የሚከሰቱት ዋና ዋና ሁነቶች ምን ምን ናቸው?

የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በጅማ ከተማና አካባቢው እስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረውን የቁባ አባ አረቡን የመውሊድ በዓልን አጥንቻለሁ። በዚህም በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ማክበሪያ ስፍራ የነበረው ገጽታ እና አጠቃላይ ሁነቶች ከላይ የተጠቀሱትን የትኩረት አቅጣጫዎችና የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ተዳሰና ተተንትኖ ቀርቧል።

## 2.7 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ተዛማጅ ጥናት ቅኝት በማደርግበት ወቅት የተገኙት ቀደምት ጥናቶች በመጀመሪያ ና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተሰሩ ናቸው።እነዚህም የተመረጡት ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨረስቲ በቋንቋዎች ጥናት ትምህርት ክፍልና በታሪክ ትምህረት ክፍል የተሰሩ ጥናቶች ናቸው።ከነዚህም ጥናቶች ሁለቱ በኤም.ኤ ዲግሪ የተሰሩ ሲሆኑ አንዱ ደግሞ ለቢ. ኤ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ነው።እነዚህ ከተገኙት ጥናቶች ለተዛማጅ ጥናት ቅኝትነት የተመረጡበት ምክንያት ከዚህ ጥናት ጋር በቀታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያመሳስላቸው ባህሪ እንዳለ በመታመኑ ነው።በዚህ ቅኝት በቀጥታ ዑለማ መውሊድን መሰረት አድርጎ የተሰራ አንድ ጥናት እንዳለ ሆኖ ሌላው ጥናት ደግሞ በቀጥታም ባይሆን ከጥናቱ ጋር የሚያገናኘው ነጥብ በመኖሩ ሁለቱም ቅኝት ተደርጎባቸው ቀርበዋል።

በኤም.ኤ ደረጃ ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች መካከል በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሁለት ጥናቶች ተቃኝተዋል።እነዚህም የአብዱራህማን (2007ዓ.ም) ‘‘የሐጅ ሁሴን(የእነሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች(መንዙማዎች)ክዋኔ ጥናት”፣የሰዩም (2007) “An Archaeolgical Survey of Islamic Shrines in Jimma Zone South Western Ethlopia” የሚሉት ናቸው።

ከእነዚህ ሁለት ጥናቶች የመጀመሪያው የአብዱራህማን (2007) የኡለማ መውሊድ ስርዐተ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞቹን አውድ ላይ መሰረት በማድረግ ተተንትኖ የቀረበ ሲሆን፤ የሁለተኛው የሰዩም ጥናት ደግሞ በደቡብ ምዕራብ ኢትዩጵያ በጅማ ዞን የሚገኙ ኢስላማዊ የቅድስና ስፍራ የሆኑትን ቦታዎች ታሪክ በማጥናት ከታሪካዊው ስፍራ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ነጥቦች ተተንትነው ቀርበዋል።እነዚህ ሁለት ጥናቶች ኡለማ መውሊድንና የቅድስና ስፍራውን መሰረት በማድረግ የተጠኑ ናቸው።

የአብዱራህማን (2007 ዓ.ም) ጥናት የሼህ ሁሴን አለሙን መውሊድ ክብረበአልእና በመውሊዱ ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞች(መንዙማዎች) ክዋኔ ላይ መሰረት ያደረገ ጥናት ነው።አብዱራህማን በጥናቱ ሁለት ዋና የምርምር ጥያቄዎች አንስቷል። የሼህ ሁሴን(የሼህ ዳንግላ)የመውለድ ስርዓተ ክዋኔ ምን ይመስላል? እና በመውለድ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ከሀይማኖታዊ ገጽታቸው ባሻገር ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች በጥናቱ “የመውለድ በዓል የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ሁነቶች ድምር ውጤት መሆኑን” መልስ አግኝቷል።አብዱራህማን መረጃዎቹን ለመሰብሰብ እና ጥናቱን ለማከናወን የተጠቀመው ዘዴ ቃለመጠይቅ፣ምልከታና የተተኳሪ ቡድን ውይይት የተጠቀመ ሲሆን፤በዚህ መንገድ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገላጭ ስልትን በመጠቀም ክዋኔ ተኮር አቀራረብን ተከትሎ መረጃዎቹን ተንትኗል።

የአብዱራህማን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በንድፈ ሀሳብ ምርጫው፣መረጃውን ለማግኘት የተጠቀመው ስነ-ዘዴና ለመተንተን የተጠቀመው ስልት ሲሆን የሚለያየው ደግሞ የሱ ጥናትበኡለማ መውሊዱላይ የተከወኑት ቃላዊ ግጥሞች(መንዙማዎች)ክዋኔያቸው ምን ይመስላል? በሚል ማጠንጠኛ ነጥብ የተጠና ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞኡለማ መውሊድአጠቃላይ ስርአተ ከበራ ሂደቱን(ከዚያራ እስከ ፍጻሜው)ያለውን መተንተን በመሆኑ

ይለያል።ከዚህ በተጨማሪም የኔ ጥናት በስረአተ ከበረው ወቅት ለማጀብ የሚገቡትን ቁሳዊ ባህሎቹንም ሆነ ቃላዊ ግጥሞቹን በመዘርዘር የቀረቡበትን አውድ መሰረት በማድረግ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳቸውን ተንትኖ በማሳየት ላይ የሚጠና በመሆኑ ይለያል።

የስዩም (2007) ጥናት ዋና አላማ በደቡብ ምዕራብ በጅማ ዞን ኢስላማዊ የቅድስና ስፈራ የሆኑትን ቦታዎች ለይቶ መተንተንና ዶክመንት ማድረግ በሚል የተጠና ነው።በጥናቱ የመጀመሪያ ክፍል የጥናቱን አካባቢ እና ጂኦግራፊያዊ አቀጣጫውን እንዲሁም አካባቢያዊ አቀማመጡን በካርታ አስደግፎ በግልጽ አሳይቷል።የቅድስና ስፍራ የሆኑትን የቁባ አባ አረቡንም ሆነ የሙፍቲ ሳዲቅዮን ቅድስና ስፍራ፣ ታሪካዊ አመጣጡንና በቦታው የሚከበሩትን በዓላት በመዘርዘር በጥናቱ አሳይቷል።

ስዩም ይህን መረጃ ለመሰብሰብ ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን መረጃውን ለመተንተን ደገሞ ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም አይነታዊና መጠናዊ የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅሟል።የስዩም ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ለጥናት በተመረጠው ስፍራ፣የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውና በመተንተኛ ዘዴው ሲሆን የሱ ጥናት ታሪካዊ ስፍራውን ለማሳወቅ (መለየት)፣በዚህ ቅድስና ስፍራ እነማን ነበሩ? ምን ይከናወን ነበር? ከዋኞቹ እነማን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የተጠና ሲሆን የኔ ጥናት በዚህ በተቀደሰ ስፍራ የኡለማ መውለድ በአልን ስረአተ ከበራ ሂደቱን አውድን መሰረት በማድረግ የሚጠና በመሆኑ ይለያል።

በአጠቃላይ ከተመለከትኳው ሁለት ጥናቶች ውስጥ አንዱ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የተሰራ ሲሆን ሌላኛው በታሪክ ትምህርት ክፍል የተሰራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።ሁለቱ ጥናቶች ከተጠኑበት ኣላማ ኣንጻር የጎላ ልዩነት አላቸው። ይኸውም በቋንቋ ትምህርት ክፍል በተሰራው ጥናት በአጠናን ዘዴው፣ ስነ-ዘዴውና ንድፈሀሳቦችን ከጥናቱ ጋር የሚያዋቅርበት መንገድ እና ጥናቱ ፎክሎራዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያደርጋቸው ጥረቶች የአጥኚውን ጠንካራ ጎን አጉልቶ አሳይቶኛል። ከዚህ በተጨማሪም ነገሮችን በጥልቀት መመርመርን ተምሬበታለሁ። በዚህ ጥናት ክፍተት ነው የምለው በጥናቱ ያልተካተተውንከዚያራ እስከ ፍጻሜውበሂደቱ አገልግሎት ላይ የሚውሉትንቁሳዊ ባህል የሚገልጹ - ማለትም ክብረ በዓሉን አጅበው የገቡትን ቁሶች - አካቶ አካትቶ በማጥናት በቀደመውጥናትጥናት የነበረውክፍተት መሞላት አለበት። ሌላው በዚህ ክፍል የተቃኘው ጥናት በታሪክ ትምህርት ክፍል የተሰራው ጥናት ነው።ጥናቱ ከትምህርት ክፍሉ አላማ አንጻር የተጠና በመሆኑ በጥናቱ የተመለሱት ጥያቄዎች ከቦታው ታሪካዊነት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ናቸው።ጥናቱ ፎክሎራዊ ጥያቄዎችን በጥናቱ አላካተተም።በመሆኑም በዚህ ጥናት የታየውን ክፍተት የኔ ጥናት ይሞላል ተብሎ የተጠና ነው።

በአጠቃለይ ከላይ የጠቀስኩት ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፍ የቁጥር(የመጠን) ማነስ የተነሳ በመስኩ ብዙ መሰራት እንዳለበት /ክፍተቶች/ እንዳሉ ለመረዳት ያስችላል።እኔም ከዚህ በመነሳት የቁባ አባ አረቡ የመውለድ በአልን(ኡለማ መውሊድን) መሰረት በማድረግ የስርአተ-ከበራውን ሂደት ከቦታው አንጻር በክዋኔ ቋንቋው በማጥናት ተርጉሜ አቅርቤያለሁ።

# ምዕራፍሶስት
# የጥናቱ ስልትና አካሄድ

ይህ ምእራፍ ጥናቱየተካሄደበትአካባቢአጠቃላይገጽታ፣ የምርምር ስልትን፣ የምርምሩን ዓይነት፣ አካሄድና የንሞና ዘዴን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን እና የጥናቱ የትንተና ዘዴ የተቃኙበት ነዉ።

## 3.1 **ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ**

ጅማ ጥንታዊ ከሆኑ የኢትዮጵያ ከተሞች አንዷ ናት። ጅማ በንጉስ አባጅፋር 1ኛው ዘመነ መንግስት በ1821 ዓ.ም አካባቢ ተመሰረች[1] ። ጅማ ከተማ በውስጧ 17 ቀበሌዎን የያዘች ሲሆን ፤ጥናቱ ከእነዚህ ከአስራሰባቱ ቀበሌዎች ውስጥ አንዱ በሆነው ጅሬን[2] ቀበሌ ውስጥ የተካሄደ ነው። ጅማ ከተማ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 352 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ከተማዋ በ$7^{0}$ $4^{N}$ ላትቲዩድና በ$36^{0}$ $5^{E}$ ሎንግ ትዩድ ከባህር ጠለል በላይ ከ1725-1789 ሜ መሀከል ባለው ከፍታ ላይ ትገኛለች። ከከተማው ካሉት ቦታዎች ከፍተኛ የሚባለው ጅሬን ሲሆን ፤ከፍታውም 1789 ሜ ነው።በዝቅተኛ ቦታነቱ የሚታወቀው ትልቁ ስታዲየም አካባቢ ያለው ቦታ ሲሆን ዝቅተኛነቱ 1725ሜ አካባቢ ነው። የከተማዋ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ተራራማ ና ሜዳማ ሲሆን በተፈጥሮ ለምለምና በደን የተሸፈነ ነው። ከተማዋን አቋርጠው ያልፉት ሁለት ትላልቅ ወንዞች ለከተማዋ ውበት አላብሰዋታል። የጅማ ከተማ የቆዳ ስፋት 102.0 ኪ.$ሜ^{2}$ በሄክታር ያላት ሲሆን የአየር ንብረቷ ወይናደጋ የሆነና በአማካኝ $19^{0}$.4c የሙቀት መጠን እና 1566.5 ሚ.ሜ የዝናብ መጠን አላት።ከተማዋን የሚያዋስኑ ዙሪያ ወረዳዎች በሰሜን ማና፣ በደቡብ ዴዶ፣ በምስራቅ ሰርቦ በምዕራብ ከሰቃ ጨቀርሳ ጋር ትዋሰናለች(ከከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት በ2004ዓ.ም በእንግሊዘኛ ከተጠና ጽሁፍ የተወሰደ።) በ2007 ዓ.ም የከተማው አስተዳደር ባለው መረጃ መሰረት በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ 17 ቀበሌዎች ከሚገኘው የህዝብ ብዛት 91.88 ወንድ 90.970 ሴት ሲሆኑ በድምሩ 182.818 ነው።በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ሲሆኑ፡- ኦሮሞ፣ አማራ ፣ ትግሬ ፣ ጉራጌ ፣ስልጤ ፣የም ፣ዳውሮ እና ሌሎችም የሚኖሩባት ሲሆን በከተማዋ በስፋት የኦሮመኛ እና የአማረኛ ቋንቋ ይነገራል፤ነገር ግን የከተማ አስተዳደሩ የስራ ቋንቋ ኦሮመኛ (አፋን ኦሮሞ)ነው።በከተማዋ

[1]ከከተማው አስተዳደር ጽ/ቤትበ2004 ዓ.ም በእንጊሊዘኛ ከተጠና ጽሁፍ የተወሰደ።

[2].ጅሬን(JIREEN) የሚለው ቃል በጅማ ውስጥ የሚታወቀው በሁለት አይነት ነው። የመጀመሪያው አባጂፋር በዚህ አካባቢ መኖራቸውና ለረጅም አመት የንጉሱ መአከላዊ ከተማ በመሆኗ ሲሆን፤ሁለተኛው የጅማ ከተማ የመጀመሪያው የምስረታ ቦታ መሆኑ እንደ ሆነ በ2009 ዓ.ም የጅማ ባህልና ቱሪዝም ቱሪዝም ጽ/ቤት ባዘጋጀው መጽሄት ተገልጾዋል።

ውስጥየሚገኙትን ዕምነቶች ስብጥር ስንመለከት ሙስሊም፣ኦርቶዶክስ እና ፕሮስታንት ሲሆኑ፤በከተማዋ የእስልምና እምነት ሰፊውን ቦታ ይይዛል።ይህ ሊሆን የቻለበትም ምክንያትከአቶ ዊዳድ አ/ፊጣ ጋር በቀን 05/08/11 በተደረገ ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት" ክልሉ በገዳ ስርዓት መተዳደር አቁሞ በንግስና ስርዓት መተዳደር በጀመረበት ጊዜ የእስልምና እምነት መቀበሉን" ይገለጻሉ።በዚህ እና የከተማዋ የመጀመሪያው መሪ ሙስሊም መሆናቸውና የሳቸው የዘር ሀረግ ያላቸው የዚህ እምነት ተከታይ መሆናቸው ይሆናል።የማህበረሰቡን ባህል በተመለከተ የጅማ ኦሮሞ እንደ ማንኛውም አካባቢ ኦሮሞ ማህበረሰብ ባህልጋር የሚመሳሰል ሲሆን አምስቱ (5) የጊቤ መንግስታት ከመፈጠራቸው በፊት የጅማ ኦሮሞ በገዳ ስርአት የሚተዳደር ነበርና ባህሉም ከገዳ ስርአቱ ጋር የተያያዘ ነበር።በኋላ ላይ ግን መንግስታት ገዳውን በመተው የንግስና ስርአት ጀምረው ፤ አምስቱም የጊቤ ግዛቶች የገዳውን ስርአት ቀስ በቀስ እየተዉ መጡ።በተለይም ክልሉ የእስልምና ሀይማኖት በመቀበሉ ወደዚያ ማዘንበል ይታይበት ነበር። ሆኖም ጅማ የራሱን አለባበስ፣አመጋገብ የሰርግና የለቅሶስርአት ይዞ ቀይቷል።አልባሳትን በተመለከተ የጅማ ኦሮሞ ባህል ልብስ የሴትና የወንድ ተብሎ የተለያየ ሲሆን ፤የሴቶቹ ቀሚስ በእጅ የተፈተለነ በጣም ውብ የሆነ ጥለት ያለው ቀሚስና ነጠላ በመልበስ ለጸጉራቸው ደግሞ እንደ አሁኑ (ሂውማን ሄር) ከሰው ጸጉር የተሰራ (ጂግሴ) ሙታለፋ የሚባል ጸጉር ያጠለቁና በሱ ላይ ያለያየ አይነት የብር ጌጣጌጦች ያደርጉበታል። የወንዶቹ ልብስ ከላይ ጀለቢያ ከጎን ጎን ቅድ ያለው (ኪታ)የሚባልና ከስር እንደ ሱሪ ያለ ከላይ ሰፋ ብሎ ከታች የሚጠብ ልብስ በመልበስ ከላይ ስስ ነጠላ ለብሶ ነጭ ጥምጣም የሚመስል ነገር በጭንቅላቱ ይጠመጥማል።በቃለ መጠይቅ እንዳገኘሁትም ሆነ በ2009 ዓ.ም ከታተመው ጅሬን መጽሄት የሴትና የወንድ ተብሎ ከተገለጸው ውጭ ያገኘሁት መረጃ የለም። ምግብ በአብዛኛው ከሌሎች አካባቢ ኦሮሞ ምግብ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በተለይ ወደ 16 አይነት ምግብ ከበቆሎ በመስራት ይመገባሉ። በለተለይ አርኪሶ ፣ ገንፎ ፣ ጨጌ ፣ ኪጆ ፣ ቂጣ፣ የተለያዩ ስራስሮች እንደ ድንች ፣ ወጭኖ ፣ ኮታሬ ፣ አደንጓሬ ምግቦችን ይበላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ምግብን በባህላዊ ዘዴ በማቆየትም በተለይ ስጋን እስከ 6 ወር ድረስ ሳይበለሸ ለማቆየት ዋቅሊሞ ይባላል።ስጋን በትልልቅ ከትፌው ድስት ውስጥ በመክተት ጀርሞች እንዲሞቱ በፈላ ውሃ በማፍላት ከዚያ ጭስ ላይ በመስቀል ለ6 ወር ያቆዩታል። ከዚህም ሌላ በርካታ የምግብ አይነቶች እንደ ቀርሲሳ ፣ ሲኩማ ወዘተ...ምግቦች አሉ።

በጅማ ማህበረሰብ የጋብቻ ባህልን በተመለከተ የሚታወቁት የጋብቻ አይነቶች አምስት ናቸው። እነርሱም፡- ሀሰአና፣አባበሊ፣ረራ፣አሴና፣ቡቲ የሚባሉት ሲሆኑ፡-

1. ሀሰአና የሚባለው ሽማግሌ በመላክ በሁለቱ ቤተሰቦች ፍቃድ ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት የሚያገቡበት የጋብቻ አይነትና በብዛት የሚታወቅ ነው።
2. አባበሊ ሁለቱ ተጋቢዎች በውጭ ጨርሰው ከልጅቷ ቤተሰቦች እውቅና ወንዱ ሴቷን ይዞ የሚገባበት አይነት ነው።

3. ረራ ይህኛው አይነት ልጅቷም ሆነች ቤተሰቦቿ ሳያውቁ የወንዱ ወገን ሽማግሌ ሰብስቦ በሴቷ ቤት ደጃፍ ተቀመጦልጅቷን እንዲሰጧቸው የሚለምኑበት እና ስንትም ቀን ቢቀይ ሳይወስዱ የማይመለሱበት አይነት ነው።
4. አሴና ይህኛው ባል ሳታገኝ የቀየች ሴት አንድ በምትፈልገው ወንድ ቤት በመሄድ የእንጓይ ፍሬዎችን ወደ ቤቱ በመወርወር ልጁን የምታገባበት መንገድ ነው።
5. ይህኛው ጠለፋ የሚባለው ሲሆን ከሴቷ ፍለጎት ውጪ መንገድ ላይ ቀመው በመጥለፍ የሚያገቡት ነው።

በከተማዋ እነዚህ አምስቱ የጋብቻ አይነቶች የሚታወቁ ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት ግን ከእነዚህ ከአምስቱ ቡቲና፣ አሴና እና ረራ የተባሉት የቀሩ ናቸው። አሁን በአብዛኛው አየተጠቀሙበት የሚገኙት ሀሰአና ና አባበሊ የተባለውን የጋብቻ አይነት ነው።

የጅማ ከተማን ስያሜ በተመለከተ የሚነገረው አፈ ታሪክ እንደ ሚያስረዳው ጅማ የሚለው ስያሜ ከመጫ ኦሮሞ ግንድ የሆነ ያንድ ጎሳ ስም ሲሆን በዚሁ የጎሳ ስም ነው ስያሜውን ያገኘችው።[4] የጅማ ከተማ አመሰራረትን በተመለከተ በ 2009 ዓ.ም " jireen" መጽሄት በተቀመጠው የጽሁፍ መረጃ መሰረት ጅማ የተመሰረተችው በ1821 ዓ.ም አካባቢ በንጉስ አባጅፋር አንደኛው (Abajifar I) ዘመነ መንግስት ሲሆን ቤተ መንግስታቸውም አሁን ጅሬን ወደ ተባለው ቦታ አዘዋውረው ከሳቸው ጋር የመጡ ሰዎች ሰፍረውበታል።ከዚያ በኋላ የተለያዩ ሰዎች መጥተው መስፈር ጀመሩ።[3] ጅማ በአሁኑ ጊዜ የ 189 ዐመት ዕድሜ አስቆጥራለች ።ይህች ከተማ በኦሮሚያ ክልል ካሉት ትላልቅ (ታዋቂ) ከሆኑ ከተማዎች ውስጥ የምትመደብ ሲሆን፤ እንዲሁም ከስድስቱ የመስተዳድር ከተሞች ውስጥ አንዷ ናት።ጅማ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀረቀረቸው በጅሬን አሁን የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት በሚገኝበት አካባቢ ነው።ይህች ከተማ ከጣሊያን ወረራ ጀምሮ እያደገች የመጣችና ታዋቂ ከሆኑ ከተማዎች ውስጥ አንዷ እንደሆነች ተገልተጾዋል። ጅማ በአሁኑ ሰአት የከተማው ማእከላዊ ከተማ ሆና እያገለገለች ያለችና በንጉስ በሀይለ ስላሴ ዘመን ደግሞ ከፋ ክፍለ ሀገር መአከላዊ ከተማ መሆኗ ይታወቅ ነበር።[4]

### 3.2 የአጠናን ስልት

ይህ ጥናት በገላጭ የምርምር ዘዴ ተካሄዷል። ገላጭ የምርምር ዘዴ ማለት ተመራማሪዉ አንድን የጥናት ርእሰ ጉዳይ አንስቶ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ

---

[3]በቀን 03/06/11 ዓ.ም ከአቶ ዊዳድ /ፊጣ ጋር በተደረገቃለምይቅ የተገኘ መረጃ።

[4]በ 2009ዓ.ም ባህልና ቱሪዝም ካሳተመው ጅሬን መጽሄት የተወሰደ።

የሚቀርብበት ነዉ። ገላጭ የምርምር ዘዴ በትንታኔ ወቅት አጥኚዋ ያየችዉን ክዋኔዎችና ሁነቶች ላላዩት ሰዎች በአእምሮአቸዉ ምስልን እየከሰተ የማሳየት ኃይል ያለዉ በመሆኑ በመውሊዱ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት የሚደረጉትን ከዋዜማው እስከ ፍጻሜው ያለዉን ስርዓተ ክዋኔ (ዚያራን፣ዱአውን (ጸሎተ ስርአቱን)፣ ቃላዊ ግጥሞችን፣ በአሉን አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎችን ወዘተ.) ያለዉን ሂደት እና ተያየዥነት ያላቸዉን ጉዳዮች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ዉይይት የተገኙ መረጃዎችን ለመግለጽ፣ ለማብራራትና ለመተንተን አስችሏታል።

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

የተመረጡት የጥናቱ ቦታዎችም ሆነ መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮርና በጓድ ጠቀም የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነዉ። ስለሆነም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በጂማ ከተማ ስር ከሚገኙአስራ ሰባት ቀበሌዎች ዉስጥ አንዱ በሆነው በጅሬን ቀበሌ ላይ ብቻ ሲሆን እነሱም በቁባ አባ አረቡ ታሪካዊ ስፍራ ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ቀበሌ በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በከተማው ካሉት የመውሊድ ማክበሪያ ቦታዎች በማህበረሰቡ ዘንድበሰፋት የሚታወቅ በመሆኑ ተመርጧል።

ቀጥሎም ከጅማ ከተማና ከበአሉ ማክበሪያ ስፍራ ለጥናቱ ተገቢ መረጃ ሰጪዎችን ከላይ እንደተገለጸዉ በዓላማ ተኮርና በጓድ ጥቆማ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። የጥናቱ ተሳታፊዎች የተመረጡት ከጥናቱ ዓላማ አንጻር በመሆኑ ነዉ። ስለዚህ የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የማህበረሰቡን ባህልና ታሪክ ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ ተብለዉ ከተመሰከረላቸዉ በእድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃ ትኩረት በማድረግ መረጃ አቀባዮቹ ተመርጠዋል። ከነዚህም ዉስጥ አምስቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸዉ። የተመረጡት መረጃ አቀባዮች በማህበረሰቡ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔን ለማካሄድ በስርአቱ ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ክወና የየራሳቸዉ ተግባር (አስተዋጽኦ) ስላላቸዉ ሁሉን አሳታፊ የሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ችላለች።የመረጃ አቀባዮችም እድሜ ከ20-80 ዓመት ተሳታፊዎች ሆነዋል።

ጥናቱ ከመጠናዊ ይልቅ በአይነታዊ ዘዴ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ላይ መመርኮዙ በጣም ጠቃሚ ሆኗል። አጥኚዋ የመረጃ ፍላጎቷን በአጥጋቢ ሁኔታ እስክታሟላ ድረስ በምልከታ መረጃ ስብሰባ ወቅት አላማዬን በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት ይረዱኛል ባለቻቸው በአንጻራዊ መልኩ ‹የበለጸገ› መረጃ ያላቸው እና ቁልፍ መረጃ አቀባዮች (key informants) ላይ መመርኮዝ ስላስፈለጋት ነው። ከዚህም ባሻገር በአላማ ተኮር አይነታዊ የመረጃ ትንተና ሂደት መረጃ ስብሰባና መረጃ ትንተና አንዱ ባንዱ ላይ ሊነባበሩ የሚችሉ በመሆናቸው የአጥኚዋ አላማ እስኪሳካ ድረስ ትንተናው እየተካሄደ ባለበት ወቅትም ወደፊትና ወደኋላ እየተጓዘች ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብና የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች በበቂ ሁኔታ ለመመለስ የናሙና ስልቱ ገደብ እንደማያደርግባት ስላመነችበት ነው። በሌላ በኩል ጓድ ጠቀም ዘዴ (snowball method) 21 ቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊዎችን በመምረጥ ተፈላጊውን መረጃ ሰብስባለች።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

እንደየጥናቶች ዓይነት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ወይም ቴክኒኮች የተለያዩ ናቸዉ።የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምርጫዉ የሚወሰነዉ ለጥናቱ ተገቢ መረጃ የሚያስገኘዉ የትኛዉ ዘዴ ነዉ በሚለዉ ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ነዉ። ካሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ዉስጥ ለማ (2002፣140) ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ተተኳሪ የቡድን ዉይይት እና መዛግብት ፍተሻ ለፎክሎረኛ ዋነኞቹ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደሆኑ ያስገነዝባሉ። በመሆኑም ከእነዚህ አራት ዘዴዎች ዉስጥ ለዚህ ጥናት ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሆኑ ምልከታን፣ ቃለመጠይቅን እና ተተኳሪ የቡድን ዉይይት ብቻ ጥቅም ላይ ዉለዋል።

### 3.4.1 ምልከታ

ምልከታ አንድ መስከኛ ከውጭ ሆኖ ሌሎች ሰዎች የሚያከናውኑትን ድርጊት ቀጥታ በመመልከት ድርጊቱንም በተመለከተበት ሁኔታ የሚገልጽበት ሲሆን፤ ምልከታው ከእይታው ገጽታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የስሜት ህዋሳቱን በመጠቀም መረጃ የሚያገኝበት ዘዴ መሆኑን Jackson (1987) እና Goldstein (1974) ገልጸዋል። እኔም ይህንን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም በጅማ ከተማ በቁባአባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔ አካሄድ፣ ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ እና በዓሉን አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎች አሰራርና አገልግሎት በምልከታ ቃኝቻለሁ። በተጨማሪም የመውሊዱ በዓል ክዋኔ የሚያስገኘውን ማህበራዊ እና ባህላዊ ጠቀሜታ በምልከታዬ ለመገንዘብ ሞክሪያለሁ።

ምልከታ እንደሚጠናዉ ጉዳይ መለያየት እና አጥኚዉ ከሚያጠናዉ ባህል ባለቤት ጋር እንዳለዉ ቅርበት በሁለት መንገድ ይካሄዳል። በተሳትፎአዊና ኢ-ተሳትፎአዊ ምልከታ ማለት ነዉ። ተሳትፎአዊ ምልከታ ክዋኔዉን ከሚካሄድበት ቡድን ጋር በመቀላቀልና ክዋኔዉን አብሮ በመከወን መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ሲሆን፤ ኢ-ተሳትፎአዊ ምልከታ አጥኚዉ ዳር ሆኖ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነዉ (Sims and Stephens, 2005: 220)። እኔም መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ቦታዉ በሄድኩበት ወቅት በተሳትፎአዊ የምልከታ ዘዴ ተጠቅሜ በሶስት ተፈጥሯአዊ መቼት ላይማለትም በወንዶች የመውሊድ ዋዜማ፣በሴቶች  እና በዋናው ከበራ  ላይ በመገኘት በስርዓተ ክዋኔዉ ከዋዜማው እስከ ፍጻሜውየተደረጉትን ክዋኔዎች ተመልክቻለሁ። እንዲሁም ሙሉ ክዋኔዉን ባይሆንም የተወሰነዉን በቪዲዮ እና ፎቶ ካሜራዎች በመቅረጽ እና ሙሉዉን መረጃ በማስተዋሻ በመመዝገብ ተሰብስቧል።

### 3.4.2 ቃለመጠይቅ

ቃለ መጠይቅ፥አንድ መስከኛ በጥናቱ ውስጥ ለሚያነሳቸው ሀሳቦች እና ሁኔታዎች መረጃ ያስገኙልኛልያላቸውን ጥያቄዎች በማዘጋጀት ስለጉዳዩ መረጃ ይኖራቸዋል ተብለው የሚታመኑ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ መሆኑን Goldstein (1974፥7778)  ጠቁሟል። በዚህ መሰረት እኔም መስክ ላይ በመገኘት ላጠናሁት ጥናት

ተገቢውን መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን በአላማ ተኮር እና በጓድ ጥቆማ ዘዴ በመታገዝ ጥናቱን አካሒጃለሁ። ይህንንም ያደረኩት በአውዱ በመገኘት የመውሊድ በዓሉን ክዋኔ ስመለከት ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችን በቀጥታ ነገሩ ይመለከታቸዋል ከምላቸው የሐይማኖቱ አዋቂዎች (ኡለማዎች) ለመጠየቅ በማሰቤ ነው።

ቃለመጠይቅ በማካሔድበት ወቅት የተጠቀምኩባቸው ስልቶች፤ ቀድመው በተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች /structured interview/ እና ቀድመው ባልተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች (unstructured interview) ሲሆን በዚህም መሰረት ከ21 ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጊያለሁ። ከነዚህ መካከል 5ቱ ቁልፍ መረጃ አቃባዮቸ ናቸው። ከጾታ ስብጥር አንጻር 6 ሴቶች እና 15 ወንዶች ናቸዉ። ሰዎቹ የተመረጡት ባላቸዉ ማህበራዊ ደረጃ፣ እውቀት፣ ስርዓቱን ከሚከዉኑ ሰዎች እንዲሁም ከዕድሜ አኳያ ከ20 እስከ 80 ዕድሜ ያላቸዉ ሰዎች ተካተዋል። የቃለመጠይቁ ተሳታፊዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸዉ ሲሆኑ አብዛኞቹ ስለ ባህሉና እምነቱ ያላቸዉ ዕዉቀት የተመሰከረላቸዉ ናቸዉ።ይህን ተግባር ሳከናውን መቅረጸ ድምጽ (ቴፕ) ተጠቅሚያለሁ። ምክንያቱም ከመስክ በኋላ ደጋግሜ በማዳመጥ ወደ ትርጓሜ እንዲያደርሱኝ በማሰብ ነው።በምልከታ ለማግኘት ያልቻልኳቸዉን መረጃዎች እንዲሁም ከምልከታ በተጨማሪ የከዋኙን ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዮችን በቃለ መጠየቅ ሰብስቤአለሁ።

### 3.4.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከአንድ በላይ የሆኑ መረጃ አቀባዮች የሚሳተፉበት ሲሆን በተለይ በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በቡድን ስለ መደገፋቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ በመገልገልም በግል ያገኘኋቸው አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን፣ መረጃ ሰጭዎችን ማለትም የበዓሉ ታዳሚዎች (ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ)፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ለብዙ ጊዜ የቆዩ፣ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ እንዲሁም የአካባቢውን ታሪክ ያውቃሉ ተብሎ የተመሰከረላቸው ሽማግሌዎችን 4 ጊዜ በማወያየት፤ በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በቡድን ስለመደገፋቸው አረጋግጫለሁ። በዉይይቶቹም በአንድ ዙር ሁለት፣አራት አራትና ስድስት ሰዎች በድምሩ አስራ አራት ሰዎች ተሳትፈዋል።ይህም ዘዴ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ያልተሟሉ መረጃዎችን ለማሟላት አግዞኛል።

በአጠቃላይ በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና በቡድን ዉይይት የተገኙ መረጃዎች በተወሰነ መልኩ በቪዲዮ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ እና በመቅረጸ ድምጽ እንዲሁም በማስተወሻ ደብተር ሙሉዉን መረጃ በመጻፍ ተሰብስበዋል።

## 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

መረጃዎቹ አዉዳዊ (ክዋኔ ተኮር) ንድፈ ሀሳብ (Performance Centered approach) በመመራት የተሰበሰቡ እና የተተረጎሙ ሲሆኑ ገላጭ እና ተንታኝ ዘዴን በመጠቀም ተገልፀዉና ተተንትነዉ ቀርበዋል። በዋናነት መረጃዎችን በማዋቀርና በማደራጀት ለመተንተንመዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ (Structural approach) ጥቅም ላይ

ዉኋል። ይህ ንድፈ ሀሳብ የከበራ ሂደትን እና የመንታ ገጽታዎች አወቃቀርን እና የከበራ ደረጃን በመከፋፈል እንደማህበረሰቡ አመለካከት ወይም ፍልስፍና መሰረት እያደራጀ በመተንተን ላይ ያተኩራል።በመሆኑም በሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማስማማት እና በማደጋገፍ ተብራርቷል። መረጃዎቹ ትንተና በሚደረግበት ወቅትም ማህበረሰቡ ለዘመናት ሲጠቀምበት በኖረዉ የቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ደህረ ሞት ጊዜ ክዋኔ ላይ በመመስረት ሲሆን ለእያንዳንዱ ስርዓቶች የሚሰጣቸዉን ባህላዊ ስያሜዎች ላይ በመመርኮዝ ነዉ።

በዋናነት መረጃዎችን በማዋቀርና በማደራጀት ለመተንተን በአይነት በአይነት በመመደብ የመውሊድ በዓሉን ክዋኔ በሁነት ላይ በመመስረት እየገለጽኩ ወደ ትርጓሜ አምርቻለሁ። በዚህም ዘዴ በመገልገል የክዋኔው ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ እና የሚፈጸሙ ድርጊቶችን (ዝየራ፣ዱአ /ምርቃት/ እና መንዙማ) ከአውዱ በመነሳት አጥንቻለሁ።እንዲሁም አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎች አሰራራቸውን እና አገልግሎታቸውን ከመዳሰስ ባለፈ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳቸውን ተመልክቻለሁ።

# ምእራፍ አራት

# የጥናቱ መረጃ ትንተና

## 4.1 የአባ አረቡ የህይወት ታሪክ ፣ የቁባ አባ አረቡ መስጅድ አመሰራረትና ታሪካዊ ዳራ

### 4.1.1 የአባ አረቡ የህይወት ታሪክ

የአባ አረቡን የሂወት ታሪክ በተመለከተ የተረጋገጠ የጽሁፍ መረጃ ባለመኖሩ ከተለያዩ ሰዎችናቀደም ብለው በዚህ ርእስ ዙሪያ የተጠኑት ሁለት ጥናቶች በአብዶ አደም(1992)እና በሰዩም መርጋ (2007)የተገለጹት መረጃዎች ልዩነት ይታይባቸው ነበር፡ይህ እንዳለ ሆኖ በቀን 12/03/11 ዓ.ም ከሸህ መሀመድ አሚን አብዱል ዋሂድና ከአቶ / አንዋር ሁሴን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስለ አባ አረቡ የህይወት ታሪክና አመጣጥ በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል።

አባ አረቡ ሰኚ አረባ ፤"አህለል በይቲ ዳ"[5] በማለት ንግግራቸውነን ጀመሩ።አባ አረቡ ዘራቸው አረብ ነው።አህለል በይት ናቸው።አባታቸው ከሀገራቸው ከሀገሩ መንግሰት ጋር በስልጣን ተጣልተው ወደ ምስር መዲነቱ ዚቃዚቅ ወረዱ።በዚህ ምክንያት አባ አረቡ እዚሁ ተወለዱ። "የአባ አረቡ የልጅነት ስም ሰይድ አሊ ኢብኑ መሃመድ ሲሆን ስለ ተወለዱበት ዓመተ ምህረትና ስለ ወላጅ እናታቸው ማንነት በቃለ መጠይቅም ሆነ ከቀደምት ጥናቶች የተገኘ መረጃ አለመኖሩ የተሟላ ታሪክ እንደ ሌላቸው ያሳያል።

በተመሳሰይ ቀን ከአቶ አንዋር ሁሴን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስለ አባ አረቡ ሲናገሩ ወደ ኢትዮጵያእንዴት እንደመጡ አይታወቅም። ኢትዮጵያ ውስጥ በኖሩበት ጊዜ ግን አልኖሩበት ዋሻ አለ ለማለት ይከብዳል። ለምሳሌ በጎንደር በማር ዘነብ ዋሻ ፣በወለጋ ሶክሶ ጪመሪ፣ በዴዶ መስመር መንጆ (ዱጋ) እንዲሁም በጅማ እዚሁ አካባቢ ሌንጮ ጊንጮ ውስጥ ይኖሩ እንደ ነበር ሲሉ ፤ ሼህ መሀመድ አሚን አብዱል ዋሂድ ይህንኑ ሀሳብ በማረጋገጥ ስለ አባ አረቡ የህይወት ታሪክ አስመልክቶ በልጅነታቸው እንዴት እዚህ እንደመጡ አይታወቅም።እዚህ ምንም አይነት የስጋ ዘመድ የላቸውም ። በልጅነት እድሚያቸው እንደ ማንም ሰው የሰውን ክብት ይጠብቁ ነበር ይባላል። ኋላ ላይ ግን የወልይነትን አቅም ፈጣሪ ሲያላብሳቸው በዋሻ ውስጥ መኖር እንደ ጀመሩ ይነገራል። ዋሻ ሲባል አንድ ሁለት ዋሻ ሳይሆን ቅድም እንደ ተባለው ከዋሻ ዋሻ እየተዘዋወሩ ነበር የሚኖሩት ይባላል ። ከዋሻ

---

[5]አህለል በይቲ ዳ ይህ ስያሜ (ማዕረግ) የሚሰጠው የነብዩ መሀመድ ቤተሰብ የሆኑ ሁሉ በዚህ ስያሜ ይታወቃሉ። አባ አረቡም የነብዩ ቤተሰብነት አለባቸው ተብሎ ስለሚታሰብ አህለል በይት ናቸው። የሚለውን ስያሜ አግኝተዋል።

ዋሻየሚዘዋወሩበትን ምክንያት ሲጠየቁ ወልይነታቸውን ሰው እንዳያውቅ ከመፈለጋቸው የተነሳ ነው ሲሉ ይልጻገልሉ።[6]

አባ አረቡ በህይወት ዘመናቸው ቀለል ያለ ህይወት የሚኖሩ ሰው ነበሩ።ቤት፣ንብረት ፣ልጅ የሚባል ነገር አላፈሩም። በህይወት የነበሩበትን ጊዜ ኢባዳ በመስራትና ለፈጣሪ በመገዛት ነበር ያሳለፉት።አባአረቡ ከአባ ጅፋር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ይነገራል።ይሁን እንጂ ከአባአረቡ ጋር ፊት ለፊት ተያይተው እንደ ማይተዋወቁና እንዲሁ በመንፈስ እንደሚገናኙ ይነገራል። አባ አረቡን ሰው የማየት አቅም እንደሌለውና እሳቸው ግን ማንንም የማየት አቅም እንዳላቸው፤ይህየሆነበትምምክንያት (ቁድራ ረቢቲ)[7]ከአለህ የተሰጣቸው ብቃት እንደሆነ በቀን 12/03/11 ዓ.ም ከ/አባ ጅሃድ አ/ገሮ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ።

እኚህ ሰው በህይወት ዘመናቸው ካበረከቱት አስተዋጽኦ ጸበል (ዘምዘማ) ከመሬት ውስጥ በአንካሴ (መርጮ) ወግተው በማፍለቅ ለህብረተሰቡ እለት ተእለት ተግባርም ሆነ ከህመማቸው እንዲፈወሱ ምክንያት ሆነዋል።ሌላው ለመጀመሪያ ጊዜ ጫትን የሰዋወቁ እሳቸው እንደሆኑና የተለያዩ ዛፎች በሳቸው ስም ተሰይመው እንዳሉና እንደሚጠቀሙባቸውም ተገልጾዋል።አባ አረቡ እምነትን በማስተማር ረገድ ከሼህ አብዱልሀኪም ቀጥሎ ሁለተኛው ሰው እንደሆኑና እምነቱንም ለማስተማር ብዙ እንደ ታገሉና ብዙ ጊዜ ሞክረው በህብረተሰቡ ተቀባይነት ሳያገኙ በተደጋጋሚ እየሸሹ ቆይተው በኋላ ላይልጆቻቸውን በማስተማር ልጆቻቸው እንዲቀይሯቸው (እንዲያስተምሯቸው)ያደረጉ ሰው መሆናቸውን ተረድቻለሁ።[8]

የአባ አረቡን የህይወት ታሪክ አስመልክቶ ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ መረጃ ባይኖርም በቃል ከተኘው መረጃና ቀደም ብለው ከተጠኑት ጥናቶች በመነሳት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል።

---

[6]በቀን 12/03/11 ዓ.ም ከሸህ መሀመድ አሚን አብዱል ዋሂድና ከ/አቶ አንዋር ሁሴን ጋር በእለቱ በተደረገ ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ።

[7]ቁድራረቢቲ፡-ማለት ከፈጣሪ የሚገኝ ጸጋ/ስጦታ/ ማለት ነው። ፈጣሪ ይህን አይነት ስጦታ የሚሰጠው ለሱ ለሚገዙትና ምርጥ ለሚባሉ ባሪያዎቹ እንደ ሆነ በእምነቱ ዘንድ ይታወቃል።

[8]ከጅማ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ጅማ ፕሮፋይል 2004 ዓ.ም ከሚለው ጥናት የትወሰደ፡

አብዶ አደም(1992) በጥናቱ የአባ አረቡ አመጣጥ ከደንቢዶሎ ይሁን ከአረቡ አለም ምናልባት ሊያረጋግጥልን የሚችል ነገር ቢኖር የተሰየመላቸው ስምና አካላዊ ገጽምታቸው ብቻ ይሆናል።ምክንያቱም አባ አረቡ አረቦ የሚለው ስም አረብ ከሚለው ቃል ጋር ዝምድና ስለሚኖረው ሲል ደምድሞሟል።

ሰዩም መርጋ (2007) የአባ አረቡን ከየት መጣነት በተመለከተ የነዋሪዎችን አባባልና(የትርሃምንግ ሀም1965 ; መሀመድ 1990 ፤ኒሻሀሮ 2009 )ን የጽሁፍ ማስረጃዎች ጠቅሶ  አባአረቡ ወደ ጅማ የመጡት ከደምቢዶሎ እንደሆነና የእስልምና ሀይማኖት ወደ ጅማ የገባው በደንቢዶሎ የእስልምና ሀይማኖት መምህራን እንደሆነና፤ አባአረቡ ከደንቢዶሎ ታላላቅ የእስልምና መሪዎች መካከል አንዱ መሆናቸውን ድምዳሜ ላይ ደርሶዋል።

የአባ አረቡን ከየት መጣነት አስመልክቶ አጥኚዋ የአብዶ አደምን ጥናትና በቃለ መጠይቅ ካገኘችው መረጃ በመነሳት ከአረብ እንደ መጡና የአረብ ዝርያ እንዳላቸው የተገኘው መረጃ አፈ ታሪክ ቢሆንም እንኳ አመጣጣቸውን አስመልክቶ በቃል የተገኘው መረጃ ተመሳሳይ ከመሆኑ በተጨማሪ  አህለል በይት እንደሆኑ ይገልጻል ። እነዚህ መረጃዎች  አረብ እንደሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ አረብ ናቸው ለማለት ያቃርባል።

### 4.1.2 የቁባ አባ አባረቡ አመሰራረት

ቁባ አባ አረቡ ታሪካዊ ስፍራ በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ታሪካዊ ስፍራዎች አንዱ ነው።የነዚህም ታሪካዊ ቦታዎች ስም ቁባ ሼህ ጉዳቶ፣ቁባ ዛዊያ/አበልሀሰን/ እና ቁባ አባአረቡ ሲሆኑ፤የዚህ የቁባ[9] አባ አረቡ አመሰራረትን በተመለከተ ሸህ መሀመዳሚን አብዱል ዋሂድ በቀን 09/03/11 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ምልልስ ላነሳሁላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡- ‹‹ይህ ታሪካዊ ስፍራ እሳቸው ከመሞታቸው በፊት ሜካ ነበር። ከሞቱና ቀብራቸውእዚህ ከተከናወነ በኋላ ነው ታሪካዊ ስፍራ እየሆነ የመጣው።›› የቀብራቸው ስፍራ እዚህ እንዲሆን እንዴት ተመረጠ? ብዬ ላነሳሁላቸው ምላሽ፡- ‹‹መጀመሪያ ይህ ቦታ የጉመይቲ (አባጅፋር እናት) ቦታ ነበር።ጉመይቲ ለአባ አረቡ ትልቅ ቦታ ስለነበራቸው (duayii naa kadhaa) ዱኣ ለምኑልኝ በማለት በስጦታ መልክ አበረከቱላቸው።አባ አረቡም የተበረከተላቸውን ስጦታ ሲቀበሉ (amma ittiin hin jiraannu booda

[9]ቁባ፡- ማለት  የቀብር ቦታ  ሲሆን፤ኡለማ(ወልይ) የሆነ ሰው ሲሞት የሚቀበርበት ቦታ ነው። እንዲህ አይነት ስም ለየትኛውም የቀብር ቦታ የሚሰጥ ሳይሆን፤ ለእንደ ነዚህ አይነት እምነቱ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ሰዎች ሲሞቱ ያንን   ቦታ ተከታዮቻቸው ልክ እነሱ እንዳሉ በማሰብ ቦታው በመሄድ ዚያራ (ሰላምታ) የሚካሄዱበት ቦታ ነው።

kalawaa itiin ijaarrannaa) ‹አሁን ቤት እንሰራባትም ወደፊት ማረፊያ ጎጆ እንሰራበታለን› በማለት ተቀበሏቸው።››

በኋላ ያሉትም ወደፊት በህይወት የሚኖሩበትን ጊዜ አስበው ሳይሆን የሚሞቱበትን ጊዜ ማለታቸው ነበር። በዚሁ ሀሳብ መነሻ መሰረት የቀብራቸው ቦታ እዚህ ሊሆን ቻለ።[10]ይህን ንግግራቸውን ለማን አስተላልፈው ነው የቀብራቸው ቦታ እዚህ ሊሆን የቻለው? ለሚለው ጥያቄ በቀን 08/03/11 ዓ.ም ሸህ ኑራ አባ/ቦር ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፦

‹‹በወቅቱ የአባ አረቡ ካዳሚ የነበሩ አባ/ጆርጋ የተባሉ ሰው ነበሩ።ለሳቸው ነው ወስያ ተናግረዋል የሚባለው፤ነገር ግን አባጆርጋ መልእክቱን አስተላልፈው ብቻ ሳይሆን የቀብራቸው ቦታ እዚህ ሊሆን የቻለው፤ታሪኩ ብዙ ነው።ምን መሰለሽ ዘመኑ በሚኒሊክ ጊዜ ነው አመተ ምህረቱን በቁጥር እርግጠኛ ባለሆንም፤አባ ጅፋር የአባ አረቡ የቅርብ ወዳጅ ናቸው፤እና በወቅቱ አባ ጅፋር በንጉስ ሚኒሊክ እንደ ሚፈለጉ መልእክት ይደርሳቸዋል።ይህን የሰሙ አባ ጅፋር አባ አረቡ ዘንድ ሄደው ‹‹ዱኣ አድርጉልኝ።ንጉሱ ለምን እንደሆን ጠርተውኛል።›› ብለው ሊሰናበቷቸው ሲሄዱ ፤አባ አረቡም ‹‹አብሽር አንተ ምንም ችግር አይደርስብህም፤ በሰላም ትመለሳለህ፤ነገርግን አንተ ስትመለስ እኔን ላታገኘኝ ትችላለህ።›› ብለው ለአባ ጅፋር ሲናገሩ አባ ጅፋር አዝነው፤ላካባቢው ሰው ‹‹እኔ ሳልመጣ ህይወታቸው ካለፈ መስጅደ አፋርተማ[11] የሚባለው መስጂድ ይቀበሩ።››ሲሉ መልእክት አስተላልፈው ወደ ተጠሩበት ቦታ ሄዱ።አባ ጅፋር ያሉት አልቀረም ሳይመለሱ ያርፋሉ።በዚህ ጊዜ የአካባቢው ሰው የንጉሳቸውን ትእዛዝ በማክበር መስጊደ አፋርተማ በሚባለው መስጂድየቀብር ጉድጓድ አዘጋጁ።የአባ አረቡ አካባቢ ሰው ደግሞ ከዚህ ቀደም በተናገሩት ወስያ መሰረት የአሁኑ የመውለድ ስፍራ የቀብር ጉድጓድ አዘጋጁ።በሁለቱም አካባቢ የቀብር ስፍራ በማዘጋጀት በተመሳሳይ ሰአት አስክሬኑን ለመውሰድይመመጣሉ። የመስጅድ አፋረተማ አካባቢ ሰዎች የንጉሳቸውን ትእዛዝ ለመሙላት የአካባቢው ሰዎችደግሞ የአባ አረቡን ወስያ ለመሙላት ሲሉ ሁለቱም ተገናኙ።በመጀመሪያ የመስጂደ አፋርተማ አካባቢ ሰዎች አራት ሆነው ለማንሳት ሞከሩ።አቃታቸው፤ለስምንት ሞከሩ አሁንምአቃታቸው።ለአስራ ሁለት ሰውሆነው ሞከሩ ሊንቀሳቀስልቸው አልቻለም።በዚህን ጊዜየአካባቢው ሰዎች ‹‹አሁን ይበቃችኋል፤እኛ ደግሞ ተራችንን እንሞክር›› ብለው ለአራት ሰው ሲያነሱ አስክሬኑ ያለምንም ችግር ተነሳላቸው።በዚህ ምክንያት የቀብር ቦታቸው እዚህ ሊሆን ቻለ።የቦታው አመሰራረት ታሪኩ ይህ ነው። ስለ ታሪኩ እውነትነት (በቀን 13/03/11 ዓ.ም) ከሸህ ኑራ፣ከሸህ መሀመድ አሚን እና ከአባ መጫ ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት ለማረጋገጥ ችያለሁ።

---

[10]በቀን 09/03/11 ዓ.ም ከ ሸህ መሀመድ አሚን አብዱልዋሂድ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ

[11]መስጂድ አፋርተማ፦ይህ መስጂድ የተሰየመው ለመጀመሪያ ቀን የጁመአ ሰላት ሲሰገድ አርባ ሰዎች በመስገዳቸው ምክንያት የተሰጠው ስያሜነው።የንጉስ አባ ጅፋር ቀብርም በዚሁ መስጂድ ይገኛል።

ከአባ መጫ አባ አረቡን በቀን 12/03/11 ዓ.ም ቁባ አባ አረቡ ማለት ምን ማለት ነው ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡-

ቁባ አባ አረቡ ማለት የአባ አረቡ መቃብር ማለት ነው።የሳቸውም ቁባ ይሄ የምታይው ነጭ ቀለም የተቀባው ቤት ነው።ሌሎቹ ቤቶች እንገዳ ሲመጣ፤እዚሁ አካባቢም ያሉ ሰዎች ለዱአ ሲቀመጡ በነዚህ ቤቶችውስጥ ነው የሚያሳልፉት።

የቤቶቹን ታሪክ በተመለከተ፡-በመጀመሪያ ቀብሩ ብቻ ነበር የነበረው። ከዚያም በአካባቢው ሰው ምክንያት በላዩላይ የአሁኑ አይነት ሳይሆን ቆርቆሮ ቤት ተሰራ። የቤቱ መሰራት ምክንያቱ የአካባቢው ሰው ለሳቸው ያለውን ክብር ለመገለጽ ሲል እንደሆነ ተረድቻለሁ።በአካባቢው ያለ ቆርቆሮ ቤት እሱ ብቻ ነበር። በኋላ አባ ጅርጋ የሚባሉ የሳቸው ካዳሚ ነበሩ።አባ አረቡ ሲሞቱ ብቻቸውን ይቀራሉ።ቤትም የላቸውም።ከዚያ አባ አረቡ ከአካባቢው ሰው ለአዱ በህለም አባጅርጋ እንደተቸገረ ይታያቸዋል።ከዚያ እዚያው የቀብሩ ግቢ ውስጥ አሁን ያለችው ጎጆ ቤት ለአባ ጅርጋ ተሰራችላቸው።ከዚያም አባ ጅርጋ በዛሄር ባይኖሩም፤እየካደሙ መኖር ቀጠሉ።የአባ አረቡ ተከታይ የሆኑ መእመናን በየጊዜው እየመጡ እሳቸውን እየዘየሩ መሄድ ጀመሩ።በሚመጡ ሰዓት መእመናኑን ተቀብለው የሚያዘይሩት አባ ጅርጋ ነበሩ።ከዚያምእመናኑ እየበዛ ሲሄድ ለዚያራ ከገባው ገንዘብና በአካባቢው ሰው እርዳታ እዚህ ውስጥ የምታያቸው ቤቶች መሰራት ቻሉ።ከቀብሩ ቀጥሎ ሁለተኛው ቤት ግን ይች ጎጆ ቤት ነበረች።በግቢው ውስጥ በአጠቃላይ ከመስጂዱና ከቁባው ውጭ ስድስት ቤቶች አሉ።የነዚህ ስድስት ቤቶችም መኖር አገልግሎታቸው ከላይ እንደተገለጸው በየትኛውም ጊዜ እንግዳ ማስተናገድ ነው።[12] ሲሉ ገልጸውልኛል።

ይህ ስፈራ መች ተመሰረተ የሚለውን ጥያቄ ለማረጋገጥ አቶአንዋር ሁሴን (ደርጋ)[13]፣ አባ መጫ አባ አረቡ (የአባ አረቡ ካዳሚ)[14] እና ለአባ ጅሀድአባ ገሮት (ከዐሥር ጊዜ በአሉ በላይ ላይ የተገኙ) ላቀረበኩላቸ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡-

‹‹ቀኑ ይሄ ነው ባይባልም የሳቸው ቀብር ከተካሄደ በኋላ ነው።ቀብራቸው ከተፈጸመ በኋላ ቅድም እንደሰማሽው የመጀመሪያው ቆርቆሮ ቤት በአካባቢው ሰው ተሰራ።የሞቱት በሂጅራ አቆጣጠር 1329 አ.ሂ ነው።ስለዚህ ይህ ታሪካዊ ስፍራ የተመሰረተው በዚህ ዓ.ም ነው ማለት ነው። ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ይህ ታሪካዊ ስፍራ የተመሰረተው በ1900 ዓ.ም ሲሆን ፤111 አመት እድሜ አስቆጥሮዋል ማለት ነው።››

[12]በቀን 12/03/11 ዓ.ም ከ አባ መጫ አባ አረቡ (የአባ አረቡ ካዳሚ) ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የተገኘ መረጃ፤

[13]ደርጋ፡- ማለት አባ አረቡን ለመካደም ሲሉ ወደ እዚህ አካባቢበመምጣት ከግቢው ውጭ የሚኖሩ የአባ አረቡ ተከታዮች ማለት ነው።

[14]ካዲሚ፡-አባ አረቡን በመካደምና ለመካደም በቁባው (በቀብራቸው ስፍራ)በግቢው ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

### 4.1.3 **የቁባ አባ አረቡ መስጂድ አመሰራረት**

*የአባ ኣረቡ መስጂድ በአሁኑ ሰኣትበከተማው ውስጥከሚገኙት ትላልቅ መስጂዶች የጁመዓ ሰላት የሚሰገድበት መስጂድ ነው። የዚህን መስጂድ አመሰራረትን በተመለከተ አቶአነዋር ሁሴንና አባመጫ አባአረቡ በቀን* 12/03/11 *ዓ.ም በተደረገ ቃለ ምልልስ ላነሰሁላቸው ጥያቂ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡-‹‹መስጂዱ በመጀመሪያ ሲሰራ እንዲህ አልነበረም።የአካባቢው ሰውና አባ አረቡን ብለው የሚመጡ ሰዎች የሚሰግዱባት ትንሽ መስጂድ ነበረች። ኋላ ላይ የአካባቢው ሰው እየጠበበው ሲመጣ፤ለማስፋትና የተሻለ አድረጎ ለመስራት በመወሰን፤የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ለመስራት ሲሯሯጡ አንድ ከኣጋሮ አካባቢ አባአረቡን ለመዘየር የመጣ ሰው ይመለከታቸዋል።ይህ ሰው አቶአባድር ይባላል። እንዲህ ሲል ይጠይቃል። ‹ምን ለመስራት ነው እንደዚህ የሚሆኑት?› ሲል ‹መስጂድ ለመስራት ነው።› ሲሉት እኔ እራሴ እሰራዋለሁ። በማለት ይሄ አሁን የምታይውን መስጂድ ሰራው።ከዚያ በኋላ በግራና በቀኝ የበረንዳ ቆርቆሮ፣ቀለምና እድሳት ከማድረግ ውጭ ምንም የተቀየረ ነገር የለም።የተሰራበትን ዘመን እንዲህ ነው ብዬ ለመናገር ቢከብድም፤በኀይለስላሴ ዘመን ነው።አባ አረቡ ከሞቱ በኋላ ማለት ነው።›› በተመሳሳይ መልኩም ከአባመጫ አባ አረቡ ጋር ከላይ በተጠቀሰው ቀን በተደረገ ቃለ መጠይቅ መስጂዱ የሚገኝበትን ቦታ ሲያብራሩ፡-*

*"መስጂዱ ከአባ /አረቡ መቃብር /ቁባ/ በስተ ግራ የሚገኝ ሲሆን፤የሆነበትንም ምክንያት ሲናገሩ ሰፋ ያለ ቦታ ያለው በዚህ በስተግራ በኩል ስለነበረ እንደሆነ ይናገራሉ።ይህን ቦታ በአቃላይ መስጂዱን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ቦተውን ጉመይቲ /የአባ ጅፋር እናት/ ናቸው፤ አ/አረቡ በህይወት እያሉ በስጦታ መልክ ያበረከቱላቸው።ነገር ግን መስጂዱም ሆነ ሌሎች እዚህ የምታያቸው ቤቶች የተሰሩት የሳቸው ቀብር እዚህ ከተፈጸመ በኋላ ነው።"*[15] *በማለት ነግረውኛል።*

*ከዚህ ገለጻ ለመረዳት እንደሚቻለው መስጂዱ የአሁኑን ቅርጽ ከመያዙ በፊት ትንሽ መስጂድ እንደተጀመረና፤ዘመኑ በትክክል ባይታወቅም በሀይለስላሴ ዘመን በአካባቢው ማህበረሰብ የተጀመረውን መስጂድ ‹በራሴ ወጪ እሰራዋለሁ› በማለት አንድ አህለል ከይር እንደሰራውና፤ከዚያ በኋላም እድሳትና የሁለት በኩል በረንዳዎችን ከመጨመር ውጭ ብዙም ለውጥ እንዳልተደረገለትለመረዳት ችያለሁ። በዚህ ስፍራ መስጂዱንና የአባአረቡን መቃብር ሳይጨምር አምስት በቆርቆሮና አንድ በሳር የተሰራ ቤት ተመልክቻለሁ።*

*በተጨማሪም ከአ/መጫ አ/አረቡ(የአ/አረቡ ካዳሚ) ጋር በእለቱ በተደረገ ቃለ ምልልስ፡-*

*"በመስጂዱ የጁመአ ሰላት ከመሰገዱ በተጨማሪ በረመዳን ጾም ሰላት የሚሰገድበት መሆኑን ገልጸው፤ቤቶቹ ደግሞ አባአረቡን ለመዘየር ከሩቅ አካባቢ ለሚመጡ ምእመናን ማረፊያ ነው።ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ማህበረሰብ ሰግዶ ዱኣ ሲቀመጥ ይገለገልበታል።" በማለት ምላሽ ሰጥተውኛል።*

*ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለሸህ መሀመድ አሚን አዱል ዋሂድ በዚሁ ቀን ላነሳሁላቸው ጥያቄ ምላሽ፡-‹‹በዋናነት*

---

[15]*በቀን*12/03/11 *ዓ.ምአቶ/አነዋር ሁሴንና አባ መጫ አባ አረቡ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የተገኘ መረጃ*

ተግባሩ ምእመናን የሰላት ሲደርስ ገብተው የሚሰግዱበት፣ ቁርኣን የሚቀሩበትና ዱኣ የሚያደርጉበት ነው።በረንዳ ላይ የተቀመጡት የተለዩ ናቸው ወይ ላልሽው …ምንም ከሌላው ሰው የተለዩ አይደሉም ፤ከሌላ ቦታ የመጡ የአ/አረቡ ተከታዮች ናቸው።እንደምታይው ያሉት ቤቶች ሁሉ ሞልተዋል፤ሜዳው ሁሉ በዳስ ተጨናንቀዋል።እነዚህ ቦታ ስላጡ ነው በረንዳ የተቀመጡት ፤የተለዩ ስለሆኑ አይደለም።የምመናኑን አቀማመጥ ተመልክተሽል ? እዚህ ሜዳ ላይ ስንት ቡድን እንዳለ ፤ከግቢ ውጭ ብትመለከቺ በራሱ ለመቁጠር የሚከብድሽ ያህል ቡድን ነው ተመስርቶ የምታይው፤ይህ ደግሞ በራሱ ባህላዊ ውበት ነው። እያንዳንዱ በራሱ ሃኛ የተጠመደ ነው።አጠገብ ለአጠገብ ሆነው እንኳን የአንዱ መንዙማ ሌላውን አይረብሽም፤የአንዱ ዱኣ ሌላውን አይረብሽም፤ይህ በራሱ መቻቻልን የምትማሪበት ቦታ ነው።በአዳራሽ ከምተይው ትእይንት የበለጠ የምታይው እዚህ ነው። አሁን እዚህ ያየሽው ሰው ጥዋት ሲነጋ አታገኚውም ፤ነገ ደግሞ ሌላ ቡድን የራሱን ሽራ ወጥሮ ታይዋለሽ ፤እንደውም እኔ ሊቀር የማይገባው ባህል ነው።›› [16]

**ምስል አንድ፡መውሊዱ የሚከበርበትን ቦታ የሚያሳይ ፎቶ**




[16] **በቀን** 12/03/11**ዓ.ም በዋናው በአል እለት የተደረገ ቃለ መጠይቅ**

### 4.1.4 የመውለድ ክብረ በዓል ምንነት ና ዓይነት

መውሊድን በሚያከብሩ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሁለት አይነት የመውሊድ ክብረ በአላት አሉ። እነዚህም ክብረ በአላት ረቢል አወል (የነቢዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበር) እና የኡለማ መውሊድ (በህይወት በነበሩበት ወቅት በእምነቱ ታላቅ አሊም (አዋቂ) የነበሩትን ታላላቅ ግለሰቦች ለማሰብ የሚከበር መውሊድ) በመባል ይከፈላሉ። የ(ረቢል አወል) መውሊድ ክብረ በዓል የነብዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት በማድረግ በየአመቱ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየመስጊዱ በመሰባሰብ የነብዩ መሐመድ ታሪካቸውና ውዳሴአቸው እየተነበበ በአማኙ ህብረተሰብ ዘንድ በቋሚነት የሚከበር በዓል ነው።

ይህ በዓል ሲከበር እንደ ማህበረሰቡ ልምድና ባህል ፤የአከባበሩ ስርአት፣ ውዳሴው እና የሚቀርብበትመንገድ ይለያያል። ይህም ሲባል የህብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ እና የዘመኑ መንፈስ ሲቀየር ፡ የክብረ በዓሉ ይዘት እና ቅርጽ በተወሰነ መልኩ ይቀየራል ማለትነው። የመውሊድ ክብረ በዓል ና ታሪካዊ መነሻን የክብረ በዓሉን ሂደት በማስመልከት ፡ሸህ መህመድ አሚን አብዱል ዋሂድ (የቁባ አ/አረቡ መስጂድ ኢማም) ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ፡ የመውሊድ ክብረ በዓል ምንድን ነው? ታሪካዊ መነሻውስ ምን ይመስላል? ብዬ ለጠየኳቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ቃል በቃል ሰጥውኛል።

“ታሪክ የሌለው ነገር ሁሉ መሰረት የለውም። ነብዩ ሙህመድ ተወልደው በ40ኛው ዓመት ሲሞላቸው የአላህን ትእዛዝ በመቀበል የእስልምናን ሀይማኖት የመሩ የመጨረሻ ነብይ ናቸው። በዚህም መሰረት በእስልምና ዙሪያ ያሉትን ድንጋጌዎች ሁሉ ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ያስተዋወቁት እሳቸው ናቸው። በዚህ መሰረት ለሳቸው ክብርና ዝና ለማስተዋወቅ /ለማሳወቅ/በእምነቱ የተለያዩ አጋጣሚዎች ተቀምጠዋል።ከነዚህም መካከል ዋናውና የመጀመሪያው አንድ ሰው በአላህ አንድነትና በነብዩ መልዕክተኛነት ካላመነ ሙስሊም አይባልም። ለዚህም መሰረቱ ሁል ጊዜ አላህን ባወሳን ቁጥር እንድናወሳቸው /እንድናስታውሳቸው ታዟል። ለምሳሌ፡-አዛን ሲወጣ(ሲባል) ስማቸው ይጠራል፣ በቀን በ5ቱ ሰላት ላይ ስማቸው ይነሳል።

በአጠቃላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ ሁሉ አስፈላጊውን ድንጋጌ ያስቀመጡ በመሆናቸው ስራው ራሱ የግድ እንድናስታውሳቸው ያደርጋል። በሌላ መልኩ ደግሞ እንደ ማንኛውም ታዋቂ ሰዎች በሙስሊሞች ዘንድ በአመት ልዩ ቀን ተደርጎ እንድናስታውሳቸው ተቀምጧል። በተለይ የተወለዱበትን ዕለት በማክበር። ይኸም የሚጠቅመው በይበልጥ ልክ በሳይንስም ፣ በፖለቲካም፣የሀገርን ጉዳይ፣ የነፃነት ቀን ተብሎ እንደሚሰየም ሁሉ በሀይማኖት በኩልም መሪያችን በመሆናቸው አርአያቸውን ለመከተል እንድንችል የተወለዱበትን ቀን በማክበር ሙስሊሙ ህብረተሰብ ዝናቸውን እንዲያስታውስና እንዲከተላቸው ጎላ ባለ ሁኔታ በመውሊድ መልክ ይከበራል። በተለይ በስራ ተጠምደው አመቱን ሙሉ ለሚያሳልፉ ሰዎች ማህበራዊ

ህይወት ለመፍጠርና ለማደስ ትልቅ አጋጣሚ ይሆንላቸዋል፡ …›› በማለትይገልጻሉ። (ለሸህ መሀመድ አሚን አብዱል ዋሂድ (የቁባ አ/አረቡ መስጊድ ኢማም) በበአሉ ማክበሪያ ቦታ በዕለቱ የተደረገ ቃለ መጠይቅ።)

ስለዚህ የነቢዩ ሙሀመድ የመውሊድ ክብረ በዓል የነቢዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት በማድረግ በየዓመቱ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየመስጊዱ በመሰባሰብ በአማኙ ህብረተሰብ ዘንድ ታሪካቸውና ውዳሴአቸው እየተነበበ በማነቃቃት የእምነቱን መሰረታዊ መሰረቶች እንዳይረሳ ለማድረግ በቋሚነት የሚከበር በዓል ነው።

ሁለተኛው እና የዚህ ጥናት የትኩረት ጉዳይ ደግሞ የኡለማ መዉሊድ ነው። የኡለማ መውሊድ የሚከበረው በአንድ አካባቢ ነው። የሚከበርበትም ምክንያት በህይወት በነበሩበት ወቅት በእምነቱ ታላላቅ ኡለማ (አዋቂ) የነበሩትንና ታላላቅ ስራዎችን ለዕምነቱ ያከናወኑትን ግለሰቦች ለማሰብ ነው። አቶ አንዋር ሁሴን (የቁባ አ/አረቡ የመውሊድ በዓል አስተባባሪ) እንደገለጹልኝ "የኡለማ መውሊድ ማለት በእስልምና እምነት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስማቸው ከፍ ብሎ ለሚጠሩ ሰዎች የሚከበር ነው።እነዚህ ሰዎች የሰሯቸው መልካም ስራዎች ለአማኙ በምሳሌነት የሚጠቀስ፣ የነብዩ ሙሐመድን አርአያነት የተከተሉ፣ እውቀታቸው የተመሰከረላቸው፣ በልዩ ልዩ ገድል የሚታወቁ ወ.ዘ.ተ.ናቸው።" በማለት ነግረውኛል።

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍም በጅማ ከተማ የቁባ አ/አረቡ የመውሊድ በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (የኡለማ መውሊድ) የአከባበር ስርዓት፣ ክዋኔውን እንዲሁም ማህበራዊ ፋይዳው በመዳሰስ ቀርቧል።

### 4.1.5 የቁባ አባ አረቡ መውሊድ ታሪካዊ አጀማመር

የቁባ አባ አረቡ የመውለድ በዓል መከበር የጀመረው ህይታቸው ካለፈ በኋላ ነው።ይህም 1900ዓ.ም እንደ ሆነ ለመረዳት ችያለው።[17]

ይህ ታሪካዊ አጀማመር አስመልክቶ በቀን 13/03/11 ዓ.ም ከአቶ አንዋር ሁሴን (ደርጋ)
ጋርባደረኩት ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ነገሩኝ፡-

አባአረቡ ከሞቱ በኋላ ምእመኑ እሳቸውን በማሰብ ለመዘየር በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ቦታዎች በተለይ የነብዩን መውሊድ ምክንያት በማድረግ ከአንድ ሁለቴ በኋላ እየተደጋገመ ሲሄድ ቋሚ ሆኖ ቀረ።ይህንን ቀንም ሁሉም ሰው በውስጡ በራሱ መነሳሳት ሲመጣ ከሌላው ጋር በመገናኘቱ፤እንጂ ይህን ቀን ብሎ የወሰነለት አልነበረም። በእንዲህ አይነት መለኩ የተጀመረ የበዓል ቀን አሁን ብዙ ሺ ህዝቦችን በማስተናገድ እየተከበረ ይገኛል።በዚህ ሀሳብ መነሻነት የቁባ አ/አባ አረቡ የመውሊድ ክብረ በዓል መሰረታዊ መነሻ የነበረው የወዳጃቸው ፍላጎት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።በዚህምጊዜ የሚከበርበትን ቀን ተነጋግረው የወሰኑ ሳይሆን በተደጋጋሚ የመእመናኑ ቁጥር በየእለቱ እየበዛ በመሄዱ ቋሚ ቀን እንዲሆን እንዳስቻለ ከቃለ መጠይቁ ለመረዳት ችያለሁ።

---

[17]ከሸህ መሀመድአሚን አብዱልዋሂድ (የቁባ አባ አረቡ መስጂድ ኢማም)

በፎክሎር መስክ የሚደረጉ ምርምር እና ጥናቶች እንደ ሚያመላክቱት ከሆነ ደግሞ የእያንዳንዱክብረበአል የሚከበርበት ዕለት የሚወሰነው ለክበራው በሚያመች ወቅት መሆኑን ይጠቁማሉ።በዚህጥናት ወቅት ከሰበሰብኩት መረጃ ለመረዳት እንደቻልኩት ከሆነ ደግሞ የቁባ አ/ አረቡ የመውሊድክብረ በአል በዋናነት (ረቢያል አወል 12 ) ላይ እንዲከበር የተወሰነ ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያቱ በዚህ ቀን የነብዩ የልደት ቀን መሆኑመጀመሪያ ምዕመናኑ የተሰበሰቡበትና እነሱምለመሰብሰባቸው ምክንያት ይህ የመውሊድ በዓል ነበር፤ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ረቢያል አወል 8 እና9 ቀደም ብለው እንደ ሚያከብሩ ተረድቻለሁ።

ይሁን እንጂ የረቢያል አወል መውሊድ የጨረቃን ኡደት (የሂጅራን ቀን አቆጣጠር ) ተከትሎ ስለሚከበር በየአመቱ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የወራትና የቀናት ለውጥ እንደ ሚያደርግ ግለጽ ቢሆንም፤የነብዩ መውሊድ በረቢያል አወል 12 ከመከበሩ በፊት ያለው ቀን 8እና9 በቋሚነት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በቀን 8 በአካባቢው ወንዶች የሚከበር መውሊድ ሲሆን በቀን 9 ደግሞ በሴቶች እንዲከበር ማህበረሰቡ ተስማምቶ ያከብረዋል።ቀን 8 እና 9 የተመረጡበትንምክንያት ሲናገሩ ወደ መውለድ ማክበሪያ ስፍራው ምእመናን ከተለያዩ አካባቢዎች ቀድመው ስለሚገቡ እነሱን ለመቀበልና ለማብላት ሲባል ነው።በሚልእሳቤ ከረቢያል አወል 12 በፊት እነዚህ ቀናት ቋሚ የአካባቢው የመውለድ ቀን በመሆንበአካባቢውማህበረሰብዘንድበታላቅድምቀትይከበራል[18]።

## 4.2 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓልስርዓተ ክዋኔ ፣ ቃላዊ ግጥሞች ና በዕለቱ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች

በዚህ ንኡስ ምዕራፍ ስር የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞችና በዕለቱ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች ገፅታን፣ ለስርዐተ ክዋኔው ዝግጅት ከሚከውናቸው ድርጊቶች ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ ያለው ሂደት በስፋት ተተንትነው ቀርበዋል። ከዚህ በተጨማሪም ክዋኔውን አጅበው የመጡትን ቃላዊ ግጥሞችና በዕለቱ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች ለክዋኔው ሙሉነት ያላቸው ፋይዳ ተዳሷል። በዚህ ሂደት ውስጥም በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ከመውሊድ ባህሉ እና ስርአቱ ጋር የሚገናኙ ነጥቦችን ከመቃኘት ባለፈ በክዋኔው ወቅት የመጡ ትዕምርታዊ ጉዳዮች ተተርጉመዋል።

### 4.2.1 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔ

የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔ ራሱን የቻለ ሂደት ያለውና በሁነቶች የተሞላ ነው። ሁነቶቹ ከክዋኔው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸውና አንዱ ሁነት ለሌላው መነሻ የሆኑ የተለያዩ ክንዋኔዎችን አካቶ ይዟል። በዚህ ክፍልም የበዓሉ ስርዓተ ክዋኔ የሚያካትታቸውን ሁነቶች ከፋፍሎ በማስቀመጥ እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

#### 4.2..1.1 **የሥርዐተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት**

ክብረ በዓል ላይ ትኩረት ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ማንኛውም ክብረ በዓል ሂደቱን የሚጀምረው ከክብረ በዓሉ በፊት በሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች መሆኑን ይጠቁማሉ። በተመሳሳይ መልኩ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች ይጀምራል። ይህ የስርዐተ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት ደግሞ መውሊዱ ሥርዐቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው።

በዚህ ጊዜ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግል የማገዶ እንጨት ዝግጅት፤ የግቢ ፅዳት፤ አጥር ማጠናከር፤ የምግብ ዝግጅት (የጤፍ ዱቄት፣ የበቆሎ ዱቄት፣ የወተት ተዋፅኦ፣ ቅጭቅጫ፣ሌሎች ለወጥ መስሪያ የሚያስፈልጉ ግብአቶች) የዳስ (የድንኳን) ስራ እና የቁሳቁስ አቅርቦትን የሚያካትት ነው። ይህንኑ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተም (ደርጋ) ለአባ አረቡ ሲሉ በአካባቢው ለሚኖሩትለአቶ አንዋር ሁሴን በ08/03/2011 ዓ.ም ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ እንደተለጸልኝ እና እኔም በቦታው ላይ በነበረኝ አስተውሎት እንዳረጋገጥኩት፤ የሥርዐተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት የሚጀምረው ዋናው በዓል ከመድረሱ 10 ቀን በፊት ነው። በዚህም ጊዜም የሚኖረው የሥራ ድርሻ እንደ እድሜ ደረጃና ፆታ የተለያየ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በቀላሉና በተቀላጠፈ መልኩ ቅድመ ዝግጅቱ እንዲቋጭ በመታሰቡ እንደሆነ ከአቶ እንዋር ሁሴን ጋር ባደረኩት ቃለምልልስ ለመረዳት ችያለሁ። ይህንንም ቅደመ ዝግጅት የወንዶች (የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባቶችና ወጣቶች) ሴቶች (እናቶችና የታዳጊዎች ሚና) ብሎ በመከፋፈል እንደሚተለው መመልከት እንችላለን።

***ሀ.በቅድመ ዝግጅቱ የወንዶች ሚና፡-*** በዚህ ስር ያለውን ክንውን በሶስት ከፋፍለን ድርሻቸውን መመልከት እንችላለን።

1.Abbaa jaarsaa (የሀገር ሽማግሌ) የአካባቢውን ማህበረሰብ በማወያየት ለዋዜማው እለት እርድ የሚሆነውን በሬ መግዣ የሚሆን ብር የሚገኝበትን መንገድ ያመቻቻሉ። የአካባቢው ህዝብ ይህ ነው የሚባል ክፍያ ሳይጣልበት ይህን ያህል እሰጣለሁ፤ በማለት ኒያቸውን ተቀብለው በነዚህ ሰዎች መሠረት ገንዘብ ተሠብስቦ ለዕርድ የሚሆነው በሬ እንደሚገዛ እና ከበሬ የሚቀር ገንዘብ ካለ ለሌሎች ወጪዎች ለስኳር፣ ጫት፣ እጣን ለመሳሰሉት ይውሉ ዘንድ አስተካክለው እስከ እለቱ ያኖራሉ። እነዚህን ስራዎች በዋናነት የሚያስተባብሩት የመውሊድ አዘጋጅ ኮሚቴ ተደርገው የሚወሰዱት አባጃርሳ ናቸው። እነዚህ አካላት ስራውን ለማስፈፀም የበላይ በመሆን ይቀመጡ እንጂ ማህበረሰቡ ስራውን በራሱ ተነሳሽነት ገንዘቡንና ጉልበቱን መስዋእት በማድረግ እንደሚፈጽሙ ከአቶ ጁነዲን ከድር ጋር በቀን 07/03/11ዓ.ም ባደረኩት ቃለ መጠይቅ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡-“ሰው እንዲህ አይነት ተግባር ታዞ አይደለም ወይም ስጥ ተብሎ አይደለም /አጅሪ ኢሳኒ/ ከሳቸው የሚከፈለኝ ነገር አለ ብሎና የሳቸው ውዴታ ለማግኘት ነው።”

2. የአባቶች ሚና ወጣቶችን በማስተባበር አጥር ማሳጠር ማጠር የዕርድ ተግባራትን ማከናወን እንደዚሁም በዕድሜ ከፍ ያሉ አባቶች (አዛውንቶች) ተመርጠው በበዓለ ዕለቱ ምዕመናን ለማስዘየርና ዱአ ለማድረግ፤ተመርጠው ይቀመጣሉ። ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው መውሊድን ሲያስብ ከሳቸው የሚገኘውን አጅር[18] በማሰብ በደስታና በነቃ ተሳትፎ እንደሚያከብር ያሳያል።[19]

3. ወጣቶችበዋዜማው ለሚከበረው መውሊድ እንጨት መፍለጥ ዉሃ መቅዳት የታረደውን ዕርድ ለእናቶች ሲሰሩ እንዲቀላቸው ማስተካከል የዳስ ተከላ የአጥር ማጠንከር ወዘተ… ስራዎችንና ከበዓሉ ዋዜማ እስከ ፍፃሜው ድረስ ምዕመናን አደጋ እንዳይደርስባቸው ከፖሊስ ጎን በመቆም የበኩላቸውን ደርሻ ለመወጣት እራሳቸውን ቀደም ብለው እንደሚያዘጋጁ በቃለመጠይቅ ወቅት ባገኘሁት መረጃ ለማረጋገጥ ችያለሁ።[20]

**ለ. በቅድመ ዝግጅቱ የሴቶች ሚና፡-** በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርዐት ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት በሴቶች የሚከናወን መሠረታዊ ነገር የምግብ ዝግጅት ነው። የዚህም ዝግጅት የሚጀምረው ወንዶች ለበሬ የሚሆነውን ብር ለማሰባሰብ ቀደም ብለው እንደሚዘጋጁበት ሁሉ በዚህም በኩል ቀደም ተብሎ ነው። የአካባቢው ተወላጅና ነዋሪ (ደር.ጋ) የሆኑት ወ/ሮ አለውያ ከማል በቀን 07/03/2011 ዓ.ም እንደገለፁልኝ፤ የምግብ ዝግጅት የሚጀምረው ለእንጀራ፣ ለገንፎና ለወጥ የሚሆኑ አስፈላጊ የሆኑ የእህልና የቅመም አይነቶችና በማዘጋጀት ነው።

በዚህም መሠረት በሴቶች በኩል አስፈላጊ የተባሉት ነገሮች ሁሉ የሚሟሉት በራስ ኒያ (በፍቃደኝነት) ላይ ተመስርቶ ነው። ሁሉም ነገሮች ይሟላሉ፤ ነገር ግን አንቺ ይሄን አንቺ ያን ተብላ ሳይሆን ሁሉም ነገር ግን አንቺ ይሄን አንቺ ያንን ተብላ ሳይሆን፤ ሁሉም በራሱ ይህን ሰጣለሁ፤ በማለት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ሴቶች ቀደም ብለው አዘጋጅተው እንደሚያስቀምጡ ከወ/ሮ ዜኒያ አ/ሚልኪ (የአካባቢው ነዋሪ) ጋር በዕለቱ በተደረገ ቃለ መጠየቅ ለመረዳት ችያለሁ።

**ሐ. በቅድመ ዝግጁቱ የታዳጊዎች ሚና፤** በቅድመ ዝግጁቱ የታዳሚዎች ሚና (እድሚያቸው ከ10 እስከ 20 የሆኑ ወንድና ሴቶችን ያጠቃልላል።) ለክብረ በዓሉ ሳምንት ያህል ጊዜ ሲቀር የበዐሉ መከበሪያ ቦታ የሆነውን የቁባ አባአረቡ አጥር ውስጥ ያለውን ሳር በማጨድወንዶቹ ሲያፀዱ ሴቶች ደግሞ በግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶች በመጥረግና አቧራው እንዳይነሳ ወሃ ያርከፈክፋሉ፤ ውሃውን የማምጣት ተግባር የሚፈፅሙት ደግሞ ወንዶቹ ናቸው። ይህን የሚያደርጉበትና ምክንያት አንደኛው የበኩላቸንን አስተዋፅኦ እንወጣ እንደማለት ሲሆን፤ 2ኛው ደግሞ በዓል ደመቅ ብሎ ከሌላው ጊዜ መታየት አለበት። እዚህ አካባቢ ያለውም ሰው ይሁን ከሌላ ቦታ የሚመጣው ሰው በሚያየው ነገር ተደስቶና ረክቶ መሄድ ስላለበት ነው። ስትል ወጣት ሀባቢ ሸህ መሀመድአሚን ጋር በቀን 07/03/2011 ዓ.ም ባደረኩት ቃለ ምልልስ ለማረጋገጥ ችያለሁ።

---

[18]ከአባ አረቡ የሚገኝ ሚኑዳ/ክፍያ/

[20] ከአቶ ጁነዲን ከድር ጋር በቀን 07/03/11 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተደኘ መረጃ

[20]በ ቀን 08/03/2011 ዓ.ም ከአቶ አንዋር ሁሴን በተገኘ መረጃ

4.2..1.2 ***የሥርዐት ክዋኔው ዋዜማ***

የስርዐት ክዋኔው ዋዜማ ህዳር 8 እና 9/ 2011 ዓ.ም የሚጀምርሲሆን፤ ዋናው የመውሊድ ከብረበዓል ከመጀመሩ በፊት የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችን አካቶ የያዘ ነው። ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ቀናት ከዋናው የበዓል ቀን ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ማለት ነው። በአካባቢው ማህበረሰብ የሚከበሩ የዋዜማ (የዋናው በዓል ቅበላ) ስነስርዐት ነው። በዚህ ጥናት እነዚህ ክንዋኔዎች ለአቀራረብ እንዲያመች ሲባል በወንዶች የሚከበረው ስርዐተ ክዋኔ ዋዜማ እና በሴቶች የሚከበር የሥርአተ ክዋኔው ዋዜማ ዝግጅት በሚሉ ሁለት ዋና ዋና ሁነቶች ተከፋፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

***ሀ. በወንዶች የሚከበር ስርዐተ ክዋኔ ዋዜማ***

ከላይ በቅድመ ዝግጅት የወንዶች ሚና በሚለው ርዕስ ስር እንደገለፅኩት፤ ‹‹የዋዜማ በዓሉ አፈፃፀም ተጀምሮ የሚጠናቀቀው አባ ጃርሳ ተብለው በሚጠሩት ሰዎች ነው። ይህ የዋዜማ ስነስርዓት ከዋናው በዓል ቀደም ብሎ መከበሩ በአንድም በሌላ ፋይዳው የጎላ ነው›› ሲሉ አቶ አንዋር ሁሴን (ደርጋ) በቀን 07/03/11 ዓ.ምጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ አክለውም፤‹‹በመጀመሪያ ይህ በቀን ስምንት የሚከበረው በዓል የወንዶች መውሊድ ይባላል። እንዲህ ስልሽ ወንዶች ብቻ ተሰባስበው የሚያከብሩት ነው ማለቴ ሳይሆን፤ ዕለቱ የአካባቢ መውሊድ ሲባል ለዚህ ቀን የሚሆነውን እርድ የሚዘጋጁት ወንዶች ናቸው ማለቴ ነው። የሚያዘጋጁትም በአባ ጀርሳና በተመረጡ ሰዎች በኩል እያንዳንዱ ሰው (ከን ኒያ ኢሳ) በራሱ የነየታውን (የወሰነውን) ያህል ገንዘብ ይሰጣል፤ የፈለገም ሙሉ በሬውን ገዝቶ ማስገባት ይችላል። እንደ ኒያው ነው። ስለዚህ ከላይ በኃላፊነት የተቀመጡት ሰዎች ይህንን አቀናጅተው የአካባቢው መውሊድ በተሳካ ሁኔታ እንዲከበር ያደርጋሉ።››

አቶ አንዋር ሁሴን አያይዘውም፤ ‹‹በዚህ ዕለት የሴቶች ድርሻም የላቀ ነው። እንደልኩሽ የወንዶች መውሊድ ተባለ እንጂ የማብሰሉን፣ እንጀራ የማዘጋጀት፤ ቡና የማፍላት ድርሻ የሴቶች ነው። እነዚህም ሴቶች ልክ ወንዶች ለበሬ የሚሆነውን ገንዘብ በራሳቸው ኒያ መሰረት እንደሚሰጡት ሴቶችም እንጀራውን የነየቱትን ያህል የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሴቶች ከቤታቸው ጋግረው ያመጣሉ።በዕለቱ የሚያስፈልጉ እንደ ቡና፣ ጫት፣ እጣን፣ ስኳር፣ የመሳሰሉትን የሚገዙት በኮሚቴነት የተቀመጡት ሰዎች ከበሬ መግዣ የቀረውን ገንዘብ ለነዚህ አይነት ወጪዎች ያውሉታል።››

‹‹ቀደም ብሎ ማክበሩ ፋይዳው ምንድነው? ካልሺኝ፤ የመጀመሪያውና ዋናው ለመውሊድ ቀኑ ለምን ተመረጠ? ለሚለው ጥያቄ፡- ቀኑ የተመረጠበት ምክንያት ረቢያ አወል 12 የሚከበረውን (ዋናውን መውሊድ) ቀን ለማክበር ምዕመናን ከተለያዩ ሩቅ ቦታዎች ይመጣሉ። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ለማብላት፤ ለመቀበል ሲባል የሚደረግ ነው። በዋናው እለት ይህ ፕሮግራም ይደረግ ቢባል የሰው ቁጥር እጅግ ብዙ ስለሆነ ለማብላት አስቸጋሪ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ቀኑ የተመረጠው። የወንዶች መውሊድ የተባለበትም ጉዳዩን ከመጠንሰስ አንስቶ እስከ ፍፃሜው ወንዶች እጃቸው ስላለበት ነው›› ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

በዚህም ዕለት በምልከታዬ እንዳረጋገጥኩት ወንዶች እንደተባለው ለእርድ የሚሆነውን ሙክት ከማዘጋጀት ባለፈ የእርድን ስርዓት ሲፈፅሙ፤ ወንዶች ለእናቶች ለመስራት እንዲመቻቸው ሲከተክቱ ተመልክቻለሁ።

***ምስል ሁለት፣ እርድ ሲካሄድ የሚያሳይ ፎቶ***



ከዚህ በተጨማሪም በግቢው ውስጥ የነበሩት ቤቶች በቂ ባለመሆናቸው በግቢ ውስጥ ከሚገኘው መስጅድ ፊት ለፊት ሽራ በመወጠር እንግዶችና የአካባቢውን ህብረተሰብ በዋዜማው ዕለት ሲያስተናግዱ ተመልክቻለሁ። ሌላው በዕለቱ የተመለከትኩት ለሴትና ለወንድ ተብሎ የተዘጋጀ ዳስም ሆነ ቤት አልተመለከትኩም። የሚመጡት ምዕማናንም ሆኑ የአካባቢው ሰዎች እንደ አመጣጣቸው ከመቀመጥ ውጭ ለወንድ ለሴት ተብሎ የተለየ ቦታ በምልከታዬ ወቅት አላስተዋልኩም። ምናልባት የተለየ ዓላማ ይኖረው ይሆን? አንድ ላይ የመቀመጣቸው ሚስጥር፤ ብዬ ለአባመጫ አባ አረቡ ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፡-

እዚህ ቦታ ላይ አብረው የተቀመጡበት ምክንያት አብዛኛው ሲመጣ ቤተሰብ በአንድነት ነው የሚመጣው፤ እና እንዳይለያዩ ከመፈለጋቸው ነው። ቤተሰብም ባይሆኑ የአካባቢ ሰዎች ይሆናሉ፤ ተያይዘው የሚመጡት እና ለዚያ ሲባል ነው አንድላይ የሚቀመጡት፤ ደግሞ ይቀመጡ እንጂ እዚህ አባ አረቡ ግቢ ገብተው ዱአ ከማድረግ

እና ከዚያራ      ውጭ ሌላ ሀሳብ ያለው ሰውም የለም። መጀመሪያ ከቤታቸው ሲመጡ የአባ አረቡ      ፍቅር እንጂ ያስገደዳቸው ለስሜት አይደለም፤ ስለዚህ ነገ ደግሞ ብታይ ከዚህ የበለጠ ነው። ሲሉ ይገልፃሉ።

በቀን 08/03/2011 ዓ.ም ከአቶ አንዋር ሁሴንና በምልከታዬ ወቅት ባረጋገጥኩት መረጃ መሰረት፤ በዚህ እለት ከመብላት መጠጣቱ በተጨማሪ እራሱን የቻለ ጊዜ ነበር።ያውም በልተው ከጨረሱ በኃላ የቡና ስነስርዓትና የጫት ቂማ ስርዐት እንዲሁም ዱአው እየቀጠለ ሄደ።በእንደህ አይነት ሁኔታ እንደቀጠለ እዚያው የሚያድሩ ሲያድሩ፤ በአካባቢው የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤታቸው በመመለስ ዕለቱን ተሰናበቱት። በዕምነቱ የሴቶችን በጋራ መቀመጥ ቢከለከልም፤ ከተሰጠኝ መረጃ እንዳስተዋልኩት ከተመጣበት ዓላማና ከመጡበት ሁኔታ አንፃር የመጡት እንግዶችም ሆኑ የአካባቢው ሰዎች ቤተሰብና የቤተሰባዊነት ስሜት በውስጣቸው ስለሚፈጠር በአቀማመጣቸው የወንድ የሴት የሚባል ቦታ እንደሌለ ተገንዝቤያለሁ።

### *ለ. በሴቶች የሚከበር ስርዐተ ክዋኔ ዋዜማ*

በሴቶች የሚከበረው ስርአተ ክዋኔ ዋዜማ አስመልክቶ ወ/ሮ መርዲያ አባሳንቢ (መስጂዳ አፋርተማ  አካባቢ የሚኖሩ) ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ቃል በቃል የተሰወደ በረቢያል አወል[21] ‹‹በቀን 9 የሚከበረው የመውሊድ ዋዜማ የሴቶች እንደሆነ ይታወቃል። የአካባቢው ሰው በደንብ ያውቀዋል። አኛም ይህን ስለምናውቅ አፋርተማ መስጅድ (መስጂዳ አፋርተማ) አካባቢ ያለን ሰዎች ትላንት በቀን 8 መጥተን፤ ከዚህ አካባቢ ሰዎች ጋር በጋራ አክብረን ተመልሰናል።ዛሬ ደግሞ የኛ ተራ ነው ያውቃሉ፤ እኛ ነን የምናበላው ትላንት እንደተመለከትሽው አርደን ሳይሆን የምናበላው፤ ይኸውልሽ የበቀሎ ዱቄት፣ ቀጭቀጫ፣ (ደቀ) አይብ ፣(ኢቶ ሰዓ) አዘጋጅተን ይዘን መጥተናል። ከዚህ የምንወስደው ድስትና ውሃ ብቻ ነው። ሌላውን  ሁሉ ይዘን ነው የመጣነው። ዛሬ የኛ የሴቶች መውሊድ በመባል ይታወቃል። መውሊዱን የምናወጣውም(መርቃ ቦቆሎቲን) በበቀሎ ገንፎ ነው። እነሱም (የአካባቢው ሰዎች ምን ይዘን እንደምንመጣና፤መች እንደምንመጣ ስለሚያውቁ ይጠብቁናል።እኛም መጥተን አብልተን ቡና አፍልተን፣ አጠጥተን ዱአ ተደራርገን ወደ ቤታችን እንመለሳለን።››

*ምስል ሦስት፣ ገንፎ ሲመገቡ የሚያሳይ ፎቶ*



[21]በእስላማዊ ቀን አቆጣጠር 3ኛ ወር

ገንፎ የሆነበት ምክንያት አለው? ለሚለው ጥያቄ ያስቀመጡት ምላሽ፡- ‹‹በዕርግጥ ወንዶች አቅማቸው ከኛ የተሻለ ስለሆነ አርደው ያበላሉ፤ እኛ ደግሞ በአቅማችን መስራት የምንችለውንና በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ ባህላዊ ምግብ ስለሆነ ማንም አይጠላውም። ተደስቶ ይበላልናል፤ ከሚል ሀሳብ የተነሳ የተጀመረና፤ በየጊዜውም ዓመት በመጣ ቁጥር የሚሠራ የምግብ አይነት ነው።›› ይሉና አያይዘው ‹‹እነሱ በቀን ስምንት ያከናወኑትን የራሳችንን ድርሻ በቀጣዩ ቀን እናድርግ ከሚል ውጭ የተለየ አላማ የለውም። ወንዶቹ የቀሙለትን አላማ ይዘን ነው የምንከተለው።›› ሲሉ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ።

ወ/ሮ መርዲያ አባሳንቢ ከ10 ጊዜ በላይ መውሊድ ለማክበር የተገኙ መሆናቸውን የገለጹልኝ እናት ሲሆኑ እዚያው በጅሬን ቀበሌ ውስጥ የቀዩ የመስጂዳ አፍርተማ አካባቢ ነዋሪ ናቸው።ለወ/ሮ መርዲያ ይህን የዋዜማ በዓል የሚያከብሩ እነማን ናቸው? ብዬ ለጠየኳቸው ምላሽ ሲሰጡ፡-

“እነማን የሚባል ነገር  የለውም። አባ አረቡን ብሎ የመጣ ሁሉ በዐሉን ያከብራል።       የተሰራውን መውሊድ ይበላል። ይሄየእከሌ ነው። ይች የአኬሌ ናት። የሚባል ልዩነት         የለም። ነይ ቡና   ጠጪ ና ቡና ጠጣ የሚባል /የምትባል የለችም። በራሱ ይመጣል፤ የመጣበትን አላማ ፈፅሞ ይሄዳል። እዚህ የመጣ ሰው ሁሉ አላማው አንድ ስለሆነ     የሚነጣጠል የለም።

እስላሙ ክርስቲያኑም በአንድ የተዘጋጀውን ምግብ ነውየሚመገቡት? ለሚለው ጥያቄዬ ምላሽ፡- ‹‹እንዲያ ማለቴ አይደለም። በእርግጥ እዚህ ሙኝ[22] /አባአረቡ/ አካባቢ ክርስቲያን የለም፤ሙስሊም ብቻ ነው ያለው። ይሁን እንጂ ወደ ከተማው አካባቢ ያሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች ይመጣሉ። እነሱም እንደዚህ በዋዜማው ዕለት ሳይሆን በዕለተ ቀኑ ነው የሚመጡት። በእርግጥ ለነእከሌ ተብሎ የሚቀመጥ ነገር የለም። የሚመገቡ ከሆነ ይሰጣቸዋል። ካልሆነ እነሱ እራሳቸው ሲመጡ ተዘጋጅተው ስለሚመጡ በምግብ ዙሪያ የሚታይ ችግር የለም። የሚመጣውም ሰው ቅድም እንዳልኩሽ የራሱን አላማ ይዞ ስለሚመጣ ያሰበውን ፈፅሞ ከመመለስ ውጭ ሌላ ጉዳይ ውስጥ አይገባም።”

ወ/ሮ መርዲያ ካሰጡኝ ሀሳብ በመነሳት በአካባቢው የሚገኙት ማህበረሰቦች ሙስሊም እንደሆኑና፤ ነገር ግን በዓሉን ለማክበር የክርስትና እምነት ተከታዮችም እንደሚመጡ ከሰጡት ሀሳብ ተገንዝቢያለሁ። ይሁን እንጂ እነዚህን የሚመጡትን ሰዎች በማሰብ የተለያዩ ምግቦች እንደማይሰራ የምግቡ አለመሰራት  ደግሞ በየትኛውም ምዕመናን ውስጥ ምንም አይነት ቅራኔ ፈጥሮ እንደማያልፍና የመጡለትን አላማ ከማስፈፀም ውጭ ምዕመናን ሌላ አላማ እንደሌላቸው፤ ከሰጡኝ ሀሳብ ለመረዳት ችያለሁ።

ከላይ የቀረቡት ሁለት ምስሎች በቀን 8 እና 9 በዋዜማው ዕለት የተወሰዱ ናቸው። ካትሪን ቤል (1997) ላይ በፎክሎር ጥናት መስክ ሰፋ ያለ ቦታ ያለውን ክብረበዓል በተመለከተ በፃፋችው መፅሐፍ ላይ አብዛኞቹ ክብረ በዓላት አንድ የሚያደርጋቸው መሰረታዊ ጉዳይ ድግስ መሆኑን ትገልፃለች።

[22]ለአካባቢው የተሰጠው ልዩ መጠሪያ ሲሆን ፤መነሻውም በአካባቢው የሚገኘው ተራራ ስያሜው በመሆኑ ነው፡፡

በዚህም ክብረ በዓል በተመሳሳይ መልኩ ድግስን ዋነኛ መሰረት አድርጎ የሚከናወን የሚበላውና የሚጠጣው ከሌለ ክዋኔው የተሟላ እንደማይሆን ልረዳ ችያለሁ።

ይህም ለምን እንደሆነ ስጠይቅ አቶ አባነጋ አባቦር የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡-

> "ይህ መውሊድ የሚከበረው ለእስልምና ታላቅ ስራ ሰርተው ያለፉትን አባ አረቡን ለማሰበና ለመዘከር ነው። ይህ ጀመዓ የተሰበሰበው ለዚሁ አላማ ነው።ከዚሁ ጎን ለጎን ሙብላቱና መጠጣቱ ዱአ መደራረጉ ዚያራ ማድረጉ የማይቀሩ ተግባሮች ናቸው። የዚህ የአካባቢው ማህበረሰብ መወሊድ በዋዜማው ዕርድ የመፈፀሙ የመሰብሰቡ ዋና አላማ በራሱ ከሩቅ የሚመጣውን ጀመዓ አብልቶ በማጥገብ በመጣው እንግዳ አዕምሮ ውስጥ ደስታን መፍጠር ነው።" (ቃለ መጠየቅ፣ አቶ አባነጋ 08/03/2011 ዓ.ም)

ይህም ማለት መወሊድ ሲታሰብ ሌሎች ክዋኔዎች ከበስተኋላው ቢኖሩም ዋነኛውና መሰረታዊ ነገር ድግሱ (የሚበለውና የሚጠጣው) ነው። በዚህ ሀሳብ ላይ ቀደም ብሎ የተጠናው የአብዱራህማን (2007) መውሊድና ምግብ ተነጣጥለው የማይታዩ ጉዳዮች መሆናቸውን ይገልፃል።እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው መሰረታዊ ጉዳዩ የኡለማ መውሊድ ቀዳሚው ተግባሩ ኡለማውን ማሰብ (መዘከር) ሲሆን በዚህ መዘከር ሂደት ውስጥ ድግስ አይቀሬ ጉዳይ ነው።

በመሆኑም በቁባ አባአረቡ መውሊድ ክብረ በአል ላይ ለመታደም የመጡትን (በዋዜማው ዕለት) የተገኙትን ወደ አምስት ሙቶ የሚሆኑ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ምዕመናን ወደ 1500 የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችን ለማስተናገድ አምስት በሬዎችና ሶስት በጎች ታርደዋል። እነዚህ ከብቶች የተገኙት ከላይ በወንዶች ሚና ስር እንደተገለፀው ከአካባቢው ወንዶች በአባ ጀርሳና በበአሉ አስተባባሪዎች አማካይነት በተሰበሰበው ብር ነው።

### 4.2.1.3 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ፣ የበዓለ ዕለቱ ሁናቴ

የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል አከባበር ክዋኔን በተመለከተ ልክ በዋዜማው ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚፈፅሙት ተግባር እንደተቀመጠው ሁሉ በዋናው በዓል እለትም እያንዳንዱ ባለድርሻ የተመደበለትን እና በራሱ የፈቀደውን ሲከወን እንደነበረ በምለክታዬ እና በዕለቱ 12/03/2011 ዓ.ም ከአባ መጫ አባአረቡ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፡-

> ..."ልክ እንደ ዋዜማው የወንዶች፣ የሴቶች፣ የወጣቶች የስራ ድርሻ እራሱን የቻለ ነው። የነሱ ስራ የሚያበቃው ምዕመናኑ ከዚህ አካባቢ ዘያረውን አጠናቀ ሲሄድ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን ተግባር ለሚፈፅሙበት ምንም አይነት ክፍያ የላቸውም። የአባ አረቡ ውዴታ ስላላቸውና ከሳቸው የሚያገኙትን ምንዳ በማሰብ ብቻ ነው። ሲሉ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል።"

ከዚሁ ሀሳብ በመነሳት የእያንዳንዱ ባለድርሻ የስራ ድርሻ /ሚና እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

በመጀመሪያ በዓለ ዕለቱ ሲባል ዋናው በዓል የሚከበርበት ቀን ሪቢያል አወል አስራ ሁለት ማለት ነው። ይኸውም በዚሁ ቀን ይጀመር እንጂ የሚጠናቀቀው በቀን 15 ነው። በነዚህ ተከታታይ 4 ቀናት ውስጥ የሚከወኑት ክዋኔዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ ልዩነታቸው የሚመጡት ምዕመናን ለማግኘት የሚፈልጉት (የሚጠይቁት) ቀደም ብለው የተሳካላቸው (የሆነላቸው) የተሳሉት ስዕለት ለማስገባት ካለው ልዩነት ውጭ የሚታዩ ልዩነቶች የሉም።

### *ሀ. በበዓለ ዕለቱ የአባቶች የስራ ድርሻ*

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር አባቶች የሚባሉት በእድሜ የገፉ እና ከወጣትነት እድሜ የዘለሉትን ይመለከታል።በዕድሜ የገፉት (ሽማግሌዎች) የሆኑት ለዱአ ተመርጠው ይቀመጣሉ። የእነዚህ ሽማግሌዎች የሥራ ድርሻም ምዕመናኑ መጥቶ ዱአ እንዲደረግለት ሲፈልግ እነሱ እንዲያደርጉለት አስፈላጊውን ግብአት አሟልቶ ከፊት ለፊታቸው በመቆም ይጠይቃል። በዚሁ መሰረት እንዲያደርጉ በተጠየቁት አይነት ዱአ ማድረግ ነው። የነሱ የሥራ ሃላፊነት ለዱአ አድራጊነትም ቀደም ብሎ ሳይሆን የሚነገራቸው፤ ሰው በራሱ ካሉት ከሚያየው ሰው እዚያው አካባቢ ከሚኖሩትም ሊሆን ይችላል። ከሌላ አካባቢ የመጡ እንደሁ በተለምዶ ለዱአ ይሆናል ብሎ ያሰበውን ሰው በመምረጥ ይህን ተግባር እንዲያከናውኑለት ምዕመኑ ይጠይቃል።

በእድሜ ትንሽ ሻል ያሉት ወይም ጠንካራ የሚባሉት ደግሞ የራሳቸውንም ሆነ ምዕመኑ ለጀባታ (ስጦታ) ያመጣው እርድ ካለ አርደው ለተሰበሰበው ህዝብ ያበላሉ።

### *ለ. በበዓለ ዕለቱ የእናቶች የስራ ደርሻ (ሚና)*

በዚህ ዕለት እናቶች ምዕመናን ከሩቅ አካባቢ እንዲሁም ከከተማው ስለሚመጡ አንዳንድ ለማብሰያ እንዲሁም ቡና ለማፍላት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ተሸክመው ስለማይመጡ፤ እነዚህን ነገሮች በማምጣት ይተባበራቸዋል። ይህን የሚያደርጉት በአካባቢው የሚኖሩት እናቶች ሲሆኑ፤ እቃውን ካገኙ በኃላ ስራውን የሚያከናወኑት ግን በዓሉን ለማክበር የመጡት እናቶች ናቸው።

ሌላው የእናቶች ድርሻ አባቶችና ሽማግሌዎች ጫት በሚቅሙበት ወቅት ቡና ማፍላት፤ የእጣን እሳት መስጠት፤ ዉሃየመሳሰሉትን የሚያቀርቡ እናቶች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው እናቶች ቦታ ያጡ ምዕመናን ወደ የቤታቸው በመውሰድ ሲካድሙ ያሳድሯቸዋል። በአጠቃላይ የእናቶች ተግባር የሚያበቃው የመውሊድ የፍፃሜው ዕለት ደርሶ ምዕመናን ወደየቤታቸው ከተመለሱ በኃላ ነው እንጂ ከዚያ በፊት ምንም አይነት የዕረፍት ጊዜ አይታይባቸውም።

### *ሐ. በበአለ ዕለቱ ወጣቶች ያላቸው የሥራ ደርሻ (ሚና)*

የወጣቶች ምድብ ወንዶቹንም ሴቶቹንም በስሩ ይይዛል። በመጀመሪያ ወንዶቹ በስራ ድርሻቸው በዕለቱ አባቶች ያረዱትን እርድ እናቶች ካዘጋጁት በኃላ ገበታ ያስተናግዳሉ። ውሃ ለመጠጥም ይሁን ለስራ ያመላልሳሉ። ቦታ

ለቸገረው ሁኔታዎችን አመቻችተው ማረፍያ እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች የአካባቢውን ሰላም በማስጠበቅ ረገድ ትልቁን ደርሻ ይወስዳሉ።ለምሳሌ ምዕመናን በሌቦች እንዳይዘረፉ ቁጭ ብለው ይጠብቃሉ።[23]

የሴቶችን (የልጃገረዶቹን) ሚና ስንመለከት ከእናታቸው ጎን በመሰለፍ እገዛ ያደርጋሉ። ይኸውም ቡና በመቁላት በመውቀጥ በማፍለት ስራ ላይ በይበልጥ ይሳተፋሉ። እናቶቻቸው ወደ ቤት ለሚወስዷቸውን እንግዶች ምግብና ቡና በማዘጋጀት ያስተናግዳሉ።ከዚህ በተጨማሪ በዕለቱ መዕመናን የሚፈልጉትን እንደ ምግብ፣ዉሃ፣ ቡና፣ እጣን፣ ስኳር፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን በገንዘብ ሴቶቹ የራሳቸውን ጊዜያዊ ሱቅ በማዘጋጀት ሲያቀርቡ፤ወንዶቹ ደግሞ ጫት ዉሃና የመሳሰሉትን በማቅረብ መዕመናኑን እየረዱ የራሳቸውን የሥራ ዘርፍ ከፍተው ሲሰሩ ከቀን 12-15 ባለው የምልከታ ጊዜዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። [24]

### 4.2.2 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርዐተ ክዋኔ አካሄድ

በፎክሎር ጥናት ዘርፍ ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ክብረ በዓል ራሳቸውንየቻሉተደግጋመው የሚመጡ ስርአቶች አሉት። እነዚህስርአቶችም የራሳቸውን ማዕቀፍ መሰረት አድርገውየሚከወኑና መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚጠናቀቁ የሚታወቅ ነው።

በቀጥታ ወደ ክዋኔው ቅደም ተከተል ከመግባቴ በፊት የቁባ አባ አረቡ  የመውሊድ በዓል ስርዐተ ክዋኔ በሁለት ጎራ ተከፍሎ የተካሄደ ነው። የመጀመሪያው በአከባቢው ነዋሪዎችና ለጅማ ቅርብ ከሆኑ ወረዳዎች በመጡ ምዕመናን የተሞላ ሲሆን፤ የከበራው ስፍራ በቁባ አባ አረቡ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ባሉት ቤቶችና በጊቢ ውስጥ ባሉት ሜዳዎች (ክፍት ቦታዎች)ዳስ በመስራት ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ከቁባው አጥር ውጪ ለቁባው አቅራቢያ በሆነ አንድ ትልቅ ዛፍ ስር በመሰባሰብ ሲያከብሩ አሰተውያለው። እነዚህ እነማን ናቸው? ለምን እዚህ ተቀመጡ?ለምን ከሌሎች ጋር በአድነት አልተቀመጡም? የተለየ አላማ አላቸውን?ለሚሉት ጥያቄዎች፤ የአከባቢ ነዋሪ ለሆኑትና በዓሉን ለማክበር በቦታው ለተገኙት ለወ/ሮ ድልቢ ሞጋ በቀን 12/03/11 ዓ.ም ላደረኩላቸው ቃለ መጠየቅ የሰጡኝ ምላሽ ቃለ በቃል ፡-

---

[23] በ ቀን 12/03/01 ዓ.ም ከአባ መጫ አባ አረቡ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅና በምልከታ የተገኘ ።
[24]ከቀን12-15 ባደረኩት ምልከታ እና በቀን 12/03/11 ከአቶ አንዋርሁሴን ጋር በተደረገ ቃለ መጠየቅ የተገኘ።

"በርግጥ የተለየ ዓላማ የላቸውም። መውሊድ ለማክበር ነው የመጡት፤ ገሪባዎች[25] ናቸው። ከድሬ ሸከናሁሴን (አርሲ)ነው የመጡት፤እና እነርሱ ከራሳቸው ውጪ እንደራሳቸውየሚሆንላቸው አያገኙም።በጣም ጥብቅ ናቸው።በዕምነቱም፤ የተናገሩትም ሆነ የረገሙ እንደሆን መሬት ጠብ አይልም።በጣም ይፈራሉም፤ ይከበራሉም።ለዚህ ነው የማይቀላቀሉት። እነሱን ያለ እንደምታይው እንሱን መጥቶ ዘይሮ ዱአውን ተቀብሎ ነዝር ካለውም አስገብቶ የሚፈልገው ነገር ካለ ዱአ ተቀብሎ ይሄዳል። ዱአቸው እንዳልኩሽ መሬት አይወድቅም።" ስሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ከዚህ ሃሳብ በመነሳት በምልከታዬ ወቅት የማገኛቸውን ልዩነት ባስፈላጊው መልኩ ከዋናው ክፍል ጋር በማያያዝ ተተንትኖ ቀርቦዋል።

### 4.2..2..1 **ዝያራ**

በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ከበራ ዕለት በመጀመሪያ የሚከወነው ሁነት ዚያራ[25] ይባላል።ይህ ሁነት የሚከወነው ከዋናው ከበራ ዕለት ቀደም ብሎ (በሙቀደማ) ዋዜማ እለት ጀምሮ ቢሆንም በዋናነት ግን በ12/03/11 ዓ.ም በርካታ የበዓሉ ታዳሚዎች "ዚያራ" ሲያካሄዱ ተመልክቻለሁ።ይህ የሆነበት ምክንያት ዋናው የከበራ ቀን ተደርጎ የሚወሰደው የሙቀደማ (ዋዜማ ለሊት) በመሆኑ አብዛኞች እንግዶችየሚገቡት በዚሁ እለት በመሆኑ ነው።

በዚህ ክብረበዓል የዚህ ሁነት አላማ ደግሞ ለዓመት ያህል በልባቸው ይዘዋቸው የቆዩትን(አባአረቡን) የልብ ወዳጃቸውን መቃብራቸውን መዘየር (ሰላም ማለት)በቅርብ ወይም በአካል አግኝተው እንዳናገሯቸው ያህል የሚሰማቸውንስሜት እደሚፈጥርላቸው ነግረውኛል።

በምልከታዬም ወቅት ይህን ሁነት እንዳሰተዋልኩት፤የዚያራው ቦታ (የአባ አረቡ መቃብር)ኀላ ባለ ነጭ ቀለም ተውቦ ከሌሎቸ ቤቶች ተለይቶ ጎልቶ ይታያል።

***ምስል አራት፡ የቁባ (የአባ አረቡ) መቃብር ፎቶ***



ከቤቱ ውጪ ያለው ቦታ በብዙ ወንድና ሴት ምዕመናን ተከቧል። ለመዘየር የፈለገ ሰው በእነዚህን ሰዎች ግፊያ መሀል አልፌ ከበረንዳ ስደርስ ከአባ አረቡየቀብር ቤት ፊት ለፊት በረንዳ ላይ የተቀመጡ ሶስት ሰዎች አስተዋልኩ። ካሜራዬን ይዤ ሲዘይሩ  ከነበሩት ሰዎች ጋር ተከትዬ ልገባ ስል በኦሮሚኛ ‹‹ዋ ካኢ መሌ አኩማ ከናን ሂን ሴኒን›› የሚል ድምጽ ሰማሁ። በዚህን ጊዜ እኔም ቦርሳዬን ዳበስ አርጌ አስር ብር ከፊት ለፊታቸው ከተነጠፈው ብጣቂ ጨርቅ ላይ ጣል አርጌ ሌሎች ሰዎች እነዳደረጉት ጫማዬን አውልቄ “አሰላሙ አለኩም ወረሙቱላሂ ወበረካቱ” ብዬ ከገባሁ በኃላ እንደ ሌሎቹ ምዕመናን በዝምታ ነገሮችን መከታተል ጀመርኩ።

ከኔ ቀደም ብለው የገቡት ሁለት ባልና ሚስት ለሰላት ሰጁድ እንደሚወረድ በጉልበታቸው ተንበርክከው የሚያለቅሱት እንጂ ድምጻቸው ምን እንደሚሉ አይሰማም። በኋላም ቀና ብለው ሁለት እጃቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ከለመኑ በኃላ ሁለቱን እጃቸውን ስመው እንደገና ሰጁድ ወረዱ። ወንዱ እንዲሁ ሲነሳ ሴትዋ ግን ትንሽ ከመቃብሩ አፈር ስትቀነጥር አየኋት። የቀነጠረችውን አፈር ደበቅ አድረጋ በሻርብ አስራ ወጥታ ቀድመው ወደያዙት ቦታ ተቀመጡ። የያዘችው አፈር ምን እንደሆነና ምን ጠቀሜታ እዳለው ለጠየኳት ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጠችኝ፡-

> በርግጥ አንች ስለማታውቂ ነው እንጅ የምነግርሽ አይነገርም ምስጥር ነው።ይሄ ምን መሰለሽ መድሃኒት ነው፤ በጥብጠሽ በትጠጪ ሆድሽ ውስጥ ያለውን በሽታ አጥቦ ያወጣልሻል። ለዚህ ነው ደብቄ የያዝኩት። አንቺ ደግሞ አታውቂም ብዬ ነው የነገርኩሽ። በማለት ምላሸዋን ሰጥታለች ።

ሌሎች ወደ ክፍሉ ከገቡ በኃላ ሁሉም በራሳቸው መንገድ ከተሰላመቷቸው በኋላ እንደ የመጡበትጉዳይ ተሳክቶላቸው ከሆነ ስለት ማድረስ፤ ለወደፊት እንዲሆንላቸው ሽተው ከሆነም ጠይቀው፤ ለራሳቸው ቃል ገብተው፤ ወደየመጡበት (ወደያዙት)  ቦታ ተመልሰው ይሄዳሉ።

በምልከታዬ እንዳስተዋልኩት በዚያራ ወቅት ለማዘየር ቁጭ ያሉት ሰዎች የሚገባ የሚወጣውን በዓይን ከመከታተል ውጭ የሚሰጡትመድሃኒትም ሆነሌላ ነገር የለም። ምዕመናኑ በየራሳቸው አባ አረቡ ልክ በህይወት ኖረው እንደሚያደምጧቸው ያህል አልቅሰው ነግረው (አድርሰው) ከክፍሉ ሲወጡ አስተውያለሁ።

ይህ ዚያራ አባ አረቡ በሕይወት በነበሩበት ወቅት  የማይከናወን እንደሆነ እና መከናውን የጀመረውም አባአረቡ ሕይወታቸው ካለፈ በኋላ ምዕመናኑ ለእሳቸው ክብር በህይወት እንዳሉ በመቁጠር ወደ በመቃብራቸው እየመጡ እየዘየሩና የሚፈልገውን ነገር እየጠየቁእንደሚያገኙና እሳቸውን ጠይቆ ማንም ሰው እንደማያፍር፣ የተቸገረ በየትኛውም መንገድ ይሁን ጠይቆ እንደማያጣ ከአባመጫ አባአረቡጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ።

አባ አረቡ ካለፉ በኃላ ቦታውን በመያዝ የመጀሪያው ካዳሚ አባጆርጋ ሲሆኑ በሳቸው ጊዜ የጀመረው እስካሁን የማዘየሩ ተግባር እየቀጠለ እንደመጣ፤ በአሁነ ሰዓት ወና ካደሚበመሆን የሚታወቁት አባ መጫ አባ አረቡ እንዲህ ሲሉ ሃሳበቸውን ይገልፃሉ፡-

“ለእኔ አባ አረቡ ወላጅ አባቴ አደሉም። ገነር ግን እኔ ሁሉ ነገር ይቅርብኝ ብዬ እዚህ እሳቸው ጋር መኖር ከጀመረኩ ቀይቻለሁ። ለዚህ ነው የአባቴ ስም በእሳቸው ስም የሚጠራው። በሌላ ስም መጠራትም አልፈልግም፤ የለኝምም።” ሲሉ ገልፀውልኛል።

ቀደም ብሎ በአብዱራህማን(2007)በተጠናው ‹‹የነሼህ ዳንግላ የሞሊድ በዓል አከባበር ስርዓት›› ላይ አብዱራህማንእንዳመለከቱት የሼሆቹን መቃብር የመዘየር ሂደት አይከወንም። ዚያራው ይካሄድ የነበረው ለሸሆዎቹ ልጆች ነበር።አጥኝው ይህንን በተመለከተ “ሸሆቹ ይህንን የመቃብር ዚያራ ያወግዙ ስለነበረ ፈጣሪ የልባቸውን መሻት አይቶ እዚህ እንዳይቀበሩ አደረገ” ሲል የራሱን ግምት አስቀምጧል።

በዚህ እንደተቃኘው ደግሞ፤ የመውሊድ ከበራ ሂደት አንዱ የሆነው ዚያራ ኡለሞቹ በሕይወት ኖሩም አልኖሩም ምዕመናኑ ለነሱ ካለው ቦታና ክብር የተነሳ በሚያገኟቸው ቦታ ይቀበሩም አይቀበሩ በምዕመናኑ ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ተሰጥቷቸው ስላሉ ለዚያራ በተመቻቸላቸው ቦታ ሁሉ እንደሚሄዱ ይህ ጥናት ደርሶበታል።

*ምስል አምስት፡ምእመናን ዚያራ ሲከውኑ የሚያሳይ ፎቶ*



በዚያራ ወቅት ያገኘኋቸው ምዕመናን በቃለ መጠየቅ ያገኘሁትን መረጃ እንደሚከተለው አቅርብያለሁ፡-

ለዚያራ በቁባ ውስጥ ከተገናኘኋቸው ምዕመናን ጋር በነበረኝ ቆይታም፤ የአባ አረቡ ስራ በረካ[26] እነሱንም እንዲደርሳቸው እንደሚፈልጉ ለመረዳት ችያለሁ። በዚህ ሂደት በአጠቃላይ ምልከታዬ ለማስተዋል እንደቻልኩት የመጀመሪያው የአላህን ትልቅነት በመመስከር የአላህን ሰላምና ራህመት በሳቸው ላይ እንድወርድ መመኘት (መለመንን) የሚገልጹ ሲሆኑ፤ ሁለተኛው መልክ ደግሞ የአባ አረቡን ፀጋ (በረከት) እንዲያገኙ የሚገልፅ ይዘት ያላቸውን ተግባሮች መሆናቸውን ለማስተዋል ችያለሁ። ከዚህ የዚያራ ሁነት ሁለተኛው ደግሞ ዱአው (በክበረ በዓሉ ከዚያራው ቀጥሎ የሚመጣው ሁነት) ከመጀመሩ በፊት ከሩቅ የመጡ ምዕመናንና ዘመዳማቾች እርስ በእርስ የሚፈፅሙት ነው።ይህ ሒደት ሲከናወን ምንም አይነት ቅደመ ሁኔታ የማይጠይቅና ዱአው እስኪጀመር ድረስ የሚዘልቅ ነው። በክዋኔውም ምዕመናኑ በተለይ ለትላልቅ ሼሆች ቦታ በመስጠት ቅድሚያ  እየሰጡ የሚዘያየሩበትና የሚተዋወቁበት ነው። ይህ የሆነበትን ምክንያት የመውሊዱ ኮሚቴሃላፊ ከሆኑት አባቢያ አባቦሰን ጋር ባደረግኩት ቃለ ምልልስ የሚከተለውን ምላሽ ሠጡኝ፦

> ትላልቅ ሸሆች ዱአቶች ስለሆኑ ምዕመናን ለነርሱ ትልቅ ክብርና ቦታ አለው።ለዚህ ሲል ነው እንሱን የሚያከብረው፤ ከዚህ በተጨማሪም እንደሀገራችን በሕል ሽማግሌ ትልቅ ክብር አለው። ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

በዚህ የዚያራ ሂደት ምልከታዬ ለማስተዋል እንደቻልኩት፤ከአካባቢው ሰዎች በተጨማሪም በክብረበአሉ ለይ ተሳታፊ የነበሩትና  ከተለያዩ  ቦታች (ከሊሙ ሻይ፣ ከአትናጎ፣ ከሰኮሩ፣ ከሰርቦ፣ ከዴዶ፣ከሰቃ፣ ከአጋሮ፣ከቶባና ከበደሌ) የመጡ እንግዶች (በሁለቱም ፆታዎች ከወጣቶች እስከ አዛውንቶችየአባ አረቡን ቀብር ከመዘየር ባለፈ እርስ በእርስ እንዲሁም ከበዓሉ ተሳታፊዎች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ሰላምታ ሲለዋወጡ አስተውያለሁ።

ይህም ሂደት በአባመጫ  አባአረቡ ከተገለፁልኝ የበዓሉ ክንዋኔዎች ዋና ዓላማዎች መካከል አንዱ የሆነውን የአባ አረቡን ቀብር (ቁባ) ከመዘየር ጎን ለጎን ምዕመናኑንለማገናኘትና እርስ በርስ ለማስተዋወቅ ያለውን ሚና በተግባር ለማረጋገጥ ችያለሁ።

ይህ ሁነት አዲስ እንግዶች በገቡ ቁጥር በዚህ መልኩ እየተከናወነ እስከ ዱአ(ምርቃት)ጅማሬ ይቀጥላል። በእርግጥ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ "ዚያራ" እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ አዲስ እንግዶች በመጡ ቁጥር የሚቀይ ክንውን ነው።

ነገር ግን አጠቃላይ ከክዋኔው ሂደት ስንመለከትቀዳሚ የሆነ ሁነት ነው ማለት ይቻላል።  በሁለተኛው ጎራ የተቀመጠው የስርአተ ክዋኔ አካሄድ ልዩነት ሲኖረው የሚገለፅ መሆኑን በተቀመጠው መሰረት በዚያራው ላይ የተገኘው ልዩነት የመጀመሪያው ቡድን የአባ አረቡን መቃብር መዘየርና ታላላቅ ሽማግሌዎችን መዘየር የመጀመሪው ተግባራቸው እንደሆነ ያስተዋልኩ ሲሆን፤ በሁለተኛው ቡድን በነበረኝ ምልከታዬ የአባ አረቡን መቃብር በቦታው ተግኝተው ሲዘይሩ አይታዩም። የራሳቸው የሆኑ በእድሜ ገፋ ያሉ በድሬ ሸከና ሁሴን አላማ(ባላ

---

[26]ከአባ አረቡ የሚገኘው በረከት ለነሱም ይደርሳቸው ዘንድ መሻታቸውን ያሳያል፡፡

ያለው እንጨት) በአንገታቸው እና በፀጉራቸው በተለያዩ ጨሌዎች ያጌጡ አባት በመሐከላቸው ቁጭ በማለት ሲዘየሩ ተመልክቻለሁ። በዚህ ክፍል መግቢያ ላይም ለወ/ሮ ድልቢ ሞጋ ላነሳሁላቸው ጥያቄ የተከበሩና የተፈሩ ሰው እንደሆኑ በሰጡኝ ምላሽ መሰረትም፤ ራሳቸውን ችለው ለብቻቸው እንዲቀመጡ አስችሏቸዋል። በ12/03/11 ለኚህ አባት ስሞትን ማን ልበል? ከየት ነው የመጡት? የሚል ጥያቄ አንስቼላቸው፤ ‹‹ኑ ዳላ ሸከና ሁሴኒ›› ሲሉ ‹‹የመጣሁትም ከአርሲ ነው›› ካሉኝ በኋላ ‹‹ኑ ሙጉቲ ሂን በርባኑ ነጋዴ ረቢቲ ነራ ዴሚ›› በማለት ሌሎች ጥያቄዎችን እንዳነሳለቸው ፍቃደኛ ስላልሆኑ ልጠይቃቸው አልቻልኩም።

ከዚህ ንግግራቸው "ኑ ዳለ ሸከና ሁሴኒቲ" (እኛ የሸከና ሁሴን ትሩፋት ነን) ‹‹ነጋዴ ረቢቲ›› (ለፈጣሪያችን ስንል የምንኖር፤ ለምድራዊ ነገር የማንጨነቅ) ለማለት እንደፈለጉ ተገንዝቢያለሁ። ለራሳቸው ትልቅ ቦታ እንደሰጡም ለመረዳት ችያለሁ። እንዳሉትም አባአረቡን ለመዘየር ብቻ ሳይሆን በየቦታው የፈጣሪያቸውን - የሸከና ሁሴንን - ስም በመጥራት ለሳቸው ሲሉ የሚኖሩ መሆናቸውን እንድገነዘብ አስችሎኛል።

4.2..2..2 **ዱአ (ምርቃት)**

የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ከበራ እለት ከዚያራ በመቀጠል የሚከወነው ሁነት ዱአ በመባል ይጠራል።ይህ ሁነት የክብረ በዓሉ (መውሊዱ) ዋነኛ ክፍል ነው።ሁነቱ የሚጀምረው በሙቀደማ(ዋዜማ) ምሽት ከኢሻ ሰላት(የምሽት ስግደት) ከተፈጸመ በኋላ ሲሆን ቀኑን ሙሉ ወደ ከበራው ሲገባ የዋለው እንግዳ ቀድሞ ተሰርቶ በነበረው የእንግዳ ማረፊያና እያንዳንዱ ቡድን እራሱ ባዘጋጀው ማረፊያ ስፍራ ከታደመ በኋላ ነው።ይሁን እንጂ ይህ ሒደት ሁሌም በምሽት ሳይሆን ቀን መጥተው በቀን የሚመለሱት ይህንኑ ተግባር ባላቸው ጊዜ ይፈጽሙታል።በዚህ ሁነት ከሚከወኑት ዋና ዋና ሂደቶች መካከል የመጀመሪያው በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ ያሉት ምእመናን ቡድን ሰርተው በመቀመጥና የጫት እደላውን በመጠባበቅ ነው።እነዚህ የጫት እደላውን የሚያካሂዱ አባቶች (አዛውንቶች)የሚመረጡት በየቡድኑ ካሉት ስብስብ በእድሜ በለጥ ያሉትን አባላቱ ራሳቸውይመርጧቸዋል። የዚህ የቡድን ክዋኔ አላማም ጸሎትና ተለማምኖ ነው።

በመቀጠልም ከየቡድኑ በእድሜ ብልጫ ያላቸው አባቶች ከፊት ለፊታቸው ካሉት ምእመናን ያስቀመጡትን ጫት በማንሳት "ቢስሚላህ አልሀምዱሊላህ ወሰላት ወሰላም አላ ረሱሊላህ" ሲሉ፤ የተሰበሰቡት ምእመናን በጋራ በመሆን "ሰለላህ አለሂ ወሰለም" በማለት በጋራ ይመልሳሉ።ይህ የዱአ ስርዓት በሚከወንበት ሰአት ለዱአ የሚሆኑ (ጫት፣እጣን፣ነድ) የመሳሰሉትን የተሰበሰቡት ምእመናን የነየቱትንና የያዙትን የቡድን መሪ(ዱአ አድራጊ) ተደርገው ለቡድኑ ለተመረጡት አባት(አዛውንት) ከፊት ለፊታቸው በመቀም ጎንበስብሎ(ላ) እጃቸውን ስሞ(ማ)ያስቀምጣል (ታስቀምጣለች)። ካስቀመጡ በኋላ እንደየተራቸው ዱአ ይደረግላቸዋል። በዱአው ክዋኔ ወቅትም ተረኛ የሆነው ሰው ወደፊት ምን ማግኘት እንደሚፈልግና አሁን የደረሰበት ችግር ካለም ከችግሩ የሚላቀቅበት መንገድ ይፈለግለት ዘንድ በመቀም እያለቀሰ (እያስተዛዘነ) ይናገራል።

ከአቶ አንዋር ሁሴን (ደርጋ)በእለቱ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ። ዱኣ በእምነቱ ይህ ስርኣት በሁለት መንገድ ይፈጸማል።አንደኛው በግል የሚፈጸም ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በቡድን የሚፈጸም ነው።እንደ ሸህ መህመድ አሚን አብዱል ዋሂድ ገለጻ ከሆነ ኡለማ መውሊድ ላይ የሚደረገው የዱዓ ክዋኔ ሁለቱንም አይነት የያዘ ነው። የዚህ ምክንያት ደግሞ በመጀመሪያ ምእእመኑ በራሱና በአባ አረቡ መካከል ብቻ ግንኙነቱንበማድረግ፤አባ አረቡ ለፈጣሪ አማላጅ አንዲሆኑለት ችግሩን (የፈለገውን) ነገር የሚጠይቅበትና ዱኣ የሚያደረግበት ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ መውሊዱ በራሱ የማሰባሰብ ሰዎችን የማገናኘት ባህሪ ስላለው ፤ሰዎች በአንድ ቦታ ለአንድ አላማ ተገናኝተው የተለያዩ ሀጃዎቻቸው እንዲወጣ በጋራ ዱአ የሚያደረጉበት ነው።

*ምስል ሰድስት፡ ጫት ሲቃም የሚያሳይ ፎቶ*



በክበራው ወቅት በምልከታዬ ለማስተዋል እንደቻልኩትም የዱአው ክዋኔ በሚካሄድበት ወቅት በአሉን ለመታደም የመጣው ምእመናን ቀድመው በነበሩት ቤቶችና ለበአሉ ማክበሪያ ባዘጋጁት ትናንሽ ዳሶች ውስጥ በክብ በክብ እንደ አመጣጣቸው ብሎም የቤተሰብ አባላት እንደየፍላጎታቸው (ከአምስት፣ ከስድስት፣ ከአስር ሊበልጥም ይችላል) ክብ ሰርተው እግራቸውን አጣጥፈው (አጣምረው) ይቀመጣሉ። በእየአንዳንዱ ቡድን አባላት ውስጥ በታላቅነታቸው የሁሉንም ፈቃድ ባገኙ አንድ ግለሰብ ፊት የተዘጋጀው ጫት ይቀርባል።እኚህ ሰው የዱአው ክዋኔ በየአባላቱ ዘንድ ደርሶ ፍጻሜውን እስኪያገኝ ድረስ ለቡድኑ አባላት እንደ አስፈላጊነቱ እየመጠኑ ጫት የማደል

ሀላፊነት አለባቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኝ አባል የጫት ቀንበጥ እንደፈለገ አያነሳም (አይወስድም)። ሲያስፈልገው እንዳስፈለገው የሚያመላክት እንቅስቃሴ (እጁን በማሻሸት) ሲያሳይ የቡድኑ መሪ “ጀባ” ይለዋል። አባሉም “መርሀባ” ይላል። ከዚህ ሌላ የቡድኑ አባል ጫት ካስፈለገው ፍለጎቱን ለመግለጽ “በማጨብጨብ” ወይም “አጀብ” በማለት የቡድኑ መሪ እንዲያየው ያደርጋል።ሌሎች ቀሪዎቹ አባላትም ‹‹አጀብ፣ አጀብ›› በማለት ድምጻቸውን አንድ በማድረግ ይቀባበላሉ።ወዲያውኑ የቡድኑ መሪ ይህን ምልክት ላሳየው “አብሸር” በማለት የጫት ዘለላውን ሁለት እጆቹ ላይ ያስቀምጣል።የቡድኑ አባልም ጮክ ባለ ድምጽ “መርሀባ” ይላል። የቡድኑንም መሪ ይዘይራል(እጅ ይስማል)።ይህ የቡድን ክዋኔ ለምዕመናን  ማረፊያ ቀድመው በተዘጋጁ ስድስት ቤቶች፤ በቤቶቹ በረንዳ፣በግቢው ውስጥ በተሰሩት ትናንሽ ዳሶች እና መስጂዱ በረንዳ በቡድን በቡድን ይከናወናል።

በዚህ ክበረ በዓል እምነቱ እንደሚፈቅደው ለሴቶች እና ለወንዶች ተብሎ የተዘጋጀ ስፍራ የሌለው ሲሆን፤በዓሉን ለማክበር የሚመጡ ምዕመናን እንደ አመጣጣቸውና እንዲሚመቻቸው ሁኔታ ቦታ በመያዝ ከላይ በገለፅኩት ክዋኔ በተመሳሳይ መልክ ይሳተፋሉ። በዚህ ሁነት /ክዋኔ/ ላይ የቦታ አያያዝን አስመልክቶ እከሌ እዚህ እከሌ እዚያ የሚባል ምደባ የለውም። ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደገልፅኩት አባ ጃርሳ (የሀገር ሽማግሌ የሆኑት) አባቶች ተጠርተው ለምርቃት ይቀመጣሉ።እነዚህ የሚታወቁና በተደጋጋሚ በዓሉን ለማክበር የሚገኙ በመሆናቸው በቤት ውስጥ እስከ አምስተኛው ቀን ድረስ ሊቆዩ ይችላሉ። ከዚህ ውጭ ዘግይቶ የገባው ከግቢ ውጭ የአከባቢው ነዋሪ የሆኑት ሰዎች ቤት ሄዶ ሊያድር ይችላል፤ ነገር ግን የሁነቱ ክዋኔ የቦታ ለውጥ ካልሆነ በቀር ከግቢ ውጪም ሆነ በግቢው ውስጥ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው። ነገር ግን የአቀማመጣቸው ሁኔታ በአንድ ድንኳን ቦታ አለመሆን በአንድ መሪ እና በተመሳሳይ ካዳሚዎች[27]እንዳይመራ አድርገውታል።ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ከአቶ አንዋር ሁሴን ጋር በዕለቱ በደረገቃል መጠይቅ ምላሽ፡-

> ……….ቀደም ብዬ የነገርኩሽን ታስታውሺው ከሆነ በአንድነት የሚከወነው የከበራ ስርዐት በዋዜማው እለት አብቅቷል። ዛሬ እና ከዛሬ በኋላ ግን ብዙ ምዕመናን ስለሆኑ በዓሉን ለማክበር የሚመጡት፤ አንድ ዳስ
>
> ሰርተሽ ማስተናገድ ይከብዳል። በዚህ ምክንያት ሁሉም እራሱን አስተናግዶ ማለት እንደምትመለከችውቤቶቹን ቀድሞ የያዘ በቤት ውስጥ፣ ያላገኘው ደግሞ የራሱን  ሸራ በመወጠር ጉዳዩን ፈፅሞ ወደ ቤቱ ይመለሳል።

---

[27]ካዳሚ  ማለት አስተናጋጅ  ማለት ሲሆን የዱአው ክዋኔ በሚካሄድበት ወቅት ማንኛውንም  አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ያሚያሟሉ ማለት ነው። በዚህ ክዋኔ ሂደት ወቅት በእያንዳንዱ ንፁስ ቡድን ውስጥ ያሉ እናቶች፣ ወጣቶች አባላቱን የመካደም ሀላፊነት የነሱ ነው፤ ቡና የማፍላት፤ ምግብ የማዘጋጀት ፤የማቅረብ፤ውሃ የመሳሰሉት ተግባራት የሚፈፀሙት በነዚህ እናቶች ና ወጣቶች ነው፤ ስለዚህ እነዚህ የንኡስ ቡድኑ  ካዳሚዎች ናቸው።

በዚህም መሠረት ከላይ የገለፅኩት የቡድን ክዋኔ አጀማመር ሠአት ተመሳሳይ ይሁን እንጂ  የአፋፃፀም ሥርዓቱ በቡድኑ አባላት ይወሰናል። በዚህም መሰረት በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ እንዲሁም በአካባቢው ነዋሪዎች ቤት ያሉት ምእመናን በየቡድናቸው ተቀምጠው ጫት እየቃሙ የዱኣ (ጸሎት)ክዋኔን ይፈጽማሉ።ካዳሚ የሆኑ እናቶችና ወጣቶች እንደምታይው በየቡድኑ የስራ ድርሻቸው ተመሳሳይ ነው።በዚህ ሂደት ውስጥም ሴቶቹም ሆኑ ወጣት ወንዶች እንዲህ በማድረጋቸው ከሚያቀርቡት የዱኣ ማስደረጊያ (መማለጃ) በተጨማሪ ይህንን ክድሚያ በማድረጋቸው የቡድኑ መሪ ተደርገው የተመረጡት ዱኣቶች[28] ዱኣ ያደርጉላቸዋል።ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተውኛል።

ዱኣ አድራጊዎችም በሰኣቱ ካዳሚ የሆኑትን እናት ወጣት ስም በመጥራት “እንዲህ ሀድራውን ሞቅ እንዳደረግሽ ጎጆሽ ይሙቅ፤አባ አረቡ መጀን፣ ነብዩ መሀመድ መጀን[29]፣ ያሠብሽውን ይሙላልሽ” እያሉ ይመርቋታል።እሷም ሁለት እጇን ወደ መራቂው የቡድን መሪ ወደሆኑት ፊት ዘርግታ ‹‹አሚን…አሚን…ያረቢ አሚን›› ትላለች። ሌሎቹም “አቦ ያረቢ ታሲሲፍ”[30] በማለት ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ መስማማታቸውን ፊታቸውን ወደ ፈጣሪ ቀና ብለው በማየት ይሁንታቸውን በአካል እንቅስቃሴ ያሳያሉ በአንደበታቸው ይገልጻሉ።[31]

በአጠቃላይ የዱኣ ክዋኔው በቤት ውስጥ ከቤት ውጭ በዳስ ውስጥ በተቀመጡት የቡድን አባላት በየቡድኑ ከሚደረጉ ፀሎቶች በተጨማሪ መሐል መሐል ላይ ምርቃትና የመንዙማ ሁነቶችን አጠቃሎ የያዘ ነው። በመሆኑም ይህን ሒደት ሁሉም የመውሊድ ተሳታፊዎች በናፍቆት የሚጠብቁትና ሳያልፋቸው የሚከወኑ ናቸው።

በቃለምልልስ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በዚህ ዱኣ ክዋኔ በሃይማኖታዊው ስርአት ባህላዊ ኑሮአቸውና በማህበረዊ ህይወታቸው የሰመረ ግንኙነት ያላቸው፣ ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ነገር ግን  በተመሳሳይ አስተሳሰብ የሚገናኙ፣ በአንድ መንፈሳዊ ዓላማ የተሰባሰቡ የበዓሉ ዋና ተሳታፊዎች ናቸው። የማህበራዊ ችግሮቻቸውንም ሆነ የግል ብሶታቸው የመፍትሄ ቁልፍ የሚያገኙበት የሰመረ ዱኣ የሚከወንበት፣ ለዛሬው ማንነታቸውም ሆነ ለነገው ህይወታቸው ህልውና ማረጋገጫ በመሆኑ በዚህ ሁነት ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው።

---

[28]ዱአቶች፡- ዱኣ(ፀሎት)አድራጊዎች የምነቱን ህግጋት ጠንቅቀው የሚየውቁ የፈጣሪን ቋንቋ ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብሎ የሚታሰቡ በእድሜ የገፉ አባቶችን /እናቶችን/ማለት ነው የሚተካ ቃል ነው።

[29]አባ አረቡ መጀን ፤ነብዩ መሀመድ መጀን ፡-የሚሉት አባባሎች ፈጣሪ ሆይ በነሱ አማለጅነት ዱአውን ተቀባይ አድርገው ለማለት የተቀመጠ ሀሳብ ነው።

[30]አቦ ያረቢ ታስሲፋ ይህ ሀረግ በውቅቱ ሲጠቀሙ “አቦ” የሚለው ቃል ላልመና (ለማስተዛዘን )ለፈጣሪ የተባለ ቃል ነው። በአጠቃላይ አቦ ያረቢ ታሲስፍ የሚለው ሀረግ ትርጉሙ እባክህ ፈጣሪዬ አድርግላቸው /አሳካለቸው ለማለት ነው

[31]ከአቶ አንዋር ሁሴን ጋር በቀን በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

የመውሊዱ ዋና ክዋኔ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ጠንካራ የእምነት ሰንሰለትም የሚገኘው በዚህ ሁነት ውስጥ ነው። በዚህ በዱአው ክዋኔ ምርቃት ዋናው አብይ ጉዳይ ነው። ይህ ሁነት የሚከወነው በዱአው መሀል መሀል አባለቱ በሚያቀርቡት ሐሳብ ወይም "ጃባቲ"[32] ነው፤ የሚከወንበት ዋና አላማ መልካም ምኞትን ለመግለፅና የተሻለ ነገር እንዲገጥም በመመኘት ነው። ይህ ክዋኔ የሚፈፀመው በቡድን ሲሆን፤ የዚህ ክዋኔ መሪም የብድን መሪ ሆነው የተቀመጡት (Aba jarssaa) ናቸው። እኚህ መራቂ ከተሳታፊዎቹ መሐል በእድሜና በሀይማኖት እውቀታቸው የተሻሉ ናቸው ተብሎ ከፍያለ ክብር የተሰጣቸው ናቸው። ነገር ግን መራቂ ሆኖ ለመመረጥ ይህ መስፈርት ብቻ በቂ አይደለም። የተመራቂውን ሀሳብ ቶሎ የሚረዳና ሐሳብም ቶሎ የማመንጨት ብቃት ያለው መሆን ይጠበቅበታል። ይህን ሁነት በተመለከተም በክብረበዓሉ ስፍራ ለረጅም ጊዜ ተሳታፊ የሆኑት አባ ነጋ አባጎጃም በ13/03/11 ዓ.ም ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ፡-

‹‹ምርቃት (ዱአ)የመልካም ምኞት መግለጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ወደፊት እንዲሆንልሽ የምትመኘውን ነገር የምትጠይቂበት መንገድ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የራሱ የሆነ ሥነሥርዐት አለው። መራቂው ሲጀምር በሠላት ይጀምራል፤ ሲያበቃም በሠላዋት ያጠናቅቃል።ያው እንዳልኩሽ መራቂው ዱአውን በሠለዋት[33] ከጀመረ በኋላ ምኞቱን ሲገልፅ ተመራቂዎቹ ‹‹አሚን...አሚን..አሚን›› በማለት መቀበላቸውን ይገልፃሉ።እንዲህ አይነት ሁኔታ የሚቀጥለው ሀድረው እየደራ ሲሄድ ነው።›› ሲሉ ነግረውኛል።

ከዚህ በተጨማሪም በምልከታ ወቅት እንዳስተዋልኩት የመራቂውና ተመራቂው ግንኙነት ተዋረዳዊ (የሰጭና ተቀባይ) ሲሆን፤ መራቂው የሚለው ነገር ሁሉ እንደፈጸም ወይምእንዲሳካ ተመራቂዎቹ ‹‹አሚን፣ ይሁን›› በማለት ማረጋገጫ ይሰጣሉ።

የዚህን ሁነት ክዋኔ ስንመለከት በመጀመሪያ ሊመርቅ የተመረጠው ሰው አባ ጃርሳ(መራቂ) ‹‹ቢስሚላህ አልሃምዱሊላህ›› (በጌታዬ ስም እጀምራለሁ) ወሰላት ወሰላም አላ ረሱሊላህ (ሰላትና ሰላም በነብያችን ላይ ይወረድላቸው)በማለት በሰለዋት(ነብዩን በማወደስና በመዘከር)ከጀመሩ በኋላ በቀጥታ ወደ ምርቃቱ በመግባት፤ አባጀርሳ(ዱአ አድራጊ) ‹‹yaa rabbii duaiin kenyaa rabbiin nuu haa taqabbaluu›› ሲል ተመራቂዎችና እንዲሁም በዋናነት ሊያስመርቁ የቀሙ ፊት ለፊት ሁለት እጃቸውን ወደ ፊት በመዘርጋት

---

[32]ጃባቲ፡-ሁለት አይነት ነው። አንደኛው ስጦታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ነዝሪ(ስለት) የሚባለው ነው።ስጦታ፡- የሚባለው በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዕና ባለቤቱ አቅሙን አይቶ የወሰነው(የመረጠው ) ነገር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡- የሚታረድ ከብት ሊሆን ይችላል፤ ጫት፤እጣን፤ነድ፤ብር .ወዘተ...

ነዝሪ(ስለት)፡-የሚባለው ባለቤቱ ቀድሞ ቃል የገባውን ነገር የሚፈጽመው ማለት ነው።

[33]ሠላዋት፡- በነቢዩ ላይ ሠለዋት ማውረድ ነው ።ይህ ሲባል ደግሞ ነብዩን ማወደስና መዘከር ማለት ነው።

‹‹አሚን.......›› **አልፎ አልፎ ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ** ‹‹አሚን ...›› **ይላሉ። በመቀጠልም በተመሳሳይ መልኩ ምርቃቱ**

**በመገኛ ቋንቋው** (**በኦሮምኛ**)**ትርጉም በአማርኛ** Bismillaahi waan niyattanii isiniif haa gutuu....Amiin **በአላህ ስም ያሰባችሁት ይሙላላችሁ**

Bismillaahi barakaa Abbaa Arabutiin haa egamanuu .....Amiin **በአላህ ስም በአባ አረቡ በረካ ይጠበቁ**

Bismilalahii waan niyyatan haa argatanuu........Amiin **በአላህ ስም ያሰቡትን ያግኙ**

Bismillaahii kayrini isin hin darbiin ......Amiin **በአለህ ስምመልካም አይለፋቸው**

Bismillaahii sharrin isaan hin argiin ….Amiin **በአላህ ስም ከክፉ ይጠብቃቸው**

Bismilahii barakaa abbaa arabutiin haa egamnuu..Amiin **በአላህ ስም በአባአረቡ በረካ ይጠበቁ**

Barakaa sayyiidi abbaa arabuutiin nagaan haa galanuu ..Amiin **በሰይዲ በአባ አረቡ በረካ በሰላም ይግቡ**

Barakaa sayyiidi abbaa arabuutiin hojjatnii haa argatan…..Amiin **በአባ አረቡ በረካ ሰርተው ያግኙ**

Berkaa sayyiidi abaa arbuutiin facaafatanii haa argatan.. Amiin **በአባ አረቡ በረካ ዘርተው ይጨዱ**

Bismilahi barakaa sayydii abaa arbutiin dhanii hagudiisnuu…Amiin **በአባ አረቡ በረካ ወልደው ያሳድጉ**

Berkaa saydii abaa arbutiin matiin isaani haegmnu..Amiin **በአባ አረቡ በረካ ቤተሰቦቻቸውይጠበቁ**

Barakaa sayyidi abbaa arabutiin kadhattani hin dhabinaa….amiin **በአባ አረቡ በረካ ጠይቃችው አያ**

Barakaa sayyidi abbaa arabutiin argattani hin dhabinaa ….amiin **በአባ አረቡ በረካ አግኝታችው አትጡ**

Barakaa sayyidi abbaa arabutiin waan niyyatan hin dhabinaa… amiin **በአባ አረቡ በረካ ሁላችሁም ያሰባችሁትን አግኙ**

Barakaa sayyidi abbaa arabutiin wantii qabdan haa barakatuu … amiin (**በአባ አረቡ በረካ ያላችሁ ይበርክትላችሁ**

Barakaa sayyidi abbaa arabutiin waan horattan isiinif haa barakatuu … amiin **በአባ አረቡ በረካ ያፈራችሁት ይበርክት**

Barakaa sayyidi nabitiin nagaa haa taatu … amiin **በአባ አረቡ በረካ ሰላም ትሁን**

Barakaa sayyidi shekanaa husenitin nagaa haa taatu … amiin **በሸከናሁሴን በረካ ሰላም ትሁን**

"**አላሁ መሰሌ**" **ሰላም ለነብያችን ይሁን**

**ወሰሌ ማላ ሰይድና ሙሀመድ ዋአላ አሊ ሰይድና ሙሀመድ**(**በነብይችን ላይ እዝነትና ራህመት ይውረድላቸው**)

**በማለት ምርቃቱን ይቋጫል። የዚህን ምርቃት (የአንድ መራቂ ምርቃት)መቋጨት ተከትሎ በዱአው እና ከዱአው በፊት ክዋኔ በተሠራው ንኡስ ቡድን መካከል የመዘያየር ስርዓት ይከተላል። ይህ የሚደረገው አባ ጀርሳው(መራቂው)ከላይ ያቀርባቸው ምርቃቶች ለንኡስ ቡድኑ አባላት በተናጠል እንዲደርስ ‹‹አሚን፣ ይሁን›› በማለት የሰበሰቡትን ለቡድን አጋሮቹም እንዲደርስ ምኞትየሚገልፅበት መሆኑን ለመረዳትችያለሁ።ይህ ክዋኔም በየተራ እየተነሱ የሚመረቁት ተባረኪዎች በጨረሱ ጊዜ ይፈፀማል።**

**በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ክብረ በዓል የቀረቡትን ምርቃቶች ስንመለከት በአብዛኛው ሐብት፣ ጤና፣ ኢማን፤ በረከት እና ሰላምእንዲኖረን የተጠየቁ ሲሆኑ በተለይ በየንኡስ ቡድን ወቅታዊ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቶባቸው እንደሚነሱ በቃል መጠየቅ ያገኘሁት መረጃ ያመላክታል።**

**በዚህ ጊደይ ላይ እኔም በቦታው ላይ በነበረኝ ምልከታ በሌሊቱ የዱኣ ክዋኔ ወቅት ከነበረው አዲስ ገዢ መንግስትጋር በተገኘ አብይን፤ ‹‹ነቢይ ዳና አብዩን አባአረቡቱ ፈለቴ፤አብይን ከንሹመኒ አባ አረቡዳ››(ለኛ የሚጠቅም መሪ ያድርገው፤ እሉንም አባ አረቡ ይጠብቁት፤ እሱን በክፉ የሚያዩት ጠላቶች ይወደሙ።) የሚሉ ምርቃቶች ከላይ በቀረበው የምርቃት ክዋኔ በተመሳሳይ መልኩ ሲፈፀሙ አስተውያለሁ። ይህ የሚሆነው ደግም ሁሌም በማህበረዊ ህይወታቸው የሚገኘው ችግሮች ፈጣሪ እንዲያቀል መልካም ምኞት ለመግለፅ ነው።ይህን ጉዳይ በተመለከተም አብዱራሂማን** (2007) **‹‹የሺህ ሁሴን ዳንግላ የመውሊድ በኣል ስረኣት እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ›› በሚል ርዕስ ባቀረበወ ጥናት፤ በመውሊድ በዓል ላይ የቀረቡ ምርቃቶችን በሚያይበት ክፍሉ ካቀረባቸው ምርቃቶች መካከል በውቅቱ ከነበረው እስላማዊ እንቅስቃሴ ጋር የነበረውን አለመግባባት ለማስተካከል፣ ሀገራችንን ወደሰላም ቀይሮልን የተጀመሩ ልማቶች እንዲፋጠኑ የሚመኙ ምርቃቶች መተንተኑን ልብ ይሏል።**

*ምስል ሰባት፡ ከቁባው ውጭ የነበሩ የበዓሉ አክባሪዎች ፎቶ*



በዚህ በዱኣዉ ስርዓተ ክዋኔ ክፍል ከመጀመሪያዉ ጎራ (ቡድን) የሁለተኛዉ ጎራ እንደመጀመሪያዉ ቡድን በቤት ዉስጥ እና በዉጭ እንዲሁም በአካባቢዉ ነዋሪዎች ቤት የታደሙ ምዕመናን የሌሉት ሲሆን፤ ከላይ በዚያራዉ ክፍል ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ለዚሁ ቡድን ብቻ ተብሎ በተዘጋጀ አንድ ዛፍ ስር ሸራ በመወጠር ተሰባስበዋል። የመዉሊድ ስርዓተ ክዋኔዉ ቅደም ተከተል እንደመጀመሪያዉ ቡድን ዚያራ፣ ዱኣ፣ ምርቃት፣ መንዙማ እያለ በተመሳሳይ አካሄድ የሚቀጥል ቢሆንም አልፎ አልፎ በአከዋወን ሂደቶቹ ስርዓት ለዉጥ ይታይበታል። ይህን ለዉጥም በምልከታዬ ወቅት ለማረጋገጥ እንደቻልኩት፤ ለዱኣ የተቀመጡት ከሌሎቹ ምዕመናን በአለባበስም ሆነ በአነጋገር ብቃታቸዉ ከሌሎች ምዕመናን የተለዩ ናቸዉ።

ከእሳቸዉ ጎን ደግሞ አንድ የሳቸዉ የቅርብ ረዳት የሆነ ወንድ ካዳሚና ሴት ካዳሚ በግራና በቀኝ ተቀምጠዋል። የወንዱ ካዳሚ የስራ ድርሻ እሳቸዉ ከአፋቸዉ የወጣዉን ነገር ድምጹን ከፍ በማድረግ ለሌሎች ማሰማት፤ ዱኣ እንዲደረግላቸዉ የሚፈልጉ ሰዎችን ተራ ማስያዝ ነዝር(ስለት) የሚሳሉ ሰዎችን ስም በመዝገብ ላይ መጻፍ የዚህ ሰዉ የስራ ድርሻ ናቸዉ። የሴቷ ካዳሚ የስራ ድርሻ ደግሞ የሳቸዉን ፕሮቶኮል ማስተካከል፤ ለምሳሌ ከትከሻቸዉ ፎጣ ከወደቀ ማልበስ፣ በራሳቸዉ ላይ ያደረጉት የጨሌ ጉፍታ ሲወድቅ ማጥለቅ፣ ለነዝር የገባ ገንዘብ እንዲቆጠር

ሲሰጣት መቁጠር፤ ሰዎች ያመጡትን ዳቦ እና ብስኩት በአቅራቢያዋ ላሉት ሰዎች ማከፋፈል የሷ ስራ ድርሻ ነዉ። ለእነዚህ ሁለት ሰዎች የስራ ድርሻ ክፍፍል በማን እንደተሰጣቸዉ እንዲገልጹልኝ ላቀረብኩላቸዉ ጥያቄ፡-

> በመጀመሪያ እሳቸዉ ፍቃድ ይስጡ የሚል ምላሽ ሰጥተዉኝ ለተባሉት አዛዉንት ይህን ጥያቄ በማቀርብበት ወቅት "sila sittii himnerraa muggutii hin barbaannu" በማለት ፍቃደኛ እንዳልሆኑ ለመረዳት ችያለሁ። እንዲሁ ከማየዉና ከአዛዉንቱ ስሜት በመነሳት ይህ ስልጣን ከሳቸዉ የተሰጣቸዉ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ እንድደርስ አስችሎኛል።

ለሁለተኛ ጊዜ በቀን 13/03/11 ዓ.ም ለወ/ሮ አለዉያ አባዝናብ፤ እዚህ የሚደረገዉ ዱአ እና እዛ መቃብሩ ስፍራ የሚደረገዉ ዱአ ልዩነት አለዉ? ብዬ ለጠየኳቸዉ ጥያቄ እሳቸዉም ከድሬ ሸከና ሁሴን ቢመጡም የአባ አረቡ ሳሂብ ናቸዉ። ‹‹እንግዲህ የሸከና ሁሴን ልዩ ነዉ፤ እኔ ማወዳደር አልችልም በእኔ አቅም። እኔ ያዉ ለዚያራ አባ አረቡን በቀልቤ አስቤ መጥቻለሁ። እዚህ ስመጣ ደግሞ አርሲ መሄድ የማልችለዉን እሳቸዉን እዚህ ሳገኝ ደስታዬ ወደር የለዉም።ዱአ ሁሉም ያዉ ነዉ፤ መቅቡል ነዉ፤ ይቀበሉናል። እሳቸዉ የትም ብንሆን ‹መራሃባ›ይሉናል›› ሲሉ ምላሻቸዉን ሰጥተዉኛል።

በመጀመሪያዉ ጎራ እና በሁለተኛዉ ጎራ ያለዉን የዱአ አካሄድ ባስተዋልኩት መሰረት ዱአ አድራጊዉ ከመሃል በግራና በቀኝ ወንድና ሴት ካዳሚዎች ከላይ በገለጽኩት መሰረት ይቀመጣሉ። ሌሎች ምዕመናን እነሱን ከበዉ ወንድ ሴት ህጻን አዋቂ ሳይለይ ክብ በመስራት ይቀመጣሉ። ለዱአ መክፈቻ ብር ወይም ጫት ከፊት ለፊታቸዉ የሚቀመጥ ሲሆን፤ በዱአ ወቅት በአንደኛዉ ጎራ ከዚህ ቀደም እንደተለመደዉ ረጅም ዱአ አሜን እየተባል ሲቀጥል አላስተዋልኩም። በሰጭና ተቀባይ መንገድ አጠር ያለ ዱአ ከተደረገ በኃላ ወደ ምዕመኑ (ዱአ ወደ ተደረገለት) ግለሰብ የሚመለስ ጫት አላስተዋልኩም። በመጀመሪያዉ ጎራ ዱአ ሲጀምር ዱአዉን በሰለዋት (በነብዩ ላይ ራህመት) በማዉረድ የሚጀምሩ ሲሆን ዱአዉ ሲጠናቀቅ እንዲሁ በሰለዋት ነዉ የተጠናቀቀዉ። በዚህኛዉ ቡድን ግን ለዱአ የሚሆን ጀባቲ ከቀረበ በኃላ ባለጉዳይ የሆነ ሰዉ በተቀመጠበት ተንበርክኮ ጉዳዩን ያስረዳል። ተራዉ ከሆነ ዱአ ይደረግለታል። ከዚያ ስኳር ትንሽ በመቅንጠር ዱአ አድራጊዉ ቱፍ ብለዉ ይሰጡታል/ቷል። ከዚያ ለራሱ/ራሷ ከሆነ ይቀመዋል/ትቅመዋለች። እዚህ የሌለ ሰዉ ከሆነ በጨርቅ ተቋጥሮ ይያዝለታል/ላታል። የሚያዝበትም ምክንያት ጉዳዩ እነዚያን ቤት ያሉትን ሰዎች የሚመለከት እንደሆነ ለመገንዘብ ችያለሁ። ይህ እንደጠቀስኩት በሰለዋት የማይጀምረዉ ዱአ በዱአ አድራጊዉ ድምጽ ይከናወናል።

| *ዱአ በመገኛ ቋንቋው (ኦሮምኛ)* | *ትርጉም በአማርኛ* |
|---|---|
| Nutii ketii jannee kotii nuun haa jadhu | እኛ ያንተ ነን ብለንሃል አንተም የኔ ናችሁ በለን |
| Karri kun nun hin dhibiin | እኛን የሚያገናኝ መንገድ አይጥፋ |

| | |
|---|---|
| Salaamalykuum huseeniyyaa[34] | **ሰላም ላንቱ ይሁን ሁሴንያ** |
| Salaamalykuum huseeniyyaa | **ሰላም ላንቱ ይሁን ሁሴንያ** |
| Silaa jireenyi hin quufamuu | **በቹም በህይወት መኖር አይጠገብም** |
| Umrri nuu haa gutamuf | **እድሜያችሁን ያርዝምልን** |

**እንዲህ ብለዉ ዱኣ ካደረጉ በኃላእጃቸዉ ላይ ‹‹ቱፍ›› በማለት ይህን ተግባር ሁሉም እንዲያከናዉኑ ካዘዙ በኋላ ‹‹ኑፈረማ››(ፈርሙልን) የሚል መልዕክት አስተላለፉ። "እጃቸው ላይ ቱፍ" የሚባልበትም ምክንያት ጉዳዩ ከውስጥ የመነጨ (ጥልቀት ያለው) መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።ከዚያም ሁሉም የቡድኑ አባላት እጃቸዉ ላይ ቱፍ ካሉ በኋላ የሁለቱንም እጃቸዉን ጣት ወደ መሬት በማድረግ (መሬቱን በመያዝ) ፊርማዉን ያጸድቃሉ። በዕለቱ በቦታዉ ለነበሩት ለወ/ሮ ዲልቢ እንዲህ የማድረጋቸዉ ጠቀሜታዉ ምንድንነዉ? ብዬ ላነሳሁላቸዉ ጥያቄ በሰጡኝ ምላሽ፡-**

**ይህ የሚያስተላልፈዉ መልዕክት የመጀመሪያዉ ሁሉም በዱኣዉ መስማማታቸዉን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ‹መሬት የሰጧትን ነገር አትክድም አብቅላ ታሳያለች፤ እና የእኛም ዱኣ ዉጤታማ ይሁን፤ ስር ይያዝ› የሚል ፍች ያሳያል። ሌላዉ ደግሞ ዱኣዉ (ምርቃቱ) መጠናቀቁን እና ሌላ አዲስ ዱኣ ከዚህ በኋላ የሚቀጥል መሆኑን ያመላክታል።**

**በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዉኛል። በቁባ አባረቡ የመዉሊድ በዓል አከባበር በዱኣዉ ክዋኔ በዚህ ክፍል የሚደረጉት የዱኣ ይዘቶች ረጅም ዕድሜን መጠየቅ፣ የሼከና ሁሴንንና የአባአረቡን ዉዴታ መፈለግ የሚሉ መሆናቸውን በምልከታዬ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ። ጉዳዩን በተመለከተ ለወ/ሮ መካ ከሊፋ ባደረግኩት ቃለመጠይቅ፤ በምርቃት ሁሌም ማህበራዊ እና ወቅታዊ ጉዳዮች እንደሚነሱ ለመረዳት ችያለሁ። ይህ የሚሆነዉ ደግሞ ከዱኣዉ ምልከታና ከቃለመጠይቁ እንደተረዳሁት ሁሌም በማህበራዊ ህይወት የሚገጥሙ ችግሮችን ፈጣሪና ለፈጣሪ ቅርብ አማላጅ በሚባሉት ሰዎች እንደሚቃለሉ መልካም ምኞታቸዉን ለመግለጽ ሲሉ የሚሰባሰቡ መሆኑን ነዉ።**

### 4.2..2..3 መንዙማ

**በቁባ አባአረቡ የመዉሊድ በዓል ከበራ የመንዙማ ግጥሞች የሚከወኑት በአዋቂዎች በተደራጀዉ ቡድን በዱኣዉ መካከል ሲሆን በወጣቶች በተደራጀዉ ቡድን ቀጥታ የሚገቡት ወደ መንዙማዉ ነዉ።[35] በዚህ ሁነት የሚቀርቡት መንዙማዎች አጠቃላይ ይዘት የነብዩ ሙሐመድ መልዕክተኛነት የሚገልጹ ዉዳሴዎች፣ የአባ አረቡንና የሼከና ሁሴን ገድል፣ ለህብረተሰቡ ያበረከቱትን ድንቅ ስራ እና ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያወሱ ሲሆኑ፤በአብዛኛዉ**

---

[34]የሚለው ስም የሚተከው የድሬውን አሊም (ድሬ ሼህ ከና ሁሴንን ) ነው፡፡ ምእመኑ ለሳቸው ያላቸውን ፍቅር ለመግለጽ እያ ቆላመጠ የሚጠራበት ምትክ ስማቸው ነው፡፡

[35]ወጣቶቹ በቀጥታ ወደ መንዙማው የሚገቡበት ምክንያት ይህንን አጋጣሚ ለደስታ ለጨዋታ እንዲሁም የቃላዊ ግጥም ብቃታቸውን የሚያሳዩበት መድረክ አድርገው ስለሚያዩት ነው፡፡

የሚቀርቡበት ድምጸት ‹‹እኛም እንደሳቸዉ አዛኝ መልካም ባደረገን›› የሚል ነዉ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ የበዓሉ ተሳታፊ የሆኑትን አቶ ጁነኢድ በቀን 15/03/11 ዓ.ም በክብረ በዓሉ ፍጻሜ ላይ በተደረገላቸዉ ቃለመጠይቅ፦

*የመንዙማ ግጥም የእስልምና ኃይማኖት የሚሰበክበት የነብዩ መሐመድና ኡለሞች የሚወደሱበት ማህበራዊ ችግሮች የሚነሱበትን ግጥሞች የሚይዝ ነዉ። በይበልጥ ደግሞ በቦታዉ ታስበዉ የሚከበርላቸዉን ኡለሞች ገድልና ትልቅነት ለማወደስ ሲባል የሚዜም በመሆኑ በነሱ ዙሪያ ያጠነጠነ ነዉ። የሚቀርቡት የመንዙማ ግጥሞች በአብዛኛዉ በኦሮምኛ ሲሆን አልፎ አልፎ በአረብኛና በአማርኛ ነዉ በማለት ይገልጻሉ።*

በዚህ ጉዳይ ላይ ሼህ አህመድአሚን አብዱልዋሂድ (የመውሊዱ አስተባባሪ) የሚከተለውን ብለውኛል፦

*መንዙማ ማለት ፈጣሪ፣መልእክተኛውና ኡለሞች የሚወደሱበት ነው። መውሊድን ስታስቢው መብላት፣ መጠጣት አለ።ከጥጋብ ቀጥሎ ደስታ ይመጣል። ደስ ሲልሽ ደግሞ ደስታሽን ኢስላማዊ በሆነ መንገድ በእልልታ፣በጭብጨባ፣ በማዜም ትገልጫለሽ። እንደዚህ አይነት መውሊድ ቦታ ስትመጪ ደግሞ ሁኔታዎቹ ሁሉ የተመቻቹ ስለሆኑ እንኳን ፍላጎት ያለው የሌለው እንኳን መንዙማ ሰምቶ ሳይጨፍር እና በድቤው ምት ሳይደሰት የሚመለስ የለም።*

ከነዚህ ሀሳቦች በመነሳት መንዙማ መውሊድን አንድ የመከወኛ አጋጣሚ በማድረግ የሚከወንና በክዋኔው ወቅትም ፈጣሪ፣ ነብዩ መሀመድ እና ኡለሞች የሚወደሱበት ማህበራዊና ወቅታዊ ችግሮች የሚነሱበት፤ ግጥሙ በድቤ፣በአሸቄና በጭብጨባ እንዲሁም በእንጉርጉሮ የሚቀርብ መሆኑን ነው።ከዚህም በተጨማሪ መንዙማ በሚባልበት ጊዜ በፍጹም ሊነጣጠል የማይችለው ጉዳይ መንዙማዉን ለማድመቅ የሚመጡት እንደ ድቤ፣ አሸቄ፣ የመሳሰሉት ቁሳዊ ባህሎች መሆናቸዉን ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮቼ ጋር በነበረኝ ቆይታ ለመረዳት ችያለሁ።[36]

እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ደግሞ ለክብረ በዓሉ የሚሰጡት ድምቀት ከፍተኛ ከመሆኑ ባሻገር ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸዉ ሆነዉ እናገኛቸዋለን። ስለዚህ የመንዙማውን ቃል ግጥም ይዘት ከተመለከትን በኋላ በመዉሊዱ በዓል የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች በሚለዉ ክፍልሰፋ ያለ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። አጠቃላይ በዚህ ክዋኔ ላይ ተሳታፊዉ ከፍተኛ ፌሽታ የሚያደርግበት፣ የእምነቱን ዉስጣዊ ግለት የሚገልጽበትና ህብራዊ ቅብብሎሽ የሚስተዋልበት ነዉ። በተመሳሳይ መልኩ የዚህን ክዋኔ ሂደትና ድርጊት በቃላዊ ግጥሞቹ ክዋኔ ክፍልበሰፋት መመልከት ይቻላል።

---

[32]በዚህ ጥናታዊ ጹሁፍ በቀጣዩ ንዑስ ክፍል የእነዚህን ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ በተመለከተ ሰፋ ያለ ትንታኔ ቀርቧል። ነገር ግን ለዚህ ክፍል ስለመንዙማ ማንሳት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ቃላዊ ግጥሞች የዱኣዉ አንዱ ሁነት በመሆናቸዉ ለማሳየትና መህል የመጡበትን ምክንያት ለመግለጽ በመፈለግ ነዉ።

#### 4.2..2..4 **የክዋኔዉ ማግስት ሁነቶች**

በክብረበዓል ላይ ትኩረት ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ማንኛውም ክብረበዓል ሂደቱን የሚጨርሰው ለራሱ በሚደረጉ ዝግጅቶች መሆኑን ይጠቁማሉ።በተመሣሣይ የቁባ አባአረቡ የመውሊድ በዓል ስርዓት ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉት ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች እንደተጀመሩ ሁሉ የራሱ የሆነ ማጠቃለያ አለው።

ይህ የስርዓት ክዋኔ ማግስት ደግሞ መውሊድ ሥርዐቱ በጠበቀ መልኩ እንዲፈጸም የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው። በዚህ ጊዜ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ደግሞ የሸኘት ስርዐት በዋናነት ይጠቀሳል።ይህ ሁነት ለበአሉ የመጡ እንግዶች መደመጠበት የሚመለሱበት ሲሆን ህዳር 11ለ12 ሌሊት ያደረገው አብዛኛው ምዕመን በዕለቱ (የካቲት 12) በመውሊድ ስም የተዘጋጀውን ሆነ እራሳቸው ከቤት አዘጋጅተው ያመጡትን ምግብ ተመግበው ወደየመጡበት ይመለሳሉ። በዚህ ቀን ያልተመለሱትና በዕለቱ ከበረውን የሚቀላቀሉት ደግሞ ህዳር 12 ለ13 ሌሊት አክብረው ህዳር 13 ወደየመጡበት ይመለሳሉ። በዚህ አይነት መልኩ ከዋዜማው ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በእንዲህ አይነት ሁኔታ ይቀጥልና በመጨረሻው የመውሊድ ማብቂያ ዋናው እለትገንፎ ወይም የታረደ ካለ ከሱቢህ ሰላት በፊት ተበልቶና ቡና ተጠጥቶ በርዘንጅ[37] ከተባለ በኋላ የመውሊዱ ፍጻሜ ይሆናል።ይህንኑ የሸኘት ስርዐት መሰረት በማድረግ፤ ምን ያህል ምዕመን ወደ ከበራው መጥቷል? እንዴትስ ተስተናገደ? ከአቶ ጁነአድ ከድር ጋር በቀን 13/03/11 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ምልልስ፦

> የትኛውም ሰው ብትጠይቂው ይህን ያህል ሰው ብሎ በቁጥር የሚነግርሽ ነገር አይኖረውም። ያለው ቦታ ሲያንስና (ለምሳሌ በቀን 8 የአካባቢው መውሊድ ሲካሄድ፣ ከዚህ በፊት ከሚታረደው የበሬ ቁጥር አንድ ተጨምሮ ነበር) የዘደው ነገር ግን ምንም ሳይተርፍ ተስተናዶው ነው ያለቀው። አሁን የዚያራ እለት ምን ያህል ሰው ነበር ብትይኝ፤ከ3000-- 3500 ያህል የሚደርስ ሰው ነበር ልልሽ እችላለሁ። የሰው ሁነት ዳግም እንዴት መሠለሽ፤ በመቀደም /በዋዜማ/ ቁጥሩ በዛ ብሎ የሚታይ ይመስላል። ነገር ግን በ12(በዋናው ቀን)የሚመጣው ህዝብ ቁጥር ከየትኛውም ቀን የበለጠ ነው። ከዚህ ቀን በኋላ እሰከ አምስተኛው ቀን ድረስ ምዕመናን ይምጡ እንጅ ቀኑ እየቀነሰ በሄደ ቁጥር የምዕመኑ ቁጥርም እየቀነሰ ነው የሚሄደው። በዚያ ላይ ደግሞ መጥቶ ውሎ ብቻ የሚመለስ አለ።ቁጥሩ ብዙ ነው። በመረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ይህን ማለት ይከብዳል እንጅ።እንዲሁ ገምት ካልሽኝ በቀን እና ሌሊቱን አድሮ የሚሄደው ተመሳሳይ ባይሆንም በተለይ በሁለቱ ቀናት 11 እና 12 ወደ 15ሺ የሚጠጉ እንግዶች በቦታው ተስተናግደው ይመለሳሉ። ታዲያ ሲመለሱ እንዲሁ በባዶ ሳይሆን እዚህ የመጣ ምዕመን በየትኛውም ቀን ድረስዘምዘም (ተህሊል ውሃ) ይዞ

[37]በርዘንጅ ቃሉ አረበኛ ሲሆን ለመውሊድ ማክተሚያ (መፈጸሚያ) በስተመጨረሻ የሚባል ዱአ ነው። ከዚህ በኋላ የሱቢ ሰላት ተሠግዶ በፈለገበት ሰዓት እነደ ሌሎቹ ተህሊሉን በመቅዳት ወዳየ አካባቢውና ቤቱ ይመለሳል።

ነው ወደየቤቱ የሚመለሰው። እንግዶቹም ምንም አይነት ችግር ሳይደርስባቸው ይመለሱ ዘንድ ወጣቶች አስገላጊውን ትብብር ያደርጋሉ በማለት ነገሩኝ።

እዚህ ላይ ከሽኝት ሁነቱ ጋር ተያይዞ በነበረኝ ምልከታ በርካታ የበዐሉ ተሳታፊዎች ከቁባው አጥር ውጭ በተወሰነ ርቀት ካለው ግድብ የጉድጓድ ውሃ (ዘምዘም) እየቀዱ ወደየቤታቸው ሲሄዱ በማየት፤ ምዕመኑ ወደ መጣበት ሲመለስ ለምን የተህሊል ውሀ (ዘምዘም) እየያዘ ይሄዳል? ውህው ለክብረበኣሉ ተሳታፊዎች የሚሰጠው ትርጓሜ ምንድነው? የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት ምክንያቶች ለማወቅ ስል አቶ ጀነኢድ ከድርን ጠየኩ።

‹‹አባአረቡ ጥለውልን ካለፉት ነገር አንዱ ይህ የተህሊል ውሃ (ዘምዘማ)ነው። እንደ ሰማሁት ይህ ውሃ እዚህ ብቻ አይደለም፤ የጅማው ገብርኤል ቤተክርስቲያን ፀበል አጠገብ ያለው ጊዮርጊስ ፀበል የሚባለውም የሳቸው እንደሆነ ይነገራል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም በሳቸው የተገኘየተህሊል ውሃ በሌላ አካባቢ እንዳለ ሲናገር ሰምቻለሁ። ይህኛውንም ሆነ በሌላ ቦታ ያለውን የተህሊል ውሃ በአንካሴያቸው (marcoo isaniin) ወግተው አለህ ውሃ እንዳፈለቀላቸውና ይህ ውሃም ለየትኛውም በሽታ ፈዋሽ እንደሆነ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ይተመናል።እና የትኛውም ምእመን ለመወሊድ በዓል መጥቶ ይህንዘምዘም ሳይጠጣና ሳይቀባ እንድሁም በእቃ ቀድቶ ሳይዝ ወደ ቤቱ የሚገባ የለም።ለየትናውም በሽታ ፈዋሽ ስለሆነ እሱን ጠጥተሽ የሚሰማሽን ቦታ ከተቀባባሽ በሽታሽ ከላይሽ ላይ ውልቅ ነው የሚለው።››

በማለት ምላሻቸውን ሰጥተውኛል። ከዚህ በተጨማሪም ከበዓሉ ተሳታፊዎች መካከል ከወ/ሮ አለውያ አ/ዝናብ፤ ከወ/ሮ አይሻ ዲልቢ እና ከሸህ አወል አባመጫ ጋር በ13/03/11 ዓ.ም በበዓል ማክበሪያ ቦታ በነበረኝ ቃለ ምልልስ በበዓሉ ፍፃሜ ከግቢው ውጭ የሚገኘውን የተህሊል ውሃ (ዘምዘም) በልዩ ልዩ እቃዎች እየቀዱ እንደሚመለሱ ተጠቁሚያለሁ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ደገሞ ውሃው ለልዩ ልዩ በሽታዎች ፈዋሽ መድሃኒት ነው ተብሎ ስለሚታመን ሲሆን፤ ስለ ውሃው የሰማው ሰው ሁሉ በፈለገው የዕቃ መጠን ወደ ቤቱ ይዞ ይሄዳል። ቤቱ ውስጥ በማስቀመጥ በሽታዎች በሚያጋጥሙት ወቅት በመጠጣትም ሆነ በመቀባት ይጠቀምበታል። በዚህም ከህመሙ ይላቀቃል፤ ደስተኛም ይሆናል ብለውኛል።

በአጠቃላይ ከላይ በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ሥርዐት ክዋኔ የተመለከትናቸው ሁነቶች እያንዳንዳቸው እርስ በእርስ የተያያዙና አንዱ ለአንደኛው መሠረት ያለው ነው።ይህ ጉዳይ ደግሞ Rappaport (1992,249) ያለውን፤

"ክበረ በዓል ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች እንዱ ሳይሆን በሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገለፁት)ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ግልፅ የሆነ ቅርጽ ያለው፤የተለያዩ ገጽታዎችና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ባህሪያቶቹ አነሰም በዛም እርስ በርስ የተያይዙ ናቸው።"በማለት ከገለጸው ጋር የሚጣጣም ነው።

## 4.3 የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በኣል ላይ የሚከወኑ ቃለዊ ግጥሞች ክዋኔ

በመውሊድ በኣል ላይ የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች መንዙማ በመባል ይታወቃሉ።እነዚህ መንዙማዎች በዓሉን ለማክበር በመጡ ምዕመናንና በአካባቢው ነዋሪዎች የሚባሉ ሲሆን አጠቃላይ ይዘታቸውም የንነብዩ ሙሀመድን ታላቅነት፣ የኡለማዎች ገድልና መልካም ሥራ የሚነግሩንና በነሱ መልካምነትና ታላቅነት ሁሉም የበአሉ ታዳሚዎች ሆኑ ምአመናኑ ለዚህ መድራሳቸውን የሚገልጹ ናቸው።

በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በኣል ሥርዐተ ክዋኔ ላይ የመንዙማ ቃላዊ ግጥሞች ዱአ ስርዐት እየተካሄደ ባለበት በሌሊትም በቀንም ይከወናሉ። በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔ ከማሳየት በፊት መንዙማ ምንደነው? ከመወሊድ በአልስ ጋር ምን ቁርኝት አለው? እንዴትስ ተጀመረ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በበኣሉ ላይ አስተባባሪ ከነበሩት ሸህመሀመድአሚን አብደላ (የቁባ አባአረቡ ኢማም)፣ ከአቶ አንዋር ሁሴን (ደርጋ) እና ከአባመጫ አባአረቡ (የአባ አረቡ ካዳሚ)ጋር ባደረግኩት ቃለ መጠየቅ የሚከተለው ምላሽ ለማግኘት ችያለሁ።[38]

> *መንዙማ የሚለው ቃል አረበኛ አይደልም፤ በኦሮምኛና በአማርኛ እንደሚባል አውቃለሁ። በሌሎች ቋንቋዎችም የራሳቸው ትርጓሜ ሊኖራቸው ይችላሉ።መንዙማ የሚለው ቃል በአረበኛው ነሺዳ የሚለው ቃል የሚተካው ይሆናል። መንዙማ ምንድነው? ለሚለው የአላህን ቃል የነቢን ታላቅነት የኡለሞችን ደግነትና መልካም ስራ በግጥም መልክ አስተምህሮት የሚተላለፉበት አንዱ ዘዴ ነው።እንዴት ተጀመረ? የት ተጀመረ? ለሚለው በታሪክ እንደሚታቀው ነብዩ መሀመድ ከዘሬ 1440 ዓመት በፊት ሂጅራ[39] (ስደት) ወደ መካ አድርው እና በዚያን ጊዜ እንደተጀመረ ይነገራል።የት ለሚለው እዚያው መካ ማለት ነው። እንደኢትዮጵያ ካልሸ በፅሑፍ የተደገፈ መረጃ የለም። ነገር ግን ተጨባጭ የሚየደርገው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚጠቀሙት የሂጅራውን አቆጣጠር በመሆኑ በዚያን ጊዜ ተጀመረ ብሎ ለመደምደም ባያስማም ግምት መስጠት ግን ያስችላል ይላሉ።*

---

[38]በቀን 14/03/11/ከሸህ መሀመድ አሚን አብደልዋሂድ(የመስጅዱ ኢማም)፤አቶ አንዋር ሁሴን የአካባቢው ነዋሪ (ደርጋ)ና አባ/መጫ አባ/አረቡ (የአባ አረቡ ካደሚ)ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት የተገኘ።

[39]ኢስላማዊ የዘመን አቆጣጠር ነው።

አብዱራህማን (2007)፤"የሼህ ሁሴን ዳንግላ የመውሊድ በዓል ስርዐት ክዋኔ እና ቃላዊ ግጥሞች ትንተና" በሚለው ጥናቱ‹‹መንዙማ›› በሚለው ክፍል ከመረጃ አቀባዮች ያገኘው መረጃ የመንዙማና የኢትዮጵያ ቁርኝት የሚጀምረው ከእስልምና የመጀመሪያዎቹ አመታት አንስቶ መሆኑን ነው። ከዚያም በዚያው ርዕስ ስር መንዙማ የኢትዮጵያን መስሊሞች እንጂ በሌሎች ክፍላተዓለም ያሉ የአሰልምና ታከታዮች አለመሆናቸውን እንደተረዳ ገልጿል።

በኔ ጥናት መረጃ አቀባዮቹ መሰረት፤ ነሽዳ አረበኛ ሲሆን መንዙማ በኦሮምኛናበአማርኛ ፍቺው እንደሆነ ገልጸውልኝ፤የተጀመረውም ነብዩ ሂጅራ በወጡበትዘመን እንደሆነና በአረቡ ክፍል ሴቶች እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ።ስለዚህ እነዚህ ሀሳቦች እንዳሉ ሆነው አንድ የፎክሎር አጥኚ ለወደፊት ረእሱን "የመንዙማዎች ፎክሎራዊ ጥናት" በሚል ቢያጠና ለነዚህ አወዛጋቢ ጥያቄዎች ምላሽ ይገኝበታል የሚል ግምት አለኝ።

በቁባ አባ አረቡ በመውሊድ በዓል ቃላዊ ግጥም (መንዙማ) ስነሰረዓት እንዴት ይከናወናል? የሚለውን ስነስረአቱ እየተፈጸመ ባለበት በሌሊቱና በቀኑ ክዋኔ መሀል መሀል ላይ እንዲሁም በለሊቱ ክዋኔ በቀጥታ[40] ሲፈጸም አስተውያለሁ።

እንደ የፎክሎር ዘርፍ ለመከወን ደግሞ ከዋኝና ታዳሚ እንደሚየስፈልገው ሁሉ ለመከውን ሰበብ የሚሆነው የመከወኛ ምክንያት ሊኖረው ይገባል።[41]ይህ ቃላዊ ጥበብ የክዋኔ ሂደት ደግሞ መውሊዱን ሰበብ አድርጎ ይከውናል።ሲከወንም እራሱን የቻለ አንድ ጥበባዊ ገጽታ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን።በዚህ ጥናትም ከቃላዊ ግጥሞቹ ጋር በተገናኘ በዋናነት የተመለከትኩት በክብረ በዓሉ ወቅት የተከወኑትን ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች)ከክዋኔ ሂደታቸው በመነሳት እንዴት ይከናወናሉ? ሲከወኑ የተሳታፊዎቹ (የአቀንቃኙና ተቀባዩ)ሚና ምን ይመስላል? የቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ሂደት በቀረበበት ደረጃ እንዲከወኑ የሚያስችሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ ላይ አትኩሬያለሁ።

በዚህ ክፍልም እነዚህን ጥየያቄዎች ለመመለስና የመንዙማዎችን ክዋኔ ለመተንተን በክብረ በዓሉ ላይ የቀረቡት የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሂደት (በሀድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) በመመስረት በዱፊ፣በኡሌ ዱፊ፣በአሽቁና በእንጉርጉሮ የሚባሉ በማለት እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

### 4.3.1 በዱፊ የሚባሉ መንዙማዎች

---

[40]በለሊቱ ክዋኔ በቀጥታ ቃላዊ ግጥም(መንዙማ)የሚካሄደው በወጣት ሴቶችና ወንዶች የተሞላው ቡድን ነው።በዚህ ቡድን ከማሸቅ ውጭ ምንም አይነት የዱአ ጊዜ በተከታታይ በነበሩት አምስት ቀናት አላስተዋልኩም።ለዚህም ምክንያት ምላሽ መንዙማ በሚለው ክፍል በቀን 15/03/11 ዓ.ም ከአቶ ጃነኢድ ከድር ጋር የተደረገውን ቃለ መጠይቅ ልብ ይሏል።

[41](ፊኔጋን ፣1992፣91-92 እና ቦውማን ፣1975፣290)። የፎክሎራዊ ጉዳይ ባህርይ በሚል ስር ካስቀመጡት አጋጣሚውን በተመለከተ ከገለጹት ሀሳብ የተወሰደ።

በቁባ አባ አረቡ የመውለድ በዓልስረዓተ ክዋኔ ላይ በነበረኝ የቀጥታ ተሳትፎ ምልከታ ላይ ለመረዳት እንደቻልኩት በድቤ የሚባሉ መንዙማዎች በተሳታፊዎች መካከል ከፍተኛ የሆነ እሸቅ (መነቃቃትን) የሚፈጥሩ፣በከዋኙና ተቀባዮቹ መካከል ስርዓት ያለው ቅብብሎሽ የሚፈጥሩ፣ክዋኔያቸው ደግሞ እራሱን የቻለ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመር ያላቸው ናቸው።

እነዚህን የመንዙማ አይነቶችን በተመለከተ ወ/ሮ አለውያ ጌራ በቁባ አባ አረቡ (በአሉን ለማክበር ከአስር ጊዜ በላይ የተገኙ፤በቦታው ሴት የመንዙማ አቀንቃኝ)እና ሼህ አብደላ ሙሳ (አጃቢያቸው) ጋር አብረው በበዓሉ ማክበሪያ ቦታ በተቀመጡበት ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ፡-

> "ይህ የመንዙማ አይነት ሞቅ ያለ በእንቅስቃሴ፣በጭብጨባና በድቤታጅበው የሚቀርቡ፤ አሸቁ ደግሞ ጭብጨባ ቢያንስ እንኳ የብዙ ሰው ያህል የመሸፈን አቅም አላት።በዚህ መሳሪያ የሚባሉ የመንዙማ አይነቶች ሰጪና ተቀባይ የሚፈልጉ ናቸው።የአንድ ወገን ሳይሆን የሁለት ባለ ድርሻዎችን ሀላፊነት የሚጠይቁ የመንዙማ አይነቶች ናቸው።"ሲሉ ይገልጻሉ።

በምልከታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት እነዚህ የመንዙማ አይነቶች የመቅረቢያ ቋንቋቸው በብዛት ኦሮምኛ ሲሆን አልፎ አልፎ አረብኛና አማርኛ ይደመጣሉ።በአጠቃላይ በእለቱ በኦሮምኛም ሆነ በአረብኛ ሲቀርቡ የነበሩት መንዙማዎች አዝማቻቸው ቢያንስ ለአራት ጊዜ የሚደጋገምና ባለ አጭር ስንኞች (በባለ አንድ ስንኝ) የተሞሉ ናቸው።ከዚህ የምንረዳው በድቤ የሚቀርቡ መንዙማዎች ሞቅ ያሉና ሰውን የሚያነቃቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ አዝማቻቸው ተደጋጋሚ የሆኑና አጭር ስንኝ ያላቸው መሆናቸውን ነው። ይህንንም እንደሚከተለው ለአብነት በቀረበው የመንዙማ ግጥም ማስተዋል እንችላለን።

[38]አሸቁ፡- ማለት በአማርኛው ከበል ሲሆን ፤ይህን ቁሳዊ ባህል ከዱፊ ጋር በአንድነት የተጠቀምኩበት ምክንያት ብቻውን ፋይዳ ሲሰጥ ባለማየቴ እና፤የጋራ ተግባር ሲፈጽሙ በመመልከቴ በአንድነት ልገልጻቸው ችያለሁ።

*ቃላዊ ግጥም በመገኛው (ኦሮምኛ) የቃላዊ ግጥም ትርጉም*

| | |
|---|---|
| Salaamualayum huseniyyaa | ሁሴንዬ ሰላም ላንቱ ይሁን |
| Salaamualayum huseniyyaa | ሁሴንዬ ሰላም ላንቱ ይሁን |
| Kunoo ijolleen ganda saakinaa | እኚው ልጆች ሰላም ያለበት ቦታ |
| Abbaa arabuun mala naa himaa | አባ አረቡ መላ በኗቸው። |

የመጨረሻዎቹን ሁለቱን ስንኞች ከዋኟ ያለማቋረጥ በነቃ ሁኔታ ትለዋለች። ተቀባዬቹም እሷን ተከትለው ባለችው ድምጸት ይቀበላሉ።ይህ ቃላዊ ግጥም በሚባልበት ወቅት "ቅብብሎሽ" ዋነኛ የመቅረቢያ መንገዱ ነው። ከዋኟ እነሱ መጨረሳቸውን ካረጋገጠች በኋላ ይህንኑ ቃላዊ ግጥምለሁለተኛ ጊዜ ትደግመዋለች። እነሱም የሷን መጨረስ ተከትለው ባለችው አይነት ድምጸት ይላሉ።በዚህ ሰዓት ጭብጨባው፣ ድቤውና አሸቁው ተጨምሮበት

መንዙማው ይደራል።ከዚያም ከዋኟ የነሱን ማጠናቀቅ ተከትላ ከመጀመሪያው በተለየና ረጋ ብላ የጥያቄ መንፈስ ባዘለ ድምጸት "kunoo ijollen ganda saakinaa" ስትል ተቀባዮቹ በአንድ ድምጽ "abbaa arabuun mala naa himaa" በማለት ምላሽ በሚሰጥ አይነት ድምጸት ይመልሳሉ።አሁንም ቀበል አድርጋ "kunoo ijoollen ganda saakinaa " "abbaa arabuun mala naa himaa" የሚል ምላሽ ታገኛለች።ከዚያ ተቀባዮቹ በመመሰጥ ጭንቅላታቸውን ከላይ ወደ ታች በማወዛወዝ ምእመኑ በአንድ ድምጽ "እስ" "እስ" "እስ" እያሉ ቁጭ ባሉበት እጃቸውን ወደ ላይ ወደ ታች እያደረጉ በማጨብጨብ (shubbisaa) ጭፈራ ያካሂዳሉ። የዚሁ መንዙማ ግጥም ከክዋኔው ሂደት ባሻገር ይዞ የተነሳውን ይዘት ስንመለከት ከዋኟም "salaamualaykum huseniyyaa salaamualaykum huseniyyaa kunoo ijollen ganda saakinaa abbaa arabuun mala naa himaa" በማለት ለሸከናሁሴን ሰላምታ በማቅረብ፤ ምእመኑ ደግሞ የሰላም ቀበሌ /ጣቢያ/ በሆነበት የአባ አረቡ ግቢ ውስጥ በመገኘቱና አባ አረቡ መፍትሄ /ከችግራቸውነጻ የሚሆኑበትን መንገድ/ እንዲፈልጉላቸው መጠየቋን ታሰማለች። ታዳሚውም እሷ ያለችውን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መቀበሉንና ጥያቄዋ የነሱም ጥያቄ መሆኑን ለመግለጽ ጭንቅላታቸውን ወደ ላይ ወደ ታች በማወዛወዝ፣ እንዲሁም ሞቅ ባለ ጭብጨባ በመታጀብ "እስ" "እስ" "እስ" እያሉ ጥያቄያቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ከልባቸው /ከውስጣቸው/በአንድ አይነት ስሜት ያሽቃሉ።ይህን ባለ አራት ስንኝ መንዙማ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁለተኛ ጊዜ ካለችና ካስባለች በኋላ ወደ ሌላ አዝማች ትገባለች።

Allahumma irhaam sheek huseen ፣

Isiin waamti sabiyyin ፣

Abbiyyoon shumataniruu abiyyiin ።

የሚለውን አዝማች ለሶስት ጊዜ ደጋግማ ካለችና ካስባለች በኋላ የመጨረሻውንና ሶስተኛውን ስንኝ ለአምስት ጊዜ ደጋግማ በማለት ተቀባዮቹ እሱኑ ደግመው እንዲሉ እድል ትሰጣቸዋለች። ይህ ቃላዊ ግጥም በነዚህ "3" ስንኞች የተገነባ ሲሆን አዝማቹን ከዋኟ /አቀንቃኟ/ ካለች በኋላ ተቀባዮቹ እሷ ባለችው ድምጸት ተከትለዋት ይላሉ።የነሱን መጨረስ ካረጋገጠች በኋላ ደግማ ይህንኑ ስንኝ ትላለች።የተቀባዮቹን ደግመው ማለት ካረጋገጠች በኋላ በመመሰጥ ዱፊውን በአንድ እጇ ብቻ በመምታት አንዱን እጇን ዱፊው እንዳይነቃነቅ በማስደገፍ ጭንቅለቷን ወደ ላይ ወደ ታች እያወዛወዘች የመጨረሻውን "abbiyyoon shumataniruu abiyyiin" የሚለውን ስንኝ በመደጋገም እንዲሉ ተራዋን እየጠበቀች ለአምስት ጊዜ ትላለች፤ተቀባዮቹም ይላሉ።

ይህንም ቃላዊ ግጥም የተመለከትን እንደሆነ ስንኞቹ አጭርና በፍጥነት የተሞሉ ሲሆኑ የማቅረቢያ መንገዳቸውም እንደ መጀመሪያው "በቅብብሎሽ" ነው።ከክዋኔው ባሻገር የተነሳውን ይዘት ስንመለከት ከዋኟ "አለሁ መርሀም ኑር ሁሴን፤ ኢሲን ዋምቲን ሰብይን፤አብዮን ሹመተኒሩ አብይን" በማለት ኑር ሁሴን የኛ አለቃ፤ መሪ። ህጻን እኳን ሳይቀር በሳቸው የሚመካ፣ የኛ አባት፣ ለኛ የሚሆነውን መሪ ላኩልን። አብይን የሾሙት /ስልጣንየሰጡት/እሳቸው ናቸው።እሳቸው የሁሉም አለቃ ናቸው።የሚለውን የመወድስ ግጥም ስታዜም እነሱም ይህ ውዳሴ ይገባቸዋል።በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ለመስጠት በዜማ በታገዘው ቃላዊ ግጥም፣ በጭብጨባና በተመስጦ

አንገታቸውንና ጭንቅላታቸውን በአንድ በማወዛወዝ "እሰ"፣ "እሰ" ፣"እሰ" የሚለውን የማድመቂያ ቃላቸውን በመጠቀም (ሹቢሳ) ጭፈራ ያካሂዳሉ።በዚህ ክዋኔ ወቅት አቀባይዋ ሴት ስትሆን ተቀባዮቹ የሁለቱም ጾታዎች ናቸው።

በዚህ ቃላዊ ግጥም ክዋኔ ወቅት አጠገቤ ለነበሩት ለሼህ አብደላ ሙሳ፤ ይህ ቃላዊ ግጥም በሴት አቀንቃኝነት ብቻ ነው የሚባለው? ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ፡-

"ወንድ ሴት የሚባል ነገር የለም። ግጥም የማፍለቅ ብቃት ያለው ማንም ሰው ማለት ይችላል።ለዚህ ነው እሷ ስትደጋግም የሰማሸው። ደግሞም እሷ አቀንቃኝ ትሁን እንጂ እኛ ባንቀላቀልበት ኖሮ መች ሞቅ ይልላት ነበር።" በማለትቀልድ የተሞላበት ምላሻቸውን ሰጥተውኛል።

ከላይ የተመለከትናቸው በዱሬ የሚባሉ ሁለት ቃላዊ ግጥሞች ባለ አጭር ስኛኞች ሲሆኑ ሁለቱም የመንዙማ ግጥሞች ላይ ያስተዋልኩት መሰረታዊ ነገር እንደ መንዙማ ባዮቹና እንደ መንዙማው አይነት የክዋኔው አይነት እንደሚለያይ ነው። ለአብነት ያህል ከላይ የቀረበውን ባለ ሶስት እና ባለ አራት የመንዙማ ግጥም አዝማች /መለያ/ ለማለት የሚጠብቁት የጊዜ ፍጆታ ረዘም ያለ ሲሆን ፤ቀጥለን በምንመለከተው የመንዙማ ክዋኔ ግን የከቃኙንና የተሳታፊዎቹ ሚና በአዝማቹ ስንኝ ላይ ቅብብሎሽ በማካሄድ (የቦታ ለውጥ በማከሄድ) እኩል መጠን ሲደርሳቸው፤አዝማቹን ተከትለው በሚገቡት ተከታታይ ዘርዛሪ ስንኞች ግን ጀማሪ በመሆኗ የተወሰነ የበለጠ ድርሻ በክዋኔ ወቅት ሲደርሳት እንመልከት፡-

ከዋኝ፡- አሰላት ወሰላም አላ፣

ተቀባይ፡- አህለን ነቢ፣

ከዋኝ፡- ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ። ሶስቱም ስንኞች የቃላዊ ግጥሙ አዝማቾች ናቸው።

በዚህ ቃላዊ ግጥም አጀማመር በክዋኔ ወቅት ያስተዋልኩት ነገር ገና ከዋኟ "አሰላት ወሰላም አላ›› የሚለውን ስንኝ በምትልበት ወቅት ተቀባዮቹ በአንድ ድምጽ "አህለን ነቢ" የሚል ምላሽ ሰጧት።በቃላዊ ግጥሙ በከዋኝና ታዳሚ መካከል በግጥሙ ዙሪያ ቤተሰባዊነት ስሜት እንዳለ ለመረዳት አስችሎኛል። በዚህ ቃላዊ ግጥም አዝማች ከዋኟ "አሰላት ወሰላም አላ" በማለት "በነብዩ መሀመድ ላይ ራህመት ይውረድ" እያለች ስትመኝ፤ተቀባዮቹም ያንኑ በመመኘት የነሱ እንዲሆኑ "አህለን ነቢ" በማለት ይቀበሏታል። እሷም ‹‹አንቱ የመዲና ሙሽራ›› በማለት ታቀላምጣቸዋለች። ከዚህ በኋላም ቃላዊ ግጥሙ በከዋኝና ተቀባይ በደመቀ አካሄድ እንደሚከተለው ቀጠለ።

| **ቃላዊ ግጥሙ በኦሮመኛ** | **ቃላዊ ግጥሙ በአማርኛ** |
| --- | --- |
| ከዋኝ፡-sayyidi jechuun isaani | ጌታ ማለት እሳቸው ነቸው |
| ተቀባይ፡-Ahlen nabii | አቤት በሉኝ(ተቀበሉኝ) |

| | |
|---|---|
| **ከዋኝ፡**-Qulqullu akka bishaani | **እንከን የሌለቦት(እነደ ወሀ የጸዱ)** |
| **ተቀባይ፡**- Assalaat wesselaam alaa | **የአለህ ራህመት ላንቱ ይሁን** |
| **ከዋኝ፡**- Ahlen nabii | **አቤት በሉኝ(ተቀበሉኝ)** |
| **ተቀባይ፡**-Musxefaa[42] arrusan xaybaa | **አንቱ የመዲና ሙሽራ(ቀንጆ)** |

**በዚህ ቃላዊ ግጥም (መንዙማ) ከቀረበበት መንገድ በተጨማሪ ያስተዋልኩት ነገር ነብዩን የሚያሞካሽ(የሚያሞግስ)እና በዚሁ ስር ቀጥለው የሚመጡት ስንኞች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው መሆናቸውን ነው።**

| | |
|---|---|
| Amma gaheeraa mootii koo | **ቅጣቴ አሁን ይበቃል ጌታዬ** |
| Ahlan Nabii | **አቤት በሉኝ ነቢ(ተመልከቱኝ)** |
| Naaf haa laalamuu doseen koo | **ማመልከቻዬ ይታይልኝ** |
| Assalaat wassalaam alaa | **የአላህ ራህመት ባንቱ ላይ ይውረድ** |
| Ahlan Nabii | **አቤት በሉኝ(ተመልከቱኝ)** |
| Musxefaa Arrusan[43] xayyibaa | **አንቱ የመዲናው ሙሽራ(ቀንጆ)** |
| Utuuman ka'ee adeeme | **እንዲሁ ተነስቼ ብሄድ** |
| Ahlan Nabii | **አቤት በሉኝ ነቢ(ተመልከቱኝ)** |
| Madinaa gahee hin buluree | **መዲና ደርሼ ላድረም ወይ** |
| Assalaat wassalaam alaa | **የአለህ ራህመት ባንቱ ላይ ይውረድ** |
| Ahlan Nabii | **አቤት በሉኝ ነቢ(ተመልከቱኝ)** |
| Musxefaa arrusan xaybaa | **አንቱ የመዲናው ሙሽራ(ቀንጆ)** |

**እያለ ቃላዊ ግጥሙ (መንዙማው) በዚህ አይነት መልኩ እስከ ፍጻሜው የሚቀጥል ይሆናል።እዚህ ላይ ከላይኞቹ ሁለት መንዙማዎች በተለየ መልኩ ከዋኟ አንድ ስንኝ ካለች በኋላ ሌለውን ስንኝ ለመቀጠል "አለን ነቢ"**

**[42]ሙስጠፋ ፡-በዚህ ቃላዊ ግጥም ለነብዩ የተሰጠ ስም ነው።**

**[43]አሩሰ፡-የሚለው ቃል ኦሮመኛ ሲሆን ሙሽራ የሚለውን ፍቺ ይይዛል።በዚህ ቃላዊ ግጥም አገባብ ግን "ሙሽራ" ቀንጆ፣የተዋቡ፣የተኳሉ መሆናቸውን ለመግለጽ የገባ ነው።**

የሚለውን አዝማች የምትጠብቅ መሆኑን ሲያሳይ ሁለት ተከታታይ ስንኞችን ካለች በኋላ ደግሞ በአዝማቹ አስረግጣ ዘግታ ካለች በኋላ ወደ ሌላ ስንኝ ስትሻገር በመንዙማው ግጥም አስተውያለሁ። ከዚህም ከተቀባዮቹ እሺታን ካላገኘች ሌላ ስንኝ የማትቀጥል መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ።ከዚሁ ጎን ለጎን ተቀባዮቹም ቢሆኑ ከዋኟ ቀድማ ካላለች የማይሉ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ።

በአጠቃላይ ይህ የሚያስረዳው በዱፊ የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞች የከዋኝንና የተቀባይን ትልቅ ድርሻ የሚጠይቁ መሆናቸውን ነው።

### 4.3.2 **በእንጉረጉሮ የሚቀርቡ መንዙማዎች**

በእንጉርጉሮ የሚቀርቡት መንዙማዎች ብዙ ጊዜ በአንድ ሰው የሚባሉ (የሚከወኑ) ሲሆን አልፎ አልፎ ግን በጋራ ይከናወናሉ። በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ላይ በነበረኝ የቀጥታ ምልከታዬ በእንጉርጉሮ ሲቀርቡ የነበሩት መንዙማዎች በአጠቃላይ በጋራ ሲከወኑ የነበሩ ናቸው። ይህንንም በተመለከተ የመውሊዱ አስተባባሪ ከነበሩት ሸህ መሀመድአሚን አብዱልዋሂድ ጋር በቀን 12/03/11.ዓ.ም ባደረኩት ቃለመጠይቅ፡-

በእንጉርጉሮ የሚቀርቡ መንዙማዎች "ዚክር" በመባል ይጠራሉ።ይህ የሚባለው በአንድ ጥሩ ድምጽ እና ግጥሞችን የማፍለቅ ብቃት ባለው ሰው የሚከወን ነው።ጥሩ ድምጽ እና ግጥሞችን የማፍለቅ ብቃት ብቻም በቂ አይደለም።ለምሳሌ፡- "ዚክር" ትርጉሙ  ማስታወስ ማለት ነው። ስለዚህ ሀይማኖታዊ የሆነ እውቀት ያስፈልጋል ማለት ነው።የሚዘከረው የፈጣሪ ትልቅና፣የነብያት ገድል፣የኡለሞች ታሪክና ማህበራዊ ችግሮችን ለማቃለል ወዘተ…ሊሆኑ ስለሚችሉ አንድ መንዙማ የሚያደርግ ሰው በግጥሙ እነዚህን ነገሮች ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል።  እዚህ እንደምትመለከችው ዚክር ሲደረግ የነበረው በአንድ ሰው አስጀማሪነት ይሁን እንጂ በጋራ ነው ሲከወን የነበረው። ምክንያቱም መውሊድ በራሱ የአንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን የሙስሊሙ ማህበረሰብ በመሆኑ፤ከዚያ ጋር ተያይዞ ነው በጋራ ሲከውን  የነበረው።ለምሳሌ፡- አንድ ግለሰብ የግል ብሶቱን ቢሆን የሚገልጸው በጋራ ከሚያንጎራጉር በግል ብቻውን ቢለው፤ የበለጠ ስሜቱ ፈንድቶ ይወጣለታል።እና መውሊድ ላይ በጋራ በመሆኑ ነው ብለውኛል ።

[44]ይህንኑ ርእስ በተመለከተ ብርሀኑበ1990 ዓ.ም "የወሎ ሙስሊሞች ቃል ግጥም በሚል ርዕስ በቀረበው ጥናት"የወሎ ኢስላማዊ ግጥሞችን በአራት በከፈለበት ምዕራፍ፡-"አራተኛው የግጥም ዘር ሀዬ ሲሆን ራስን የሚገልጽ እንደሆነ ያስረዳል።ይህ ዘር መድህኒትነት ያለው፣ ተከታታይ ሙዚቃዊና ግለሰብን የሚገለጽ ግጥም የሚቀርብበት ነው።ግጥሙ በወንዶችም በሴቶችም ይቀርባል።የዚህ ግጥም የታወቁ አጋጣሚዎች ወዳና ሀድራት ናቸው።አንዳንዴ በሌሎች እስላማዊ አጋጣሚዎች ሊቀርብ ይችላል። ሀዬ በአንድ ከዋኝ ብቻ የሚቀርብ የግጥም አይነት ነው።የዚህ ግጥም ታዳሚዎች ከዋኙን በጽሞና ከማዳመጥ ያለፈ ሚና የላቸውም።ይህ የግጥም አይነት እንደ ሌሎቹ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመርም የለውም። በማለት ገልጸዋል።

እዚህ ላይ በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔ ይህ ዘር ሲከወን በቡድን አንድም ሆነ በቡድን ሁለት በውሊዱ ላይ ግን በአንድ ከዋኝ ብቻ የሚቀርብ የግጥም አይነት እንዳልሆነ ታዳሚዎችም ከዋኙን ከማዳመጥ ያለፈ ሚና እንዳላቸው ቢሆንም በከዋኝና ታዳሚ መካከል ያለው ቅብብሎሽ ፈጣን ምላሽ የነበረው ሳይሆን ጊዜ የሚፈልግ ነው።ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ላይ የሚቀርቡት የግጥም አይነቶች እንደ ሌሎቹ ግጥም አይነቶች የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመር እንዳላቸው ለማረጋገጥ ችያለሁ።

ይህንን ክዋኔ ለአብነት በተመለከተው የመንዙማ ግጥም ውስጥ እንመልከት። ይህ መንዙማ ከመጀመሩ በፊት ከዋኙ በዱአው ውስጥ ሲያነሳቸው የነበሩትን ሀሳቦች ሙሉ በሙሉ አንጸባርቀዋል።የተደረገውም ዱአ ለአንድ በእድሜ የገፉ እናት ከበሽታቸው ይላቀቁ ዘንድ እና ረጅም እድሜ እንደሚመኙላቸውበዱአው ክፍል ሲነሳ ተስተውሎዋል። ይህ ሀሳብ በራሱ ወደ መንዙማ ሲቀየር ከዱአው በቀጥታ በኺው ዱአ አድራጊ

አለሁ መርሀም ኑር ሁሴን.......ንዮ.........

በማለት ሲጀምሩ፤

ተቀባዮቹ ..........አ.......አ...........ኑር ሁሴን...ንዮ በማለት ይቀበላሉ።በእንዲህ አይነት መልኩ ከተቀበሉት በኋላ እነዚህን አራት ስንኞች

Nama Rabbin dhaqii jadheetu Nuraa bira dhufaa

Ani innan dhufee barri duubaan qilxuu jalaan kufaa

Dudduubbeen boroodhaa isa kessaa jaartii kanattii

Umrii dheerina taa'u jaartii kanaatti naa tuufaa

በተረጋጋ እና በተመሳሳይ ሁኔታ ይሉና አምስተኛውን

Yaa Abbaa Arabuu galmee rakkoo nurraa cufaaMaaliif of gad qabuun dhufaa

ካሉ በኋላ ኤ……ኤ……ሲሉ ከዋኞቹ፤ተቀባዮቹ ኤ…ኤ…ሼክ ሁሴንዬ…በማለት ቀስ ባለ ድምጸት እየተንጎራጎረ እስከ መንዙማው ማጠቃለያ ይደርሳል።በዚህ ክዋኔም በቀጥታ በነበረኝ ምልከታ እንዳስተዋልኩት ከዋኙ ታዳሚዎቹን ካስጀመራቸው በኋላ ተከታታይ ያሉት ስንኞች ፍጻሜ አገኝተው እንዲቀበሉ መልእክት እስኪያሳያቸው ድረስ ትከሻና ራሳቸውን ከግራ ወደ ቀኝ እያወዛወዙ በተመስጦ አልፎ አልፎ አንዳንዶቹ አይናቸውን ጨፍነው ሲያደምጡ አስተውያለሁ።ልክ ስንኞቹን ጨርሶ ኤ… ኤ…ሲል በአንድ አይነት ድምጽ ተቀባዮቹ ኦ…ኦ…ኑር ሁሴንዮ….በማለት ይቀበላሉ።

አብዱራህማን (2007) “የሸህ ሁሴን ዳንግላ የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔ እና ቃላዊ ግጥሞች ትንተና” በሚለው ጥናቱ ቃላዊ ግጥም (እንጉርጉሮ) የሚቀርበው በሚለው ክፍል ጥናቱ፡-

ይህ ዘር በዚህ የሞሊድ በዓል ላይ በሴቶች እንደማይባል፤ ታዳሚዎቹ ከዋኙን በፅሞና ከማዳመጥ ያለፈ ሚና እንደሌላቸው እና፤ በዱፊ እንደሚቀርቡት መዙማዎች የመክፈቻ እና የመዝጊያ ቀመር እንደሌለው በጥናቱ ገልፆዋል።

በአጠቃላይ እነዚህን ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ በቦታው ተገኝቼ ስከታተልና በተመሳሳይ ርዕስ ከተጠና ጥናት ካገኘሁት መረጃ በመነሳት የቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔ በተመለከተ ሶስት ነገሮች ለመጠቆም እወዳለሁ።

የመጀመሪያው በቁባ አባ ረቡ የመውሊድ በኣል ላይ የሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች መወድስነታቸው ነቢዩ መሐመድን እና አውሊያን (ኡለሞችን) ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቃላዊ ግጥሞቹ በአብዛኛው ማንነትን የሚገልፁና “እኛ” በሚል ድምፀት የሚቀርቡ ናቸው። ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ በተመሳሳይ ጥናት፣በተመሳሳይ ርዕስ፣ በተመሳሳይ የመከወኛ ዘዴ ተጠንቶ ለውጤቱ መለየት የጥናቱ አካባቢና ባህል ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ በዚህ ጥናት ትልቅ ግንዛቤ የሚሰጥ መሆኑን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ነብዩ መሐመድን እና አወሊያዎችን ለማወደስ በመውሊድ ክብረ በዓል ላይ የቀረቡት የመንዙማ ግጥሞች በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ ፣ ፎክሎራዊና ኪነጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው። ግጥሞቹም በእርግጠኛነት ማን ደረሳቸው የሚለውን ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የተለያዩ የታሪክ፣ የስነ-ቃል እና የፎክሎር መረጃዎችን በጥንቃቄ ማሰባሰብ የሚጠይቅ ቢሆንም በክዋኔ ወቅት በምልከታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት ከ50% ቦታው የቀረቡት መንዙማዎች ስንኝ የሚዋቀሩት ከዋኔው በሚመለከታቸው እንዲሁም በሚመኛቸው እና አሁን ባለው ተጨባጭ የሀገሪቷ ሁኔታ ላይ ሲሆን፤ ሌላው 50% ደግሞ መንፈሳዊ ዕውቀት የሚጠይቁና ከትውልድ ትውልድ በቃል ሲተላለፉ የመጡ ናቸው። በዚህም ምክንያት የመጀመሪያዎቹን 50% ድርሰት የማናቸው የሚለውን ለመመለስ የከዋኚው/ኟ/ የድረሳ ብቃት ውጤት እንደሆኑ ለመናገር ያስደፍራል።

የፎክሎር ጥናት እና ምርምር፣በተለየም ክዋኔን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ እያንዳንድ የክዋኔው ሂደቶች ምንነት እና ለምን እንደተከወኑ ጭምር መገለፅ እንዳለበት ትኩረት ሰጥተው ያትታሉ።በዚህ መውሊድ በዓልም የቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ባስተዋልኩበት ወቅት መዙማውን በዋናነት ሲሉት (ሲያቀነቀኑት) የሰማሁት በሁለቱም ፆታዎች በመሆናቸው መንዙማውን ለማቀንቀን (የክዋኔው መሪ ለመሆን) ምን ያስፈልጋል? የመንዙማዎቹ ድረሳ መቼ እና እንዴት ይከወናል? የተፈቀደውስ ለማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቼ ጠይቄ ነበር።

ከዚህም ለመረዳት እንደቻልኩት መንዙማ እራሱን የቻለ ጥበብ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ተሰጦዎችን ይፈልጋል። የመጀመሪያ መንፈሳዊ ዕውቀትና ግጥም የማፍለቅ ብቃት ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የተዘጋጀውን ግጥም በሚስብ እና በሚማርክ ድምፅ አሳምሮ ማዜም ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአሁኑ ሰዓት የሚደመጡት ግጥማቸው ከዚህ በተፃፉና ለብዙ ዘመን የቆዩ ተደጋግመው የሚታወቁ ሲሆኑ ወቅቱን እና ሁኔታውን ተገን አድርገው በከዋኙ በዕለቱ እና በቦታው የሚገጠሙ ግጥሞች ይኖራሉ። እነዚህ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ግጥሞች ደግሞ ግጥማቸውም ሆነ ቅላፄአቸው በብዙ አካባቢ ይታወቃል። ሁኔታዎችን እና አጋጣሚዎችን በመጠቀም የሚደረሱ ግጥሞችን በተመለከተ በቦታው ለነበረ ሰው እዚህ ነው ለማለት ምንም አስቸጋሪ አይሆንበትም። በቦታው ለሌለውም ፍንጭ የሚሰጥ ነገር አለው።

ለምሳሌ ክዋኔው አባአረቡ ላይ ከሆነ የአባአረቡ ስም ይገባበታል። ደሬ ሸከና ሁሴን ላይ ከሆነ እንደዚሁ። ስለዚህ በዚህ መልኩ የት ነው ለሚለው ምላሽ ይሰጣል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቀን 15/03/2011 ዓ.ም ከወ/ሮ አለውያ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡- የመዙማ ቃላዊ ግጥሞችን ለማቀንቀን የተፈቀደውስ ለማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ከሰጡኝ ገለፃ እንደተረዳውት፤

የመንዙማ ዕውቀት ካለው ፆታ እንደማይገድበው እና ተደባልቀው ማዜም እንደሚችሉ ነው። ነገር ግን በአካባቢው ባህል በየመስኪዱ የሚከበሩ መውሊዶች ሲኖሩ ወንዶቹ በመስኪድ ከኢሻ ሰላት በኃላ “ዱአ” የሚቀመጡት መንዙማው በወንዶች ብቻ ይከወናል። በተመሳሳይ መልኩ “ደረማ” በሴቶች ብቻ የሚከወን የዱአ ስርዓት ማለት ነው። በዚህ ጊዜ በዚህ የክዋኔ ቦታ ወንዶች አይደርሱም፤ ሴቶች ብቻ ይከውኑታል። ከዚህ ባለፈ በእንዲህ አይነት (በቀባ) በሚከወነው የመውሊድ በዓል ስርዓት የመዙማ ሂደት የፆታ ልዩነት አያደርግም።

የዚህንም ምክንያት (የስርዓተ ክዋኔው ዋዜማ) በሚለው ክፍል በቀን08/03/2011 ዓ.ም ከአባመጫ አባአረቡ (የአባ አረቡ ካዳሚ) ከሆኑት ሸማግሌ ጋር ያደረኩትን ቃለ መጠይቅ ልብ ይሏል።

### 4.4 የቁባአባአረቡየመውሊድክብረበዓልንለማጀብየገቡቁሳዊባህሎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ የመውሊድ ክብረበአል ክዋኔ ለማጀብ ወይም ለማድመቅ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች መካከል ለመተንተን ይመች ዘንድ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የገቡ፣ የመመገቢያና ጌጣጌጦች በማለት በሶስት ምድብ

በመክፈል የቁሳዊ ባህሎችን ጠቀሜታና አሰራር ለመዳሰስና ማህበራዊ ፋይዳቸውን ለመግለፅ ሞክሬያለሁ። እነዚህን ቁሳዊ ባህሎች መመልከት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ክብረ በዓል ሲታሰብ ከበራዉን ሙሉ ከሚያደርጉት አላባዊያን መካከል አንዱ በመሆናቸው ነው።[45]

***ምስል ስምንት ፡ ቁሳዊ ባህሎቹን የሚያሳዩ  ፎቶዎች***





[45]**ይህንሀሳብበተመለከተም** Sims **እና** Stephens (2005፣95) **እንደሚከተለውይገልጹታል።**

…Rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and costumes…

ስለ ቁሳዊ ባህል ሲነሳ በመጀመሪያ በአእምሯችን የሚመጣው ቁሳዊ ባህል ዋና ትኩረቱ የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታውን ተጠቅሞ የሚያመርታቸውን ተጨባጭ የሆኑ የመገልገያ መሳሪያዎችን የአሰራር ቴክኒክ በተለይም በባህላዊ መንገድ የተዘጋጁትን ቁሶች የሚመለከት መሆኑን ነው። እርግጥ ነው የቁሳዊ ባህል ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ ቁስ ነው።ይሁን አንጂ ቁሱን ብቻ ተመልክቶ ቁሱ የተሰራበትን ንጥረቁስ እና አገልግሎት መግለጽ ብቻውን በቂ አይሆንም። የጥናት መስኩ አላማም አይደለም።ዋና ጉዳዩ ቁሱን ስለሰሩት የሰው ልጆች ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ሀይማኖታዊ፣ኢኮኖሚያዊ …ወዘተ ጉዳዮች እያነሱ መፈከር ነው። በዚህም መሰረት በመውሊድ ክብረ በዓል ያስተዋልኳቸውን ቁሳዊ ባህሎች በቅደም ተከተል ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

### 4.4.1 የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች (ዱፊ፣ኡሌዱፊ እና አሸቁ)

*ሀ. Duffii (ድቢ)*

ዱፊ በመውሊድ በዓሉ ላይ የቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔ ለማድመቅ ከሚገለገሉበት ቁሳዊ ባህል ውስጥ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። ይህ መሳሪያ በተለያዩ የእስልምና ክብረበዓሎች ላይ በሰፋት ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በመውሊድ በዓል ደግሞ የተለየ ስፍራ ይሰጠዋል። ለዚህየሚጠቀሰውን ምክንያት በተመለከተ ከሼህ ሙሳ አብደላ ፣ ከወ/ሮ አለውያ እና [46]ከ/አቶ አንዋር ሁሴን በቀን 13/03/2011ዓ.ም በነበረኝቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ አግኝቻለሁ።

> ዱፊ የእስልምና እምነት ተከታዮች ከሚጠቀሙበት መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው፡ ሩቅ ቦታ እንኳ ሆነሽ የዱፊን ድምጽ ስትሰሚ በአዕምሮሽ የሚመጣው ይህ እምነት ነው። በቅርብ ሆነሽ ስትሰሚው ደግሞ የሚሰጥሽ ነሻጣ (ንቃት)ይህ ነው የሚባል አይደለም። ውስጥሽ ላይ ከፍተኛ የሆነ ደስታ ይፈጥራል።እስከ እግርስ ጥፍር ድረስ የሚሰማሽን ደስታ ነው የሚፈጥርልሽ።…

ዱፊ እንጨት ተቀርጦ ተጠርቦ ይሰራል።የእንጨቱ አይነት አንበቤሳ፣ ዋንዛ፣ ቀረሮ፣ ብሳናሊሆን ይችላል። አሰራሩንም በአጭሩ ለመግለጽ ያህል፤በመጀመሪያ የተቀረጠው እንጨት እንደ "ቶቶ" (ተጠርቦ የተሰራ የጎድጓዳ ሳህን ቅርጽያለው) አንድ ተመርጦ የተዘጋጀው ክብ እንጨት ይፈለፈልና እንዲጎደጉድ ይደረጋል።በመቀጠል ይህ ተጠርቦና ተፈልፍሎ የተዘጋጀው እቃ በኩበት ቀዳ ይለበጣል።ከዚህ በመቀጠል ከቆዳ በሚዘጋጅ ጠፍር ይሰፋል። ከዚያ ላንድ ሳምንት ያህል እንዲደርቅ ጸሀይ ላይ ይቆያል።በመጨረሻም ደርቆ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ቡኮ(ሊጥ) ይቀባል። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ጥሩ ድምጽ እንዲያወጣ በሚል እሳቤ ነው።ከዚህ በኋላ ለጥቅም ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል።በዚህ ላይ ሁል ጊዜም ቢሆን ጥሩ ድምጽ እንዲሰጥ ዱፊ ከመመታቱ በፊት ጸሀይ ወይም እሳት ይሞቃል። መንዙማ በሚባልበት ጊዜ ዱፊ መቺው ሰው የተመረጠና ልምድ ያለው ሰው

መሆን አለበት።ምክንያቱም የከዋኙን የአፍ እንቅስቃሴና የድምጸት ቅየራ በቅጽበት መረዳትና ምቱን መቀየር መቻል አለበት።ይህ ካልሆነ የክዋኔው ሂደት ስለሚስተጓጎል ተሳታፊዎች ፍዝ ይሆናሉ።ክዋኔ ደግሞ ንቁ ተሳታፊዎችን እነጂ ፍዝ ተሳታፊዎችን አይፈልግም።

### ለ. *Ulee Duffii* (**የድቤ መምቻ**)

ኡሌ ዱፊ(የድቤ መምቻ) ሁለት አጫጭር ዱላዎች ከባህርዛፍ፣ከቡና፣ከዘይቱና ወዘተ. ሊዘጋጁ የሚችሉ ሲሆን ጫፋቸው በጨርቅ ይጠቀለላል።ይህም የሚሆነው በሁለት ምክንያት ሲሆን፤ አንደኛው ዱላው ድቤውን እንዳይጎዳው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጥሩና ወፈር ያለ ድምጽ እንዲሰጥ ነው።

### ሐ. *Ashiqee* /**ከበል**/

አሽቄ /ከበል/ ከእንጨት የሚሰራ ማጨብጨቢያ ሲሆን ዱፊውን በማጀብ መንዙማውን የሚያደምቅ ነው። አሰራሩም ሁለት ትናንሽ ጣውላዎችን ባላ በመሰለ ቅርጽ አጠላልፎ ጫፍ ላይ በማሰርና በአንድ እጃቸው ይዘው ሲያንቀሳቅሱት ደመቅ ያለ የጭብጨባ ድምጽ የሚፈጥር ባህላዊ መሳሪያ ነው።ይህን መሳሪያ አልፎ አልፎ የተወሰኑ ቡድኖች ብቻ ይጠቀሙበታል።

> ይህን መሳሪያ ከአርሲ ድሬ ሸከና ሁሴን የመጡ ሰዎች በብዛት ይይዙታል። ምክንያቱም የአመጣጡ ታሪክ ከዚያ በመሆኑ ብቻ ነው በነዚህ ሰዎች ብቻ ሊያዝ የቻለው።የአሽቄ መኖር አለመኖር በመውሊዱ ላይ የሚያጎድለው ነገር የለም። ነገር ግን አሽቄ ስትኖር በትንሽ ሰው ሀድራው ይሞቃል።ከሌለች ደግሞ የብዙ ሰው እጅ ጭብጨባ ይፈልጋል ማለት ነው።ከዚህ ውጭ የሚያመጣው ነገር የለም።[47] በማለት ይገልጻሉ።

[47]ከሽህ ሙሳ አብደላ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ



4.4.2 **በኩብረ በዓሉ ለመመገቢያ የዋሉ ቁሳዊ ባህሎች**

*የመመገቢያ ቁሶች ስንል ለመመገቢቢያም ሆነ ለመጠጫኒነት የሚውሉትን ቁሶች የሚያጠቃልል ሲሆን፤ከላይ በዚሁ ርዕስ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው ለየት ያሉትን  የሰው ልጅ ተጠቦ ጥበቡን ተጠቅሞ ከባህላዊ ቁስ ያበጃቸውንና ዘወትር በየሰፍራው የማናገኛቸውን፤ማለትም በዚህ መውሊድ በዓል ስርዓት ላይ ጎልተው የሚታዩትን ቁሳዊ ባህሎች ብቻ ነው።እነዚህንም ለመተንተን ያመች ዘንድ የመመገቢያና የመጠጫ ቁሶች በማለት በሁለት ከፍለን እንመልከት።*

### 4.4.2.1 *የመመገቢያ ቁስ*

#### *ሀ.Maaddii (የእንጨት ትሪ)*

*ማዲ (ከእንጨት የተሠራ ትሪ) እንጨት ተቀርጦ ተጠርቦ ይሠራል። የእንጨቱ አይነት በብዛት ዋንዛ ነው። አሠራሩንም በአጭሩ ለመግለፅ ያህል፤በመጀመሪያ ትልቅና ሰፋት ያለው ዋንዛ ተመርጦ በክብ ክብ ቀጠን ቀጠን ተደርጎ ይቀረጣል። ከዚያ ዳር ዳሩ ጎድጎድ ያለ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ይጠረባል። በመቀጠል የተጠረበው ዝርግ*

(ትሪ) ዉበት እንዲኖረው በመስታወት ስባሪ (በብርጭቆ ወረቀት) ይታሻል። እንዲህ ከተዘጋጀ በኋላ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ለአንድ ሶስት ጊዜ የከብት ሞራ በመቀባት እንዲጠጣ ይደረጋል።

ይህን የሚያደርጉት ጥንካሬ እንዲኖረው እና እንዳይሰነጠቅ በሚል እሳቤ ነው። ከዚህ በኋላ ለጥቅም ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል። ማዲ(የእንጨት ትሪ) አገልግሎት የሚሰጠው ለእንጀራ ለገንፎና ለጨጻ ሲሆን ገንፎ በሚሆንበት ጊዜ በባህሉ መሰረት የቀጮ ቅጠል መሀሉ ላይ ጣል በማድረግ ገንፎውን በላዩ ይጭኑበታል። ይህ ቅጠል ያስፈለገበት ምክንያት ገንፎ ከማዲው ጋር እንዳይያያዝ በሚል ሀሳብ ነው።

*ለ. Gilgilii* ***(አገልግል)***

አገልግል በመወሊድ በአል ላይ ብቻ ያተኮረ ቁሳዊ ባህል ሳይሆን፤ለመውሊድ በአል ከፍተኛ አስተዋፆኦ ከሚያደርጉ የመመገቢያ ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው። ይኸውም ምእመናን ወደ ስፍራው ለመጔዝ ሲያስቡ ጊዚያዊ ረሀባቸውን ለማስታገስና አካባቢውን እስኪለማመዱት በዚህ እቃ በመቋጠር ከቤት ያመጡትን ምግብ ይጠቀሙበታል።

አገልግል ከስፌትና ከቀዳ ይሰራል። ይህን ለማዘጋጀት የሚያሥፈልገው ጥሬ እቃ ሚጢ(ዘንባባ)፣ ሚግራ(ስንደዶ) ሊሆን ይችላል። አሰራሩንም በአጭሩ ለመግለፅ ያህል በመጀመሪያ በዘንባባው ስንጣቂ ወይም በስንደዶ እግር የሌለው ባለክዳን ስህን ቅርፅ ያለው እቃ ይሰራል። በመቀጠል ይህ የተዘጋጀው ስፌት ስሁንም ክዳኑንም በተለፋ በከብት ወይም በፊየል ቆዳ ይለበጣል። ከዚያ በመቀጠል በጅማት ዳርና ዳሩ ተወጥሮ የውጨኛው ክፍል ይሰፋል። ከዚህ በኋላ ለመጠቀም ዝግጁ ስለሆነ በአገልግሉ መጠን ልክ እየመጠኑ መጠቀም ይቻላል።

4.4.2..2 **ለመጠጫ የዋሉ ቁሳዊ ባህሎች**

***ሀ.*** Quluu (**የቡና መጠጫ**)

ቁሉ ማለት ከቅል የተሰራ የብና መጠጫ ነው። በቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ በቡና ስነስርአት ከሚስተዋሉ ቁሳዊ ባህሎች ዋነኛው ነው። ከወ/ሮ አለውያ ጌራ ጋር በበአሉ ማክበሪያ ቦታ በተደረገ ቃለመጠይቅ፤ ‹‹እኔ በህይወቴ ቡና ያለ ቁሉ ጠጥቼ አላውቅም። ያለ ቁሉ የሚጠጣ ቡና ቡናም አይመስለኝም። ዘመናዊ ስኒዎች እቤቴ ውስጥ አሉ። በክብር ይቀመጣሉ እንጂ ተጠቅሜባቸው አላውቅም›› ሲሉ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።

ቁሉ ባህላዊ እቃ ከመሆኑ ውጪ ከመውሊድ በአል ጋር ምንም አይነት ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሌለው ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ ለመረዳት ችያለሁ። ቁሉ መገኛውም ሆነ ተጠቃሚዎቹ ከአርሲ ከድሬ ሸከና ሁሴን የመጡ የእሳቸው ተከታዮች እንደሆኑ በቃለ መጠይቅ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ። አባ አረቡም የሳቸው ሳሂብ (ጓደኛ) በመሆናቸው እሳቸው ጋር በሄዱበት ወቅት ይዘው እንደመጡና፤ በዚሁ እቃ ቡና እንደሚጠጡ ተረድቻለሁ። ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው እዚያ የሄደ ሰው ብቻ የሚያመጣው እቃ ከሆነ፤ ምርቱ እዚያ ቦታ እንደሚገኝ እንጂ ከመውሊድ ጋር ግንኙነት እንደሌለው ነው። አሰራሩንም ለመግለፅ ያህል ለቁሉ ደረጃ የደረሰው ቅል ቅርጹ አጠር ብሎ ከላይ ክብ ሆኖ ወገቡ ቀጠን ይልና የታችኛው ክፍል የላይኛውንይመስላል።ቅሉ በዚህ

ደረጃ ሲደርስ ይቆረጣል። ከዚያ በጥንቃቄ ጭንቅላቱ(አናቱ)አካባቢ በስለት ነገር በእርጥብነቱ ይቆረጣል። በመቀጠል በውስጡ ያለው የዘር ፍሬ በሙሉ ተቦርቡሮ ይወጣል። ከአናቱ የተቆረጠውን ለክዳን ያበጁታል። ከዚያ "ዋቶ" የሚባል እንጨት ተወቅጦ ለእቃው የሚመጥን ውሃ ተጨመሮ በድስት (በማንቀርቀሪያ)ይፈላል። ከዚያ ፍሬው ወጥቶ በፀዳው ቅል ውስጥ ይጨመራል። አላዩን ደግሞ በእጅ ይታሻል። እንዲህ የሚደረግበት ምክንያትም ወይም በዋቶ የመታሸቱና የመዘፍዘፉ ጠቀሜታ ቁሉ እንዲቀላና ወዝ እንዲኖረው ከሚል እሳቤ ነው። ከዚያም ተጨምሮበት ለአንድ ቀን (ሃያ አራት ሰዓት) ውስጡ ይቀመጣል (ይቆያል)። በመቀጠል ውሃው ይደፋና በቀራሱማ እና በወይራ እንጨት እሳት በማንደድ የእሳቱን ጢፎ (ፍም የያዘ እንጨት) ቁሉ ውስጥ በማስገባት ደጋግሞ ማሸት ነው። እንዲህ የተደረገ ቅል መአዛው እስከ ስድስት ወር ድረስ ከውስጡ አይጠፋም። የሚጨመርበት ነገር ጣዕሙ ቆንጆና ያማረ ይሆናል። በእንዲ አይነት መልኩ ለዚህ ደረጃ የደረሰው ቁሉ ለመጠቀም ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል።

በቀን 13/03/2011 ዓ.ም ለወ/ሮ አለውያ ጌራ በበአሉ ማክበሪያ ቦታ ቁሉ እዚህ የለም?ይህ ሁሉ ሰው አርሲ ሄዶ ነው የሚያመጣው? ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ፡-

> ‹‹በትክክል እዚህ ጅማ ውስጥ የትም የገቢያ ቦታ ውስጥ ቢኬድ የሱ መሸጫ ቦታ የለም። ምናልባት ከአባት ከእናት ውርስ ሊገኝ ይችላል። እኔ እራሴ በልጅነቴ አባቴ ወደ አኬራ (ሞት) ሲሄዱ የእሳቸውን ወሰጄ ነው ስጠቀም የነበረው። አሁን ግን ለሸከና ሁሴን ካለኝ ፍቅር የተነሳ እዚያ(አርሲ)በሄድኩበት አንዱዋን ዘር ይዤ መጥቼ ቤቴ ተከልኩዋት። አሁን በቀላ ብዙ ዘር ይዛለች። ለእኛ ቤተሰቦች ሁሉ የሰጠሁት እኔነኝ። ለገዳም አምጥቼ እሰጣለሁ›› ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተውኛል።

### ለ. Masaaqulaa (ውሃ መያዣ)

መሳቁላ ከቅል የሚሰራ የውሃ መያዣ (ወዱእ ማድረጊያ) ቁስ ነው። አሰራሩም የደረሰው ቅል ከዛፉ ላይ ይቆረጣል። ከዚያ አናቱ (ጭንቅላቱ) ክፍት እንዲሆን በስለት ይቆረጣል። የዚህ ቅል ቅርፅ አንገቱ ረዘም ብሎ ወደታቹ የሚሰፋ ነው።ውስጡ ያለውን ፍሬ በቀላል ማውጣት የሚቻል ባለመሆኑ፤ የዘር ፍሬው እንዲወጣ ይቀል ዘንድ በእንጨት ነገር ወደ ውስጥ በመቦርቦር ያሉትን ፍሬዎች ሙሉ በሙሉ እንዲወጡ ይደረጋል። ከዚህ በመቀጠል ከላይ ለቁሉ የተደረገው ቅደም ተከተል ሁሉ በዚያው መሰረት ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ለመጠቀም ዝግጁ ስለሚሆን መጠቀም ይቻላል።

### ሐ. Maqanxaa (መገንታ)

መቀንጣ (መገንታ) የውሃ ወይም የወተት መጠጫ ነው። ይህ ቁስ እንደ ሌሎቹ ከቅል የሚሰራ ሲሆን አገልግሎቱም ለውሃ ወይም ለወተት መጠጫነት የሚያገለግል ነው። በነዚህ በሶስቱም ቁሶች መሀከል ያለው የአገልግሎትና የቅርፅ ልዩነት እንጂ በአሰራራቸውና ለአገልግሎት ዝግጁ የሚሆኑበት መንገድ ተማሳሳይ ነው።

4.4.2.3 **በክብረ በአሉ እለት የታዩ ጌጣጌጦች**

በዚህ ስር የሚነሱትን ቁሳዊ ባህሎች ለመተንተን ያመች ዘንድ ካሰራራቸው አንፃር ከእንጨት የተሰሩና ከጨሌ የተሰሩ በማለት በሁለት ተከፍለው ቀርበዋል።

4.4.2.3.1 **ከእጨት የተሰሩ**

በእለቱ ከነበሩት ቁሶች በእንጨት ስር የሚካተቱት አላማ፤ ሙሰባ፤ኡሌ፣ ቦኩ ናቸው።

*ሀ. Alaamaa (**የናሽከናሁሴን**)*

*አላማ ሸከና ሁሴን በህይወት በነበሩበት ወቅት ከእጃቸው የማይለያቸው ዱላ ነው። ይህም ዱላ ሸከና ሁሴን በሚጓዙበት ጊዜ እንደ ምርኩዝ ከመጠቀማቸው በተጨማሪ እጅግ ጠንቃቃና አዋቂ ከመሆናቸው የተነሳ መሰገጃቸውን፣ቁርአናቸውን፣ ሙሰባቸውን ወዘተ/ ያልሆነ ቦታ እንዳይቀመጥና ቁራን ቀርተው ቁራናቸውን ማስቀመጥ ሲፈልጉ በባላው ውስጥ አስገብተው እንደሚያንጠለጥሉ ከሼህ ተማም አባዲኮ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህ በተጨማሪ በእለቱ ከወ/ሮ መካ ከሊፋ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ፡-*

> *አላማ ማለት (ኡሌ ሸከና ሁሴን) ዱላ ነው። ይህ ዱላጠቀሚታው ቀላል አይደለም፤ አንዲት ወላድ ምጥ በሚበረታባት ሰዓት እንጨቱ ታጥቦ ብትጠጣ ወዲያው ከጭንቀትዋ ትገላገላለች። በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።*

*ይህንን ሀሳብ እንዴት ያዩታል በማለት ለሼህ ተማም አባ ዲኮ (የእምነቱ አባት ባቀረብኩት መሰረት፡-*

> *ይህ መሰረት የሌለው ሀሳብ ነው።እርግጥ ነው ሸከና ሁሴን በጣም አዋቂ ከስልሳ በላይ ቋንቋ ያውቃሉ ተብሎ የሚገመቱ ሰው ናቸው። ስለ እምነቱም ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚስተምሩ ነበሩ። የአሁኑ ሰው እሳቸው ለምን አደረጉ የሚለውን ሳይረዳ በደፈናው የእሳቸው ተከታይ ነኝ በማለት የሰሩትን እንኳን ሳይለይ ባልሰሩትና እሳቸው በማይወዱት ነገር ውስጥ ሲዘፈቅ እንመለከታለን። እና ይህ እሳቸው የሰሩት ባለመሆኑ ተቀባይነት የጎደለው ሃሳብ ነው።*
>
> *እሳቸው እኮ ምርጥ የነብዩ ወዳጅና ተከታይ ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ ነብዩ የሰሩትን ስራ ነበር ሲሰሩ የነበረው። ይሄ ሁሉ እሳቸው በህይወት እያሉ ሳይሆን ወደ አኬራ ከሄዱ በኋላ የእሳቸው ተከታይ ነኝ ባዮች ናቸው ይህንን ስራ የሚሰሩት። ሲሉ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።*

*የአላማ አሰራርን በተመለከተ ባካባቢው ከሚገኘው (አርሲ) አሮሬሳ፣ ወዬራ፣ ጉርሰዴ እና አዴሳ እንጨት ይዘጋጃል። በመጀመሪያ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የሆነው እንጨት ባላ ያለው ክፍል ታይቶ ይቆረጣል። የተቆረጠው እንጨት በደንብ የነደደ የሚለበልብ እሳት ላይ ይደረጋል። በእሳት ላይ መደረጉ ሶስት ጠቀሜታዎች አሉት። አንደኛው እንጨቱ እንደፈለገ መተጣጠፍ (መጉበጥ) እንዲችል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቅርፊቱ ከላዩ ላይ ተልጦ እንዲወጣ*

ነው። ሶስተኛው እና የመጨረሻው እንጨቱ እንደ እንጨት ሳይሆን እንደ ብረት በቀላሉ እንዳይሰበር ያደርጋል ብሎ ከማሰብ የተነሳ ነው። በዚህ ደረጃ የደረሰውን ባለባላ እንጨት በፈለጉበት (በተመቻቸው) ቦታ እንዲቀምላቸው ያመቻቸው ዘንድ ለእግሩ ማቀሚያ አንካሴ ብረት ይሰራለታል። ይህ መደረጉ መሬቱን ወግቶ መያዝ ስለሚችል ነው። በእንዲህ አይነት መልኩ የተዘጋጀ አላማ ለመጠቀም ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል።

### *ለ. የእንጨት ሙስባ (መቁጠሪያ)*

ሙስባ (መቁጠሪያ) ፈጣሪን በቀን ውስጥ ሳንሰላች ይህን ያህል ብለን ወስነን እንድናመሰግን የሚያስችለን የመቁጠሪያ አይነት ነው። ሙስባን ከተሰራበት ጥሬ እቃ አንፃር በጨሌ የተሰራና በእንጨት የተሰራ ብልን መመደብ እንችላለን። በመሀከላቸው የጥሬ እቃ (የተሰሩባቸው ነገሮች) ልዩነት እንጂ በመሀከላቸው የጠቀሜታ ልዩነት የላቸውም። ከእንጨት ሙስባ እንጨቱ "ቁርቁራ" ይባላል። የሚበቅለው አርሲ በመሆኑ የሚዘጋጀውም እዚያው ነው። የእኝጨቱ እዚያው መብቀል የአየር ንብረቱ ሁኔታ ገድቦት ይሆናል፤ የሚል እምነት ነው ያላቸው መረጃ አቀባዮቹ። አሰራሩን በተመለከተ ቁርቁራ የተባለው እንጨት ይቆረጣል። ከዚያ ቦሀላ በተፈለገው መጠን በእጅ ስለት ባለው ነገር ተቦርቡሮና ተፍቆ ይዘጋጃል። ከዚህ በመቀጠል በተቦረቦረው ቀዳዳ ጅማት ወይም ክር በማስገባት በተከታታይ 33 የተቦረቦረውን ሙስባ ይገባና አንድ በመጠኑ ለየት ያለ በማስከተል ይገባል። ይህ በእምነቱ ዘንድ ለየት ያለው(ተለቅ ያለው ኢማም ይባላል) ከዚያ የሚቀጥል ከሆነ ሰላሳ ሶስት ተመሳሳይ ሙስባ ይገባና እንደ መጀመሪያው በመጠኑ ተለቅ ያለው(ኢማም) ይገባል። በእንዲ አይነት መልኩ ተመሳሳዮቹ ሙስባዎች 99 እና ተመሳሳይ ኢማሞቹ ሶስት ያሉት በእምነቱ የተለመደውን ትልቅ ሙስባ ይዘጋጃል። ትልቁ ይሄኛው ሲሆን ትንሽ የሚባለው ደግሞ ሰላሳ ሶስት ተመሳሳይ ሙስባ እና አንድ ኢማም[48] ይኖሩታል። የቁጥሮቹ 33 እና 99 መሆን፤በ99ኙ ፈጣሪ ስም ላይ ተመርኩዞ የተሰራ መሆኑን ሲያመለክት፤ እንደ ትልቁ(ባለ99ኙ) ሙስባ ያልያዘ ሰውም በ33ቱ 3ጊዜ በመቁጠር እኩል መሆን ማስቻሉን ለማሳየት ሲባል የተቀመጠ ቁጠር ነው።

ሙስባን በተመለከተ በሁለቱም መንገድ የተዘጋጀውን ሙስባ ተመሳሳይ አገልግሎት ስለሚሰጡ በዚህ ደረጃ የደረሰውን ሙስባ ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል።

### *ሐ. Ulee bokkuu (ቀዷም)*

ኡሌ ቦኩ[49] (ቀዷም) ከእንጨት የሚሰራ ባህላዊ ብትር ሲሆን የሚይዙትም ገሪባዎች[50] (ቃድሪያዎች) ናቸው። የሚይዙበትም ምክንያት መለያቸው አድርገው ስለሚያስቡ ነው። ለዚህ አገልግት የሚውለው የእንጨት አይነት ጋምቤሎ ወይም የሚት እንጨት ሊሆን ይችላል።

---

[48]ኢማም ማለት ሜ ካሉት የሚበልጥ ከስር ያሉት የሚከተሉት የሚሰግድ ሲሆን ፤ በሙስባ መሀከል የሚገቡ ኢማሞች የሚነገድ ተግባር ሳይሆን የሚፈፅሙት የሚለየት ነው፡፡ አንደኛው ሰላሳ ሶስት ሙስባ ከሌላኛው ጋር እንዳይቀላቀል ሚድረግ ነው፡፡

[49]ኡሌ ቦኩ ሌላው ማጠሪያው ቀዷም ይባላል፡፡ ቀዷም ማለት ደግሞ በእድሜ የቆች ብዙ ታሪክ ያላት ማለት ነው፡፡

አሰራሩን በተመለከተ በመጀመሪያ እንጨቱን ግማሽ ሜትር ያህል ተለክቶ ይቆረጣል። ከዚያም በአንዱ ጫፍ የወንድ ብልት ቅርፅ በስለት ነገር በመፋቅ ይወጣለታል። የዚህ ቅርፅ ትርጉምም የወንድነትና የጀግንነት ምልክት እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ። ይህ ቅርፅ ከወጣለት በኋላ እንዲጠነክርና ቅርፊቱ እንዲነሳ በእሳት ይለበለባል። ከዚያ በኋላ እላዩ ላይ ያለው ቅርፊት ተራግፎ ሲያልቅ ወዝ እንዲኖረውና የበለጠ እንዲጠነክር በሞራ ወይም ሂዲ(እንጏይ ፍሬ) ይታሻል። ከዚህ በኋላ ላገልግሎት ዝግጁ ስለሆነ ይህንን ባህል የሚከተሉ ሰዎች ይይዙታል።

### 4.4.2.3.2 **ከጨሌ የተሰሩ**

የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርአተ ከበራ ክዋኔ የተለያየ ቀለም ያላቸው ብዙ ጨሌ ያደረጉ ሰዎች በሁለቱም ፆታ አስተውያለሁ። ይህን ጨሌ አስመልክቼ ለወ/ሮ መካ ከሊፋ ፤ወ/ሮ አለውያ ጌራ እና ለሼህ አወል ከማል፤  ይህ ጨሌ ትርጉሙ ምንድነው?ምንን ያመለክታል? ከመውሊድ ጋርስ ምን ግኑኙነት አለው? ብዬ ላነሳውላቸው ጥያቄ ምላሽ፡-

> ጨሌው ጨሌ አዳ (የባህል ጨሌ) ይባላል። ባህሉን የሚከተል ሰው ነው በዚህ የሚያጌጠው። የሚያመለክተው ደግሞ የሼከና ሁሴን ተከታይ መሆናችንን ነው። ከመወሊድ ጋር ምን ግኑኙነት አለው ላልሽው በጣም ግንኙነት አለው እንጂ፤ በመጀመሪያ መውሊድ የሚያከብር ሰው በራሱ ባህል
>
> የሚያከብር ነው። ባህሉን የማይከተል ሰው
>
> መውሊድ አያከብርም። ስለዚህ ሁለቱም አዳ(ባህል) ስለሆኑ ይገናኛሉ። ከዚህ ከተደረደው ሁሉ ይህኛው ቢጫው ጨሌ የሼከና ሁሴን ተብሎ ይጠራል። የተባለበትም ምክንያት አዘውትረው ስለሚጠቀሙበት ነው። ይህ በብዛት የተደረገው ጨሌ ለማጌጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ የእሳቸው ተከታይ መሆናችንን ለማመልከት ነው። ሲሉ ይገልፃሉ።

***ሀ. ጨሌ አዳ***

ጨሌ አዳ  በሚለው ስር የተለያዩ ጨሌዎች ይገኛሉ። እነዚህም ሙስባ፣ ጨሌ፣ ጨሌ ሼከና ሁሴን ናቸው። በነዚህ ጨሌዎች መሀከል የከለር ልዩነት ካልሆነ በቀር የአሰራር ልዩነት የላቸውም። ለዚህ ሲባል የአንዱ አሰራር ሲገለፅ የሁሉንም ጨሌዎች አሰራር ይገልፃል ማለት ነው። አሰራሩ በአጭሩ ሲገለፅ በመጀመሪያ የሚፈለገው ቀለም ጨሌ ይሰበሰባል። ከዚያ ለጌጥ የሚፈለገው ጨሌ በተፈለገው እርዝመት  ያህል በክሩ እንዲጠልቅ ተደርጎ የተፈለገው መጠን ሲደርስ ይቋጠራል። ይህ ማለት ለመዋቢያ (ለማጌጫነት) ስለ በቃ መጠቀም ይቻላል ማለት ነው። ሌላው

---

[50] ገሪባዎች (ቃድሪያዎች )የሸከና ሁሴን ተከታዮች ማለት ነው

አይነት አሰራር ከላይ በእንጨት የተሰሩ ጌጦች በሚለው ክፍል እምነቱን መሰረት በማድረግ የሚሰራው (ሙስባ) ነው።

በዚህ እርስ ስር ወ/ሮ አለውያ ጌራ ጋር ባደረኩት ቃለ ምልልስ ጨሌዎችን በተመለከተ፡-

‹‹ከጨሌዎች ውስጥ አንዱን ሜፉ ድርብ የሆነውን መርጠው ይሄ "ቀነፋ" ይባላል እናት ወልዳ የባልዋ ቤተሰቦች ቤት ለመራስ ስትገባ የህፃኑ ወንድ አያት ሜፏን በጥሰው የልጁ ግንባር ላይ ያስራሉ። ይህ ማለት እኔ እናቱ እስከ አርባ ቀን ድረስ የተከበርኩ መሆኔን ያመለክታል›› ሲሉ ይገልፃሉ። ይህ ሀሳብ በሚያመለክተው ጨሌ ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታ ጎን ለጎን የጎላ ባህላዊ ጠቀሜታ እንዳለው ያሳያል።

*ለ.Sinqii (ሽልማታ)*

ይች የጌጥ አይነት በጨሌ የተዋበች ማንጠልጠያና ክዳን እንዲሁም መቀመጫ የተበጀላት ትናሽዬ የወርቅ መሶብ ቅርፅ ያላት ናት። ብዙውን ጊዜ የአርሲ ሴቶች የባህል ልብስ ከለበሱ በኋላ የሚፈልጓቸውን ትናንሽ ነገሮች ከተው እንደ እጅ ቦርሳ ይገለገሉበታል። የዚችን ጌጥ ጠቀሜታ ወ/ሮ አለውያ ጌራ በ14/03/2011ዓ.ም እንዲ ሲሉ ይገልፃሉ፡-

‹‹እኔ ሲንቂን ከያዝኩ ሰው ያከብረኛል፤ አይደፍረኝም። ይገፎው ሄጄ ሰው አስታርቅበታለሁ። ወጣቶችን አስማማበታለሁ እና ከጌጥነቱ በተጨማሪ ብዙ ጥቅም አለው›› ይላሉ።

አሰራሩን በተመለከተ በመጀመሪ ትናንሽ ጨሌዎች በየአይነቱ ማዘጋጀት። ቢያንስ 4 ወይም 5 አይነት ቀለም ያስፈልጋል። ብዙውን ጊዜ አዳን ተከትሎ የሚሰራ ስለሆነ አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ነጭና ጥቁር ጨሌዎች ይፈለጋሉ። እንዲሁም ጅማቶች አስፈላጊዎቹ ቁሶች ናቸው። እነዚህ ከተዘጋጁ በኋላ ማንኛውም ሰው አይሰራውም‹‹ የራሱ የሆነ ጥበብ ሰላለው በባለ ሙያ (እውቀቱ ባለው ሰው) ይዘጋጃል። አዘጋጁም ተጠንቅቆ በተፈለገው ዲዛይን መሰረት መቅደም ያለበትን ቀለም እያስቀደመ መከተል እና ቀጥሎ መግባት ያለበትን እያስገባ በተፈለገው መሰረት አዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል ።

በአጠቃላይ ከላይ በመውሊድ በዓል ስርአተ ከበራ ክዋኔ ላይ በአሉን ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን (ዱፌ፣ኡሌ ዱፌ፣ አሸቂ፣ ማዲ፣ ግልግሊ፣ ቁሉ፣ መሳቁላ፣ አላማ፣ ኡሌ ቦኩ፣ ሙስባ፣ ሽልማታ) ከአገልግሎታቸው ወጣ ብለን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምር ቁሶቹ የሚከተሉትን ሶስት ባህሪያት ይዘው እናገኛቸዋለን ፡-

የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊ እና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ይዘው እናገኛቸዋለን። በዚህም መሰረት በማንኛውም አውድ ውስጥ ሆነን "ዱፌ"ን ፣ ኡሌ ዱፌና አሸቂን ስናስብ በቀጥታ የሚመጣብን የእስልምና ሐይማኖት መንዙማ ክዋኔ መሆኑ አያጠራጥርም። እንደዚሁ አላማ፣ ቁሉ፣ መሰቁላ፣ ሙስባ፣ ጨሌ አዳ በአንድነት የተሸከሙ /የያዙ/ግለሰብ ስንመለከት የሚታሰበን "ገሪባ" ስለሚባሉት ማህበረሰቦች ነው። እነዚህ ሰዎች ደግሞ የምን እምነት

ተከታይና የምን ባህል ተከታይ እንደሆኑ መገመት አይከብድም። የተቀሩት ቁሶች ኡሌ ቦኩ፣ማዲና ሽልማታ የጎላ ሀይማኖታዊ ገጽታ ባይኖራቸውም፤ባህላዊ ፋይዳቸው የላቀ ነው።ሌላው እነዚህ ቁሶች የተሰሩባቸውን ንጥረ ቁሶች እንደፈለግን በየትም ቦታ የማናገኛቸው መሆኑ የበለጠ ዋጋ እንድንሰጣቸው ያደርገናል። ይህ በተፈጥሮ እንደልብ ያለመገኘት ጉዳይ የቁሶቹን እሴት ቀጣይ ያደርገዋል።

ሁለተኛው ደግሞ ታሪክ ነቃሽነት (Surviving Historical Events)፡- ዱፊ ፣ ኡሌ ዱፊና አሸቄ ፣ አላማ ፣ ቁሉ ፣ መሳቁላ፣ሙስባ እና ጨሌ አዳን ተመልክተን (አጥንተን) በረጅም ዘመን ስለተፈጸመ የእስልምና ታሪክ ወይም ድርጊት የሚነግሩን ቁምነገር አላቸው። ምክንያቱም ቁሶች በአንድ በተወሰነ አካባቢና የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠነኛ የሆነ ለውጥ በማሳየት ረጅም እድሜ ይቀያሉና። በዚህም መሰረት ዱፊ፣ ኡሌ ዱፊ፣ አሸቄ፣ አላማ፣ በሳቁላ፣ ቁሉ፣ ሙስባ እና ጨሌአዳ ስለአለፈው ወይም ስላልኖርንበት ዘመን የመውሊድ ክብረ በዓልን ክዋኔ ታሪክ ለማወቅ እድል ይሰጡናል። በመሆኑም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ባህሎች በታሪክም ሆነ በቁሳዊ ባህል የጥናት መስክ ስለ እስልምና ሁለንተናዊ ባህል እና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

[51]**ይህን ሐሳብ በተመለከተም** (Prown, 1982፡3) “The most obvious cultural beliefs associated with material objects have to do with value”. **ብዙ ጊዜ ቁሶች የተለየ እሴት ባለቤት ሆነው ይገኛሉ። ይህንን እሴት አንድም በተፈጥሮ ወይም ሰው ራሱ ይጭንባቸዋል በማለት ይገልጸዋል።**
[52]**ይህንን ሀሳብ በተመለከተ** Prown (1982፡3). **የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል።** Objects created in the past are the only historical occurrences that continue to exist the present. They provide an opportunity by which we encounter the past at first hand; we have direct sensory experience of surviving historical even.

ሶስተኛውና የመጨረሻው የቁሶች ተወካይነት እና ውስንነት የመውሊድ ክብረ በዓልን በማጀብ ከገቡት ቁሳዊ ባህሎች ቃላዊ ግጥሞቹን /መንዙማቹን/ ለማጀብ ከሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች በጽሁፍ ከተገኘ መረጃ የበለጠ ተወካይነት አላቸው። ይህም ማለት ዱፊ፣ ኡሌ ዱፊ፣ አሸቄን በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የተማረውም ሆነ ያልተማረው፣ደሀውም ሆነ ሀብታሙ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረው ህዝብ ይገለገልባቸዋል ማለት ነው። ይህም ሲባል የሚነበቡት ወይም በቃል የሚባሉት መንዙማዎች ከቦታ ቦታ ሲለያዩ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ግን ተመሳሳይ ናቸው ማለት ነው። ሌሎች በክብረ በዓሉ ክዋኔ ላይ አጅበው ወይም ለማድመቅ የገቡት ቁሳዊ ባህሎች ከተፈጠሩበት ቦታ፣አብረው ካደጉት ማህበረሰቦች እና የእነዚህ ማህበረሰቦች ባህል ተከታይ ከሆኑት ውጭ በቁሶቹ ላይ የአካላይነት ባህሪ ሳይሆን የውስንነት ባህሪ ይታይባቸዋል። ይህም ባህሪያቸው ከሀይማኖታዊነት የበለጠ ባህላዊነታቸው የጎላ እንዲሆን አድርጓቸዋል ማለት ይቻላል።

## 4.5 **የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር** (Function)

ፎክሎር በርካታ ተግባሮች ያሉት ሲሆን ይህንንም በማስመልከት William R. Bascom (1965፣ 279–298) የፎክሎርን ተግባር (escape, validation, education, and social control ) በማለት በአራት ይከፍላቸዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ቁባ አባ አረቡን ምክንያት በማድረግ የሚከበረው የመውሊድ ክብረ በዓል ያሉትን ተግባራት (Functions) እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ የማጠናከር (የመትክል) ተግባር አለው፡፡ ይህንንም ከላይ ሸህ መሀመዳሚን አብዱልዋሂድን ጠቅሼ እንደገለጽኩት በመውሊዱ የነብዩ መሐመድ ስራዎች እና የኡለሞች ገድል በመንዙማዎች ስለሚወሱ የእነሱን አርአያነት በዓሉን ለመካፈል በመጡ ህጻናት ላይ እምነቱን እና ጽንነታቸውን የማስረጽ እና የመትከል ተግባር አለው፡፡

ከዚህም በተጨመሪ የመውሊድ ክብረ በዓል የማምለጥ (የማምለጫ) ተግባር አለውማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ይህ ክብረ በዓል ቃላዊ ጥሞቹን ለማጀብ የገቡት ቁሳዊ ባህሎች በመጥቀም መንዙማ በመባሉ /በመኖሩ/ የእምነቱ ተከታዮች ከአሥልችው የእለት ተዕለት የህይወት ውጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል፡፡ሌላውና የመጨረሻው የመውሊድ ክብረ በዓል ማህበረሰቡን የመቆጣጠር ተግባር አለው፡፡ ይህን በተመለከተም ከወ/ሮ አለውያ አ/ዝናብ (በአሉን ለማክበር ለ8ኛ ጊዜ በቦታው የተገኙ)እናት ጋር ባደረግኩት ቃለመጠይቅ፡-

‹‹አባ አረቡ አሁን ላንቺ አይታዩሽም (ለኛ አይታዩም) እሳቸው ግን እኛን ያዩናል፡፡እና እዚህ መጥተሽ ዘይረሽ ስትመለሺ ሸልማትሽን ከሳቸው ይዘሽ ነው የምትመለሺው፤ቤትሽም በረካ አብሮ ነው የሚገባው፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ምእመናንከበራው ቦታ ለመጓዝ ከራሳቸው ፍላጎት በተጨማሪ አንዳች በውስጣቸው ያለው እምነት ወደ ስፍራው ሳይሄዱ ቢቀሩ የሚደርስባቸው ነገር እንዳለ ስለሚያስቡ አመቱን ጠብቀው በዓሉን ለማክበር ወደ ከበራው ስፍራ እንዲሄዱ ያስገድዳቸዋል ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍአምስት
# የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት

ይህ የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን የጥናቱ ግኝቶች እና ከግኝቶቹ በመነሳት የአጥኚው ይሁንታ የቀረበበት ነው።

## 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ በጅማ ከተማ የሚከበረውን የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ ስርአተ ከበራ (ከዚያራ እስከ ፍጻሜ) ያለውን ክዋኔ ሂደት መተንተንን አላማ አድርጎ የተካሄደ ነው። ጥናቱ ሲካሔድ ክዋኔውን በሁነቶች በመከፋፈል ለመመርመር ጥረት ተደርጓል።በተጨማሪም ክብረ በዓሉን አጅበው የገቡትን ቁሳዊ ባህሎች አሰራር ፣ ጥቅማቸውን ና ትርጓሜየቸውን ለማየት ተሞክሮዋል ። ከቃላዊ ግጥሞቹ ክዋኔ ጋር ተያይዘው የሚነሱትን ቁሳዊ ባህሎች ፣ አሰራር ፣ ጥቅማቸው ና ትርጓሚያቸውን ለማየት ተሞክሯል።

የጥናቱን አቢይ አላማዎች ከግብ ለማድረስም አጥኝዋ በመስክ ቀይታዋ ቃለመጠይቅን፣ምልከታን እና ተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግላለች። መረጃዎቹም በተፈጥሮአዊ መቼት የተገኙ ሲሆን በቴፐ፣በቪዲዮ ካሜራ እና በፎቶግራፍ ምስል ተቀርጸዋል። በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መስክ ላይ የተሰበሰቡት መረጃዎች በክፍል ሁለት በተከለሱት ንድፈሀሳባዊ መሰረቶች በመታገዝ ለመተንተን የተቻለ ሲሆን የትንተናው ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል።

የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች ይጀምራል። ይህ የስርአተ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት ደግሞ መውሊዱ ሥርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው። በቁባ አባ አረቡ የመውድ በአል ስርዓተ ክዋኔ ዋዜማ የሚጀምረው ዋናው በዓል ከመድረሱ 10 ቀን በፊት ነው። ይኸውም ከረቢያል አወል 1 እስከ 7 ኛው ቀን ድረስ አስፈላጊው ግብአት የሚሟለበትና የከበራውበ ቦታ የሚጸዳበት ነው። ቀን ስምንት የወንዶች የመውሊድ ሲሆን ይኸ ውም እርድ በማረድ በአሉን ለማክበር ከሩቅ አካባቢ /ከተሞች/ የሚመጡትን ሰዎች ለመቀበል ወይም ለመመገብ ታስቦ የተደረገ ነው። በቀን 9 የሚከበረው የሴቶች መውለድ ሲሆን መስጂደ አሩረተማ አካባቢ በሚኖሩ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚዘጋጅ ነው። እንደ አጠቃላይ የቁባ አባ አረቡ መውሊድ በሙቀደማ (ዋዜማ)ቀንነት የሚታወቀው ረቢያል አወል 11 ኛው ለሊት ለቀን 12 መንጊያ ነው።በሁለቱም እለት ክዋኔ ላይ የሌላ እምነት ተሳትፎ በምልከታዬ አላስተዋልኩም።ምክንያቱም በዋዜማው እለት የሚገኙት ከሩቅ አካባቢ የመጡ ት እና የአካባበው ነዋሪዎች እንደ መሆናቸው በአካባቢው የሚኖሩት ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆናቸው፤ በእለቱ የሌላ እምነት ተከታይ ተሳታፊ አልነበሩም።

በመውሊድ በዓሉ የአከባበር ስርዓት ላይ በዋናነት የተስተዋሉትን የክዋኔ ሁነቶች ዚያራ ፣ዱአ፣ ምርቃት ና መንዙማ ናቸው። የነዚህ ሁነቶች አጠቃላይ መጠሪያ "ዱአይ" እንደ ሆነ በጥናቱ ተጠቁሞዋል።በዚህ በዱአይ ክዋኔ ወቅት የጾታ ፣ የእድሜ ፣ ማህበራዊ ሁኔታ እንደ ማይገድባቸውና ሁሉም ለጋራ አላማ ተቀላቅለው እንደ ሚቀመጡ አስተውያለሁ።ከዘዚህ በተጨማሪም ሁነቶቹ አንዱ ከአንዱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው እንደ መሆናቸው

ተሳታፊዎቹም ይህንን አውቀው ይፈጽሟቸዋል።በተመሳሳይ መልኩ የቁባ አባ አረቡ የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች እንደ መጀመሩ ሁሉ የራሱ የሆነ ማጠቃለያ አለው ። በዚህ ሸኝትም ምእመኑ ወደመጣበት ከመመለሱ በፊት ንጋት ከሱብሂ ሰላት በፊት በርዘንጅ የሚባል የሸኝት መንዙማ ከተባለ በኋላ ምመኑ ወደ መጡበት ሲመለሱ የተህሊል ውኋ ለመድሐኒትነት እየያዙ እንደሚሄዱ እና ፈውስን እንደ ሚያገኙ ለመረዳት ተችሏል።

በመውሊድ በአል ከበራ በስፋት ከሚስተዋሉ ሁነቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ መንዙማ ነው። የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሒደት (በዱአው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) አንጻር በሁለት መንገድ ( በድቤ እና በእንጉርጉሮ ) እንደ ሚባሉ ለመረዳት ተችሏል። በዚህም መሰረት በዱፊ የሚቀርቡት ክዋኔያቸው ፍጥነት ያለው ሆኖ በሰጪና ተቀባይ መልክ (አሳታፊ) ሲሆን በእንጉርጉሮ የሚቀርቡት ላይ ግን አሳታፊነቱ እንዳለ ሆኖ ቀዝቀዝ ያለ እና ረዘም ያለ ጊዜ ከዋኙ የሚያገኝበትን እድል የሚፈጥር መሆኑን ነው።

ከክብረ በዓሉ ስርዓተ ክዋኔ ሂደት ወጣ ብለን ክብረ በዓሉን ለማጀብ የገቡትን ቁሳዊ ባህሎችን በሶስት ምድብ በመክፈል ቃላዊ ግጥሞቹን ለማጀብ የገቡ፣የመመገቢያ ቁሳቁሶችና ጌጣጌጦች በማለት አሰራራቸውና ጠቀሜታቸው የተዳሰሰ ሲሆን ከዚያም ወጣ በማለት ማህበራዊ፣ባህላዊ ና ሀይማኖታዊ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምር ቁሶቹ ሶስት ባህሪያት ይዘው እናገኛቸዋለን። እነሱም የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊ ና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ናቸው ፣ ሁለተኛው ደግሞ ታሪክ ነቃሽነት ሲሆን፤ ሶስተኛው እና የመጨረሻው ተካይነት ውስንነት ሆነው ተገኝተዋል።

በመጨረሻም የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር ስንመለከት የማጠናከር (የመትክል) ተግባር አለው። ይህንንም የነብዩ መሐመድ ስራዎች እና የኡለሞች ገድል በመንዙማዎች ስለሚወሱ የነሱን አርአያነት በዓሉን ለመካፈል በመጡ ህጻናት ላይ እምነቱን እና ጀግንነታቸውን የማስረጽ እና የመትከል ተግባር አለው። ከዚህም በተጨመሪ የመውሊድ ክብረ በዓል የማምለጥ (የማምለጫ) ተግባር አለው ማለት እንችላለን። ምክንያቱም ይህ ክብረ በዓል በዱፊ፣ኡሌ ዱፊ ና አሸቄን በመጠቀም መንዙማ በመኖሩ የእምነቱ ተከታዮች ከአሠልችው የእለት ተዕለት የህይወት ወጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል። ሌላውና የመጨረሻው የመውሊድ ክብረ በዓል ማህበረሰቡን የመቆጣጠር ተግባር አለው።በተለይ የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ምእመናን መውሊዱን ለማክበር በየአመቱ ስፍራው ድረስ በመሄድ ከበረውን የሚያከሂዱት ከራሳቸው ፍላጎት በተጨማሪ አንዳች በውስጣቸው ያለው እምነት ቢቀሩ እንኳ የሚደርስባቸው ነገር እንዳለ ስለሚያስቡ አመቱን ጠብቀው ለማክበር ወደ ከበራው ስፍራ እንዲሄዱ የስገድዳቸዋል።

## 5.2 አስተያየት

ይህ የመውሊድ ክብረ በአል ለማህበረሰቡ እያበረከተ ያለው ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ግልጋሎት ላቅ ያለ መሆኑን በጥናቱ ለማመልከት ተችሏል። በመሆኑም ከጥናቱ አጠቃላይ ውጤት በመነሳት የሚከተሉትን አስተያየቶች ለመሰንዘር እወዳለሁ።

በአሁኑ ሰዓት (በመውሊዱ ክብረ በዓል እንዳስተዋልኩት ) ምንም እንኳ በአብዛኛው የሚደመጠው መንዙማ እንደጥንቱ በዱፌ ና በአሸቄ ባሉ ባሕላዊ መሳሪያዎች የታጀበ ቢሆንም፣ የመንዙማው ይዘት ጎልቶ የሚታየው በነብዩ ውዳሴና በኡለሞች ገድል አንዲሁም በወቅታዊ ጉዳዩች (ፖለቲካዎች)ላይ ጎልቶ ይታያል። የነዚህ ጠቀሜታዎች እንዳለ ሆኖ የቦታው ፎክሎራዊነት እንዳይቀንስና ቀጣይነት እንዲኖረው ዳዕዋ /ሀይማኖታዊ ትምህርት / በበአለ እለቱ ምሽት የሚሰጥበት ሁኔታ ቢስተካከል ፤ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከማኅበራዊ ፥ ታሪካዊ ፥ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ ፣ ፎክሎራዊ እና ሥነ ጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም ወደ ፊት ክፍተቶቹ ታይተው ቢሞሉ መልካም ነው ባይ ነኝ።

ሌላው በዚህ ክብረ በዓል ላይ አጅበው የገቡት ቁሶች በሰው እጅ ካሉት ውጭ በቁባ አባ አረቡ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙት በአንድ ደረጃውን ያልጠበቀ ክፍል ውስጥ መቀመጣቸው አሷራና ጥቀርሻ ተዳርገዋል።በእንዲህ አይነት ሁኔታ መቀመጣቸው ደግሞ ቁሶቹ ረጅም እድሜ እንዳይኖራቸውና ታሪካዊነታቸው እንዲጠፋ ያደርጋቸዋል ። ስለዚህ በቂ ጥበቃ ተደርጎላቸውና ምሉዕ ሆነው ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ ቅርሶቹ ተጠብቀው ሊተላለፉ ይገባል እላለሁ።

## ዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች


ሀሰን ታጁ።(2009)።መውለድ ተከታታይ እትም።ነጃሺ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

መኮንን አሰማማው።(2007)"በድላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና ከይቦቤ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ይዘት ትንተና" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።የአማረኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህረት ክፍል፤ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

አብዱራህማን ፋንታሁን። (2007)። ‹‹የሀጂ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ )የመውሊድ በአል ስርአተ ከበራና ቃላዊ ግጥሞች(መንዙማዎች)ጥናት››ላይ የተሰራ የኢትዮ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል ለ አርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ጅሬን።(2009)።ጅማ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ዓመታዊ መጽሄት።ኒኮም ማተሚያ ቤት ጅማ።

ስዩም መርጋ።(2007)"AN ARCHAEOLGICAL SURVEY OF ISLAMIC IN JIMMA ZONE SOUTH WESTERN ETHOPIYA"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።በታሪክ ጥናት ትምህርትክፍል፤ ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

Abrahams,Roger.(1968).Introductory Remarks to arhetorical Theory of Folklor. *Journal of American Folklore.* vol. 320. 143-58

Bouman,Richard(1983).Hand book of American folklore,*Journal ofAmerican Folklor.* pp.362-367.

Brill, M. (2008). Celebrations, Islamic culture, Prophets, Birthdays, Fasting, Koran, https://www.jstor.org/stable/3399341 (Retrieved on 21 April, 2019).

Catherine Bell.(1997).*Ritual :Perspectives and Dimensions.* New York:Oxford University Press,

Dan Ben-Amos,(1993) Context in Context.The organizing Folcklore: Towardse New Perpectives on the Politics of culture.*The Journal of American Folklor,*vol.52, No 2/4, pp 209-226.Published by American Folklore society.

Fennegan,Ruth. (1970). *Oral Litratare in Africa.*Nairobi:Oxford University Press.

Jackson, Bruce. (1987) *Fieldwork.*Urbana and Chicago: UniversityIllinois Press.

Kaplan, M. (2015).What Is Mawlid? How Muslims Celebrate The Prophet Muhammad's Birthday During Rabi' Al-Awwal, https://www.jstor.org/stable/3399341 (Retrieved on 21 April, 2019).

MacDonald, Donald A. (1972) "*Fieldwork: Collecting Oral Literature*." In Folklore and Folk life: An Introduction. (Richard M. Dorson (Ed.). Chicago and Landon; the University of Chicago Press,

Rappaport,R. A. (1992) *Folklore,cultural performances,and Popular Ertainments,* Ed.Richard Bouman,(249-260).NewYork,OxfordUniversity Press

Reynolds, Jafar. (2017). Why do Muslims celebrate Maulid al-Nabawi?Religious festivals, Ceremonies, https://www.jstor.org/stable/3399341(Retrieved on 21 April, 2019).

Sims,M.C and Stephens,M. (2005). *Living folklore:An introduction to the study People and their Traditon.*Logan,Utah state University press.

Terimingham, Spencer (1952) *Islam in Ethiopia*. Geoffrey Cumberlege; Oxford University Press, London.

Thomas,A. Green (Ed).(1997) *Folklore an Encycolpediya of Beliefs, customs,Tales, Music and Art;*santa Barbara,California Denver,Colorado Oxford.England.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፤ብቃለ መጠይቅ ወቅት የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች

1. የመውሊድ ክብረ በዓል ለምን ይከበራል? ታሪካዊ አጀማመሩ ምን ይመስላል?

2. የመውሊድ ክብረ በዓል የእምነቱ ተከታዮች መቼ እንዴት ያከብሩታል? በምን አውድ?
3. የከበራው አጠቃላይ የክዋኔ መዋቅር ምን ይመስላል?

4. በክብረ በዓሉ ላይ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ሁነቶች ምን ምን ናቸው?

5. በመውሊድ ክብረ በዓል መንዙማን ለማቀንቀን ( የክዋኔው መሪ ለመሆን ) ምን ያስፈልጋል?
6. መንዙማ ከመውሊድ በአልስ ጋር ምን ቁርኝት አለው?

7. የመንዙማዎቹ ደረሳ መቼና እንዴት ይከናዎናል? የተፈቀደውስ ለማነው?

8. የመከበሩ አጠቃላይ ማህበራዊ ( ለእምነቱ ተከታዮች ) ፋይዳውስ ምንድን ነው?

9. ቁሳዊ ባህሎቹ  ከበዓሉ ጋር ምን ግንኙነት አላቸው?

አባሪ  ሁለት፡ የመረጃ አቀባዩች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉስም | እድሜ | ጾታ | የመኖሪያአካባቢ | የስራድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ/ ዊዳድ አ/ፊጣ | 56 | ወ | ጆማ ከተማ ነዋሪ | የቀድሞው የጅማ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ |
| 2 | ሸህ መሀመድ አሚን አብዱልዋሂድ | 70 | ወ | ቁባ አባ/አረቡ አካባቢ ነዋሪ | የቁባ አባ አረቡ መስጊድ ኢማም |
| 3 | አቶአንዋርሁሴን | 41 | ወ | የካባቢውነዋሪ(ደርጋ) | በንግድስራየሚተዳደር |
| 4 | አቶ/ጁነዲን ከድር | 52 | ወ | የአካባቢው ነዋሪ | የግል ድርጅት ዘበኛ (የገሬ ሀላፊ) |
| 5 | ወ /ሮ  አለውያ ጌራ | 46 | ሴ | የጌራ ከተማ ነዋሪ | የመንዙማና  የዱአ ሰው |
| 6 | ሸህ ኑራ አባ/ቦር | 75 | ወ | መስጂዳ አፋርተማ አካባቢ ነዋሪ | የሀገር ሽማግሌና መውሊዱን በዓል ላለፉት 25 አመታት የተሳተፉ |
| 7 | አባ ጅሀድ አባ/ገሮ | 51 | ወ | የሰኮሩ ከተማ ነዋሪ | በግብርና ስራ የሚተዳደሩናላለፉት 10 ዓመታት በበአሉ ላይ የተሳፉ |
| 8 | አበ/መጫ አባ/ አረቡ | 80 | ወ | የቁባ አ/ አረቡ ነዋሪ | የአባ/አረቡ ካዳሚ |
| 9 | ወ /ሮ አለውያ ከማል | 48 | ሴ | የአካባቢው ነዋሪ | የቤት እመቤት ላተፉት 18 አመታት በበአሉ ላይ የተሳተፉ |
| 10 | አባ/ነጋ አባቦር | 52 | ወ | የአሰን ዳቦ ከተማ ነዋሪ | የጥበቃ ሰራተኛ ላለፉት 10 ዓመታት በበዓሉ ላይ የተሳተፉ |
| 11 | ወ/ሮ ዲልቢ አባ/ሞጋ | 46 | ወ | የአካባቢው ነዋሪ | የቤት እመቤት ላለፉት 8 ዓመታት በበዓሉ ላይ የተሳተፉ |
| 12 | ሸህ ተማም ሸኮታ | 60 | ወ | የከተማው ነዋሪ | የእምነቱ አባት(አዋቂ) |
| 13 | አባ ቢያ አባ ቦሰን | 52 | ወ | ከተማው ነዋሪ | የገሬ ሸኒ ሀላፊ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ሸህ ሚፍታ ተማም | 50 | ወ | የአካባቢው ነዋሪ | የመውሊዱ አስተባባሪ |
| 15 | ወ/ሮ መርዲያ /ሳንቢ | 43 | ሴ | የመስጂዳ አፋርተማ አካባቢ ነዋሪ | ጅማ ዩኒቨርስቲ ጽዳት ሰራተኛ |
| 16 | ወ/ሮ መካ ከሊፋ | 50 | ሴ | የሊሙ ገነት ከተማ ነዋሪ | ገሪባ ከ20 አመታት በላይ በበዓሉ ላይ የተሳተፉ |
| 17 | ወሪ/ት ሀባቢ ሸህ መሀመዳሚን | 20 | ሴ | የአካባቢው ነዋሪ | ተማሪ (የኢማሙ ልጅ) |
| 18 | ሸህ አደም ሙሳ | 66 | ወ | የሰርቦ ከተማ ነዋሪ | ገሪባ (የመንዙማ ግጥም አዋቂ) ለረጅም አመት የበአሉ ተሳታፊ |
| 19 | ወ/ሮ አለውያ አ/ዝናብ | 48 | ሴ | ከተማው ነዋሪ | ጅማ ዩኒቨርሲቲ ወጥ ቤት ከ 7 አመታት በላይ በበዓሉ ላይ የተሳተፉ |
| 20 | አባ ነጋ አ/ጎጃም | 77 | ወ | የሊሙ ሻይ ከተማ ነዋሪ | ሀገር ሽማግሌ ለረጅም አመት በበዓሉ ላይ የተሳተፉ |
| 21 | አተ/አወል ከማል | 76 | ወ | የሰቃ ከተማ ነዋሪ | እርሻ ስራ የሚተዳደሩ የረጅም ታፊሳፊ |

## አባሪ ሶስት ፡-በቁባ አባ አረቡ መውሊዱ ላይ የሚቀርቡ መንዙማዎች (ቃል ግጥም) በመገኛ ቋንቋ (ኦሮምኛ)

**ቃል ግጥም** .1

Abba arabuu

Abba arabuu balbala kessan dhufnee

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Balbbala kessan dhufnee hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee(2)

Yaa ijolle himaniruu yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Salaamataa dhamaniruu bahrikoo

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Isaanis jawwabaniruu yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Balbala kessan dhufnee

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Ashaqii maa hin muginaa yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Argachu malee hin dhabinaa yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Zamzama kessan dhugnee

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Utuman ta'e foolisaa yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Silaa funfadhee foolisaa yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Zamzama kessan dhugnee

Hin fayyinaa zamzam kessan dhufnee.

Abba arabuu balbala kessan dhufnee

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Ililililil……ilililili…

Ashaq..Ashaq..Ashaq…

Argachu mal hin dhabinaa yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Obbolessi inni tiruun koo yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Gesse na gatee kophaa koo yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Itti naannessen laahdi koo yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Makinaa karaa jireeni yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Altokko qabaa fireeni yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Na gessi karaa madinaa bahriikoo

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Madinaa biyya bareddu yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Kaloo abaabonnii dhedduu yaa dawaa

Hin fayyinaa zamzama kessan dhugnee

Zamzama kessan dhugnee

Hin fayyinaa balbala kessan dhufnee(4)

Ilililil..ilililil…..

**ቃልግጥም** .2

Salaamualaykum jamaalaa

Salaamualaykum jamaalaa

Salaamualaykum jamaalaa

Ababbaa faaxuumaa zaahraa (2)

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa.

Utuman taa'e dammaqaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

N a gessi karaa madinaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Madinaa biyya bareddu

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Kaloo abaabonni dheeddu

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Salamualaykum jamaalaa

Salamualaykum jamaalaa

Ababbaa faaxuumaa zaahraa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Akiraa oluun hin jiruu

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Ashaqii maa hin muginaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Argachu mal hin dhabinaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Salamualaykum jamaalaa

Salamualaykum jamaalaa

Ababbaa faaxuumaa zaahraa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Ashaq..Ashaq..

Ilililil…ilililililil…..

Abbaa arabuun arabaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Kottaatii harkaan nuu qabaa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa

Salamualaykum jamaalaa

Salamualaykum jamaalaa

Ababbaa faaxuumaa zaahraa

Shubbaaki irraa gad nuu laalaa(2)

**ቃል ግጥም** .3

Assalat Wassalaam aiaa

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa (2)

Amma gaheeraa motiin koo

Alan Nabii

Naaf haalaalamu doseen koo

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa(2)

Utuman ka'e adeemee

Alan nabi

Madinaa gahee hin buluuree

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa(2)

Hey..hey….hey…

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa(2)

Yaa rasuul amiin takkatuu

Alan nabii

Namnii isiin waamee hin rakkatuu

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa(2)

Ashaq...Ashaq….Ashaq

Maqaan kee nabii hin miyaa'a

Alen nabii

Akka walalaa dammati

Dammille gagaa qabaatii

Alan nabii

Haabibiin abbaa namaati

Alan nabii

Sataraa haala namaati

Alan nabii

Assalaat wassalaam alaa

Alan Nabii

Musxeefaa arrusan xaybaa(2)

**ቃልግጥም**.4

Sallallaa alaa muhammed

Sallallaa alaa muhammed

Sayyidii

Sallallaa alay wassallam

Sayyidii (2)

Abbaa koo gaangoo shaggaari

Sayyidii

Abbaa maashotaa gaggaari

Sayyidi

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Yaa rasul amiin takkatu sayyidii

Namni isiin waame hin rakkatuu

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Muhammed jadheen garaatti

Sayyidii

Katabaa qabaa nyaaraatti

Sayyidii

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Anuu sumattan watwaadhaa

Sayyidii

Motii na jalaa awwaadha

Sayyidii

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Warahmatuka shufaau

Sayyidii

Dammi haamma isaa hin miyaau

Sayyidii

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Sayyidal waduud adaraa

Sayyidii

Mee ammuma nuu addaraa

Sayyidi

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Aduddeen biyya Arabiin

Sayyidii

Risaalaa fidde kan nabii

Sayyidi

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Alhamdulillah gammannee

Sayyidii

Sayyidal waduudin argannee

Sayyidii

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Habibii bineensi baree

Sayyidii

Anaali hin qabuu isiin malee

Sayyidii

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Ytuman ta'ee safiinaa

Sayyidii

Marmartuu karaa madiinaa

Sayyidi

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii

Bagan ta'ee rediyoon kee

Sayyidii

Narra hin kenyee taation kee

Sayyidi

Sallallaa alaa muhammed Sayyidii

Sallallaa alay wassallam Sayyidii(4)

### ቃል ግጥም .5

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

Sayyidii jechuun isaani

Marhaaba

Qulqullu akka bishaani

Marhaabaa

Namnii moolida baasu

marhaabaa

haajaa isaa rabbi haa baasu

marhaabaa

Azaa isaa rabbi haa kaasu

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

Kophaa koon taa’ee gungumaa

Marhaabaa

Maaliif na gattan dhuguumaa

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

Abbaa arabuun arabaa

Marhaabaa

Kottaati haarkaan nuu qabaa

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

Salaamataa dhaamaniruu

Marhaabaa

Isaanis jawwaabaniruu

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

Utuman taa’ee shufeerii

Marhaabaa

Akka amadal buuseerii

marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaabaa

Marhaabaa

Marhaabaa nabii marhaaba

Marhaabaa(2)

## አባሪ አራት፡-በቁባ አባ አረቡመውሊዱ ላይ የሚቀርቡት መንዙማዎች (ቃል ግጥም) ትርጉም በአማርኛ

### ቃል ግጥም አንድ

አባ አረቡ

አባ አረቡ በልበለ ኬሰን ዱፈኔ

ሂን ፈይና ዘምዘመ ኬሰን ዱገኔ

በልበለ ኬሰን ዱፈኔ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ(2)

ያ ኢጆሌ ሂመኒሩ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ሰላመታ ዳ መኒሩ ባህሪኮ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ኢሳኒስ ጆዋበኒሩ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

በልበለ ኬሰን ዱፈኔ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ(2)

አሸቂ ማ ሂን ሙጊና ያደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

አርገቹ መል ሂን ደቢና ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ዘምዘመ ኬሰን ዱግኔ

ሂን ፈይና በልበለ ኬሰን ዱግኔ

ኡቱመን ታኤ ፎሊሳ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ሲላ ፉንፈዴ ፎሊሳ ያደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ዘምዘመ ኬሰን ዱግኔ

ሂን ፈይና በልበለ ኬሰን ዱግኔ።

አባ አረቡ በልበለ ኬሰን ዱገኔ

እልል.....እልል...እልል...

አሸቂ ...አሸቂ...አሸቂ...

አርገቹ መል ሂን ደቢና ያደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ኦቦሌሲ ኢኒ ቲሩንኮ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ጌሴ ነ ገቴ ቀባኮ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

መኪና ከራ ጂሬኒ ያደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

አል ተኮ ቀባ ፍሬኒ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ነጌሲ ከራ መዲና ባህሪኮ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ከሎ አባቦኒ ዴዱ ያ ደዋ

ሂን ፈይና ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ዘምዘማ ኬሰን ዱግኔ

ሂን ፈይና በልበለ ኬሰን ዱፍኔ(4)

እልል...እልል ...እ

## ቃል ግጥም 2

### ሰላማለይኩም ጀማላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

አበባ ፋጡመ ዛህራ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ።(2)

ኡቱመን ታኤን ደመቃ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ነጌሲ ከራ መዲና

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

መዲና ቢየ በሬዱ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ከሎ አባቦኒ ዴዱ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

አበባ ፋጡመ ዛህራ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ።(2)

አኪራ ኦሉን ሂንጂሩ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

አሸቂ ማ ሂን ሙጊና

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

አርገቹ መል ሂንደቢና

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

አበባ ፋጡማ ዘአህራ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

አሸቅ…አሸቅ…

እልል…እልል…

አባ አረቡ አረባ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ኮታቲ ሀረካ ኑ ቀባ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

ሰላማለይኩም ጀማላ

አበባ ፋጡማ ዘህራ

ሹባኪ ኢራ ገድ ኑ ኢላላ

## ቃል ግጥም 3

### አሰላት ወሰላምአላ

አሰላት ወሰላምአላ

አለን ነቢ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

አመገሄራ ሞቲንኮ

አለን ነቢ

ናፍ አላለሙ ዶሴኮ

አሰላት ወሰላምአላ

አለን ነቢ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

ኡቱመን ካኤ አዴሜ

አለን ነቢ

መዲና ገሄ ሂን ቡሉሬ

አሰላት ወሰላም አላ

አለን ነቢ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

ሄይ…ሄይ…ሄይ…

አሰላት ወሰላም አላ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

ያረሱላሚን ተከቱ

አለን ነቢ

ነምኒ ኢሲን ዋሜ ሂንረከቱ

አሰላት ወሰላም አላ

አለን ነቢ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

አሸቅ …አሸቅ…አሸቅ…

መቃን ኬ ነቢ ሂን ሚያአ

አለን ነቢ

አከ ወለላ ደማቲ

ደሚሌ ገጋ ቀባቲ

አለን ነቢ

ሀቢቢን አባ ነማቲ

አለን ነቢ

አሰላት ወሰላም አላ

አለን ነቢ

ሙስጠፋ አሩሰን ጠይባ(2)

## ቃል ግጥም 4

## ሰለላ አላ ሙሀመድ

ሰለላ አላ ሙሀመድ

ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም

ሰይዲ

አባኮ ኮ ጋንጌ ሸገሪ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

ያረሱል አሚን ተከቱ ሰይዲ

ነምኒ አሲን ዋሚ ሂን ረከቱ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

መሀመድ ጀዔን ገራቲ

ሰይዲ

ከተባ ቀባ ኛራቲ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

አኖ ሱመተን ወትዋዳ

ሰይዲ

ሞቲ ነጃላ ኦዋዳ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

ወረህመቱካ ሹፋኡ

ሰይዲ

ደሚ አማ ኢሳ ሂን ሚኡ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

ሰይደል ወዱድ አደራ

ሰይዲ

ሚ አሙማ ኑ ሀደራ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

አልሀምዱሊለህ ገመኔ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

ሀቢቢ ቢኔሲ በሬ

ሰይዲ

አን አሊ ሂን ቀቡ ኢሲን መሌ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

ኡቱመን ታኤ ሰፊና

ሰይዲ

መርመርቱ ከራ መዲና

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

በገን ታኤ ራዲዮንኬ

ሰይዲ

ነራ ሂን ቴኜ ታቲዮንኬ

ሰይዲ

ሰለላ አላ ሙሀመድ ሰይዲ

ሰለላ አለይ ወሰለም ሰይዲ

## ቃል ግጥም 5

## መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሀባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሀባ

ሰይዲ ጀቹን ኢሳኒ

መርሀባ

ነምኒ ሞሊደ ባሱ

መርሀባ

ሀጃሳ ረቢ አባሱ

መርሀባ

አዛሳ ረቢ ሃባሱ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ(2)

ቆባኮን ታኤ ጉምጉማ

መርሃባ

ማሊፍ ነገተን ዱጉማ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ(2)

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

አባ አረቡን አረባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

ኢሳኒስ ጀዋበኒሩ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

ኮታቲ ሀርካን ኑቀባ

መርሃባ(2)

ኡቱማን ታኤ ሹፊሪ

መርሃባ

አከአመደል ቡሴሪ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ

መርሀባ ነቢ መርሀባ

መርሃባ(2)

## አባሪ አምስት፡ የመውሊድ ክብረበአሉን ክዋኔ ገጽታ የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶ



**ፎቶ አንድ**

**በቁባ አባረቡ ጊቢ ውስጥ የሚገኙ ቤቶች**

**ፍቶ ሁለት**

ከሸህ መሐመድ አሚን አብድዋሂድ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ የሚያሳይ ምስል



በአባ አረቡ የሚገኙ የተወሰኑ  ቁሳዊ ባህሎች በምስል ፎቶ ሶስት



ምእመናን በክብረ በዓሉ እለት ዚያራ ሲያካሂዱ የሚያሳይ ምስል። ፎቶ አራት



ምእመናን በሀድራ ላይ እያሉ አምስት

